# የአከባቢ ሳይንስ

## የመምህሩ መምሪያ  መጽሐፍ አምተስኛ ክፍል

**አዘጋጆች**

ግርማዬ ደፋር

አሰግድ ደረጀ

ፍቃዱ ከበደ

ጉታ ሁንዴ

ታርኩ ዲጋ

**ተርጓሚዎች**

ሞቲ ድንቁ

ሀብታሙ በየነ

ዘዉዴ ረጋሳ

**ገምጋሚዎች**

በቀለ ቀነአ

ቤኪ ቶለሳ

በላቸው አበራ

ዳባ ገመቹ

ነጋሽ ሂቦ

**ግራፍክስ**

ታደሰ ድንቁ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡ የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

## መዉጫ


የኢትዮጵያ መገኛ .......... 1

ምዕራፍ 1 .......... 1

1.1 የኢትዮጵያመገኛ .......... 1

1.2 የኢትዮጵያ ፍጹማዊና አንጻራዊ መገኛ .......... 3

1.3 የኢትዮጵያ መገኛ በካርታ ላይ ከጎሮቤት ሀገሮች ጋር ስነጻጸር .......... 4

1.4 የኢትዮጵያመገኛናየቦታዎችአቅጣጫ .......... 5

1.5 ካርታ ማንሳት .......... 6

**ምዕራፍ** 2 .......... 8

2.1 የሰዉ የምግብ ስርዓተ-እንሽርሽሪት .......... 8

2.2 ዉሃ .......... 14

2.3 ልኬት .......... 16

2.4 የጉልበትምንጮች .......... 22

2.5 ድምፅ .......... 24

**የኢትዮጵያየተፈጥሮሀብት** .......... 29

**ምዕራፍ-** 3 .......... 29

**ለምዕራፉ የተሰጠ የትምህርት ክፍለጊዜ ብዛት**-----------------------------54 .......... 29

3.1 የኢትዮጵያ የአየር ንብረት .......... 30

3.2. የኢትዮጵያየተፈጥሮሃብቶች .......... 33

**ምዕራፍ-** 4 .......... 37

**የኢትዮጵያማህበራዊአከባቢ** .......... 37

4.1 የኢትዮጵያ ህዝቦች የባህል ብዝሃነት .......... 38

**ምዕራፍ-**5 .......... 58

5.1 ኤች.አይ.ቪ.ኤድስበኢትዮጵያዉስጥ .......... 59

5.2 በወረዳዉስጥህገወጥኬሚካሎችእናመድኃኒቶችንመጠቀም .......... 63

5.3 በአከባቢያችንጉዳትልያስከትሉየሚችሉጎጂልማዶች .......... 67

5.4 ድርቅእናረሃብ .......... 70

# ምዕራፍ 1 የኢትዮጵያ መገኛ

**ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት**................. 42

**ከምዕራፉ የሚጠበቁው የመማር ውጤቶች፣**

- አንጻራዊ እናፍፁማዊመገኛንምንነትይገልፃሉ
- ኢትዮጵያን በአንፃራዊ መገኛ በካርታ ላይ ይገልፃሉ
- ኢትዮጵያን በፍፁማዊ መገኛ ይለያሉ
- በኢትዮጵያ ካርታ ላይ የኬክሮስ እና ኬንትሮስ መስመሮችን በመጠቀም የቦታዎችን መገኛ ያሳያሉ
- በኢትዮጵያ ካርታ ላይ የቦታዎችን አቅጣጫ ያሳያሉ
- የመሬት ካርታ፣ ጂፒኤስ እና የጎግል ካርታን በመጠቀም የቦታዎችን መገኛ ይለካሉ፣ይመዝግባሉ
- ካርታዎችንበማዘጋጀትየኢትዮጵያንክልሎችአንፃራዊመገኛያሳያሉ
- የኢትዮጵያጎረቤትሀገሮችን በስምይለያሉ

## መግቢያ

ተማሪዎች በ4ኛ ክፍል ስለ አከባቢያቸዉ መገኛ ተምረዋል፡፡በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለኢትዮጵያ መገኛ ይማራሉ፡፡ ትምህርቱ ከ4ኛ ክፍል ጋር ስለሚያያዝ እንድያስታውሱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በ5ኛ ክፍል የሚማሩትን የትምህርት ይዜቶችን ካለፈው ክፍል ጋር በመገናኘት ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 1.1 የኢትዮጵያመገኛ

ለዚህ የትምህርትይዜት የተሰጠው የክፍለ ጊዜብዛት------------------8

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው ብቃት፣

- የኢትዮጵያጎሮቤትሀገሮችበስምይለያሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

የዚህትምህርትይዜትዋናዋና ነጥቦች የኢትዮጵያ መገኛ እና የጎሮቤት ሀገሮች ዝርዝር ናቸው፡፡ስለዚህ መምህራንስዕል 1.1 ካርታ በመመልከት በአቅጣጫ ላይ በመመስረት ኢትዮጵያን የሚያዋስኑ ሀገሮችን መለየት አለባቸዉ፡፡

## ቅድመዝግጅት

በመጀመሪያ ከአፍርካ ካርታ ላይ የኢትዮጵያ ጎሮቤት ሀገሮች መለየት አስፈላጊ ነው፡፡በመቀጠል በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅና በምዕራብ እንዲሁም በሁለቱ አቅጣጫ መካካል የሚያዋስኑ ጎሮቤት ሀገሮችን ለይተው ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ይህንን ይዜት ለማስተማር ከተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች በቡድን ዉይይት፣ ገለጻ፣ጥያቄናመልስ፣ በግል ተግባራትን ማሰራት ውስጥ ምቹ የሆነውን መርጣችሁ መጠቀም፡፡

## የመማርማስተማርዘዴ

ይህን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን በጥያቄእና መልስ ከሚያውቁት እንድነሱ የኢትዮጵያ ጎሮቤት ሀገሮች እንዲዘረዝሩ ወይም ስማቸዉን እንድጠሩ ማድረግ፡፡ በመቀጠል በስም የዘረዘሩትን ሀገሮች በየትኛዉ አቅጣጫ እንደሚገኙማስጨበጥ ያስፈላጋል፡፡ አቅጣጫ መናገር ከከበዳቸዉ በቡድን ሆነዉ እንዲወያዩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ተማሪዎችየፈጠራችሎታእንድያዳብሩመርዳት

የኢትዮጵያን ጎሮቤት ሀገሮች በየትኛው አቅጣጫ እንደሚገኙ በተለየዩ መንገዶች የሚገልጽ ተማሪዎች ካሉ እድል ይሰጣቸው፡፡ ተማሪዉ በመረጠዉ መንገድ ለመግለጽ የምሞክር ከሆነ አበረታታ፡፡

## ተከታታይሚዘና

ተማሪዎች የኢትዮጵያን ጎሮቤትሀገሮችን በስም የዘረዘሩት ቤየትኛው አቅጣጫ ኢትዮጵያን እንደሚያዋስኑ መግለጽ መቻላቸዉን ማገዝ፡፡ እንዲሁም በግልና በቡድን ውስጥ ያላቸዉን ተሳትፎ መገምገም ያስፈልጋል፡፡

### የተግበርናየመልመጃጥያቄዎችመልስ

**ተግባር 1.1**

1. የኢትዮጵያ መገኛ በካርታ ላይ ማሰያት በሚችሉትሁኔታ እገዛ ማድረግ፡፡
2. ኢትዮጵያንየሚያዋስኑጎሮቤትሀገሮችበካርታላይእንዲያሳዩአግዙ፡፡

**መልመጃ 1.1**

1. ኢትዮጵያን የሚያዋስኑ ሀገሮች ጂቡቲ፣ ሶማልያ፣ ኬንያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ሱዳንና ኤርትራ ናቸዉ፡፡

## 1.2 የኢትዮጵያ ፍጹማዊና አንጻራዊ መገኛ

ለዚህየትምህርትይዜትየተሰጠየክፍለጊዜብዛት ....................................8

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገቡ ብቃት፣

- ፍጹማዊና አንጻራዊ መገኛ ምንነትይገልጻሉ
- የኢትዮጵያ አንጻራዊ መገኛ በካርታ ላይ ያሳያሉ
- የኢትዮጵያፍጹማዊመገኛይለያሉ
- ካርታ በማዘገጀት የኢትዮጵያ ክልሎች አንጻራዊ መገኛ ያሳያሉ፡፡

## ዋናዋናነጥቦች

በዚህ ትምህርት ይዜት ዉስጥ መታወቅ ያለባቸዉ ዋና ዋና ነጥቦች የኢትዮጵያ ፍጹማዊና አንጻራዊ መገኛ ነዉ፡፡ መጀመሪያ የፍጹማዊእና የአንጻራዊ መገኛ ልዩነትን መለየት አስፈላጊ ነዉ፡፡ ኢትዮጵያን የሚያዋስኑ ጎሮቤት ሀገሮች በሚያዋስኑት አቅጣጫ መለየት ይጠበቃል፡፡እንዲሁም ኢትዮጵያ የሚትገኝበት ደረጃ መለየት አስፈላጊ ነዉ፡፡ይህን ይዜት ግልጽ ለማድረግ የመማር ማስተማር ዘዴ በቡድን ዉይይት፣ ገለጻ፣ ጥያቄና መልስ፣የግል ተግባራትን ማሰራት ያስፈልጋል፡፡

### ቅድመ ዝግጅት

መምህራን ኢትዮጵያን የሚያወስኑ ጎሮቤት ሀገሮች መለየት ይጠባቃል፡፡ስለዚህም ካርታን በደንብ በመረዳት ኢትዮጵያ ከምድር ወገብ ወደ ላይ በመለካት በስንት ዲግሪ መካከል እንደሚትገኝ ቀድሞ መዘጋጀት አስፈላጊ ነዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ይህን ርዕስ ለማስተማር ተማሪዎችን በቡድን በማከፋፈል የምስራቅ አፍርካ ሀገሮች ፍጹማዊና አንጻራዊ መገኛ እንዲለዩ ማድረግ፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ጎሮቤት ሀገሮች ከኢትዮጵያ በየትኛዉ አቅጣጫ ላይእንደሚገኙ በካርታ ላይ ይናገራሉ፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፍጹማዊ መገኛ እንዲያብራሩማድረግ፡፡

## ተማሪዎችየፈጠራችሎታእንዲያዳብሩመርዳት

የኢትዮጵያ ፍጹማዊና አንጻራዊ መገኛ በተለየ መንገድ ተማሪዉ መግለጽ ከቻለ እድል ይስጠዉ፡፡ፈጠራዉ ትክክል ከሆነ አበረታታ፡፡

## ተከታተይሚዘና

ተማሪዎች የኢትዮጵያ ፍጹማዊ እና አንጻራዊ በደንብ መግለጽ መቻላቸዉን መገምገም፡፡እንደዚሁም በግልና በቡድን የሚያደርጉትን ተሳትፎ በመከታተል ግንቢ ግብረመል ስመስጠት፡፡

**የመልመጃጥያቄዎችመልስ**

**መልመጃ** 1.2

1. የኢትዮጵያ አንጻራዊ መገኛእና የኢትዮጵያን ከጎሮቤት ሀገሮች ጋር በማስተያየት የኢትዮጵያ መገኛ መግለጽ፡፡ ፍጹማዊ የኢትዮጵያ መገኛ ከምድር ወገብ እና ከሜርዲያን በዲግሪ ርቀት የሚገለጽ ነዉ፡፡
2. ኢትዮጵያ ከኬክሮስ ከሞያሌ ጫፍ$^{30}$፤ከባድሜ ጫፍ 1$^{50}$፤ኬንትሮስ ከአኮቦጫፍ3$^{30}$ እስከ ኦጋዴን ጫፍ 4$^{80}$መሃከልተገኛለች፡፡

## 1.3 የኢትዮጵያ መገኛ በካርታ ላይ ከጎሮቤት ሀገሮችጋር ስነጻጸር

ለዚህ የትምህርትይዘትየተሰጠው የክፍለጊዜብዛት ..................8

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው ብቃት፡**

- የኢትዮጵያጎሮቤት ሀገሮችን በስማቸዉ ይለያሉ፡፡

**ዋናዋናነጥቦች**

ጎሮቤት ሀገሮችጋር በማነጻጸር በካርታ ላይ ኢትዮጵያ መገኛ እንዲያሳዩ ማድረግ ነዉ፡፡

**ቅድመዝግጅት**

የኢትዮጵያ መገኛ ከሌሎች ጎሮቤት ሀገሮች ጋር በማነጻጸር መግለጽ፡፡ መጀመሪያ ኢትዮጵያ መገኛ ጎሮቤት ሀገሮች ጋር ስነጻጸር የት ትገኛለች የሚለዉን ማስገንዘብ አስፈላጊ ነዉ፡፡ስለዚህ ጥያቄ እና በመልስ እንዲሁም በምልከታ ማስተማር ይቻላል፡፡

**የመማርማስተማርዘዴ**

- ተማሪዎች ቀድሞ ከተማሩት ላይ ኢትዮጵያን የሚያዋስኑ ሀገሮች እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡ ኢትዮጵያ ከነዚህ ጎሮበት ሀገሮችጋር ስትነጻጸር የት እንደሚትገኝ እንዲናገሩ አድርጉ፡፡

**ተማሪዎችየፈጠራችሎታእንድያዳብሩመርዳት**

ኢትዮጵያከ ከጎሮቤት ሀገሮች ጋር ሲትነፃጸር የት እንደሚትገኝ በራሣቸዉ ፈጠራ እንዲገልጹ አበረታተቸዉ፡፡

## ተከታታይሚዘና

ተማሪዎች ኢትዮጵያን ከጎሮቤት ሀገር ጋር በማነፃር በደንብ መግለጽ መቻላቸዉን መገምገም፡፡

## የመልመጃመልስ

## መልመጃ 1.3 ሀገር

1. የኢትዮጵያጎሮቤቶች ጂቡቲ፣ሱማልያ፣ኬንያ፣ደቡብሱዳን፣ ሱዳንናኤርትራናቸዉ፡፡
2. ሱማልያ፣ደቡብሱዳን፣ኤርትራ፣ኬንያ፣ሱዳን፣ጂቡቲ

## 1.4 የኢትዮጵያመገኛናየቦታዎችአቅጣጫ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት......................9

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው ብቃት፡

- በኢትዮጵያ ካርታ ላይ የኬክሮስና ኬንትሮስ መሰመሮችን በመጠቀም የቦታዎችን መገኛ ያሳያሉ፡፡.
- በኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉተዋቂ ቦታዎችን ስም ይጠራሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

የዚህ ርዕስ ዋና ይዜት በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ ተዋቂ ቦታዎችን ለይቶ ማወቅ ነዉ፡፡ተማሪዎችያለገደብ የቦታዎች መገኛ እንዲያነሱ ማድረግናትክክለኛ አቅጣጫ ወይም ግንዛቤ መስጠት አስፈላጊ ነዉ፡፡ ይህን የትምህርት ይዜት ለማስተማር የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን ማለትም፣ዉይይት፣ገለፃ፣ጥያቄናመልስ ላይ በመመርሰት ማሰራት፡፡

## ቅድመዝግጅት

በኢትዮጵያዉስጥየሚገኙተዋቂቦታዎችንሁሉበተማሪመፃሀፍዉስጥአልተጠቀሰም፡፡መምህ ራንተዋቂቦታዎችከተለያዩምንጮችበመፈለግመረዳትአስፈላጊነዉ፡፡

## የመማርማስተማርዘዴዎች

በመጸሐፍ ላይ የተዘረዘሩትን እንደመነሻ በመዉሰድ ማጠናከር አስፈላጊ ነው፡፡ተማሪዎች የሚያዉቁትን ተዋቂ ቦታዎችን እንዲናገሩ ማድረግ፣ ሌሎች ደግሞ የተዘረዘሩትን ቦታዎችን አቅጣጫ እንዲያሳዩ አድርጉ፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲያዳብሩ መርዳት

በኢትዮጵያ ካርታ ላይ የተጠቀሱ የታዋቂ ቦታዎችን አቅጣጫ በፍጥነት የመረዳት፡፡ልዩችሎታእና ክህሎት ያላቸዉን ተማሪዎችን በመለየት እዉቀታቸዉን ለሌሎች እንዲያካፍሉ አድረጉ፡፡

## ተከታታይሚዘና

ተማሪዎችተዋቂ ቦታዎችን በአቅጣቻቸዉ መግለጽ መቻላቸዉን መመዘን፡፡በክፍል ዉስጥ የሚያሰዩትን ተሳትፎመከታተልእናመደገፍ፡፡

## የመልመጃመልስ

**መልመጃ** 1.4

1. የሚታወቁ ቦታዎችን ያለገደብ እንዲዘረዝሩማድረግ፡፡

## 1.5 ካርታ ማንሳት

ለዚህርዕስየተሰጠየትምህርትየክፍለጊዜብዛት ........................................9

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገቡ ብቃት፣

- በኢትዮጵያ ካርታ ላይ የቦታዎች አቅጣጫ ያሳያሉ
- "GPS"(Geographical Position System) የግጉል እና የመሬት ካርታ በመጠቀም የተለያዩ ቦታዎችን የመለካት ጭሎታ ያሳድጋሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

የዚህ ርዕስ ይዜት ዋና ዋና ነጥቦ የካርታ ጥቅም እናየ"GPS" አጠቃቀም ላይያተኩራል፡፡በካርታ ላይ መረጃን እንዴት ማንበብ እንደሚቻል ግንዛቤ ማሳደግ፡፡ይህን ትምህርት ለማስተማር የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን ማለትም ፕሮጀክት፣ዉይይት፣ገለፃ፣ጥያቄናመልስ፣ድርጊትላይየተመሰረተየግልስራበማሰራትይሆናል፡፡

## ቅድመዝግጅት

የእስማርት ሞባይልንላይየ"GPS"ንመተግበር ወይም የተለየ "GPS" ያለዉ መሳሪያ ስለምያስፈልግ መምህራን ቀድሞ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊነዉ፡፡ስለዚህ ቀድመዉ ከእንተርኔትመረብ፣የዋቢመፃህፍት በማንበብ መዘጋጀት አለባቸዉ፡፡እንዲሁም ስለካርታ አነሳስ በደንብ ማንበብ አስፈላጊ ነው፡፡

### የመማርማስተማርዘዴዎች

ይበልጥተማሪዎችካርታማንበብናየ"GPS"ንአጠቃቀም በመለማመድ ዕወቀታቸዉን ማሳደግ አለባቸዉ፡፡የተለያዩተግባራትን በመስጠትተማሪዎችበተነሳሽነትእንዲለማመዱማበረታታት፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲያዳብሩ መርዳት

ተማሪዎችየ"GPS"ናካረታአጠቃቀምና ማንበብ ላይ ልዩተሰጦ ያለቸዉን ማበረታታት ከመምህራንይጠበቃል፡፡

## ተከታታይሚዘና

ተማሪዎች በሚያሳዩት ተሳትፎና በሚያደርጉት ልምምድ ላይ በመመሰረት ምዘና ማካሄድ፡፡

## የተግባርናየመልመጃዋያቄዎችመልስ

## ተግባር 1.3

ተማሪዎች በቡድን በመሆን ከኢትዮጵያ ካርታ ላይ ክልሎችን እንዲያሰዩ አግዛቸዉ፡፡

**መልመጃ 1.5**

1. የወረቀት ካርታ፣ ሰንጠረዥ፣ እንጨት ወይም ልብስ ላይ የሁለቱ ፈርጆች ወክል ወይም ግማሽ የመሬትአካልነዉ፡፡ጥቅሙ የተለያዩ መረጃዎችን ግልጽ በሆነ መንገድ ይገልፃል፡፡
2. "GPS"ንከሳተላይት ጋርበመገናኘት የምሰራ የቴክኖሎጅ ዉጤት ነዉ፡፡.

## የምዕራፍ 1 የማጠቃለያጥያቄዎችመልስ

**I. እዉነት/ሐሰት**

1. እዉነት 2. እዉነት

**II. አዛምድ**

1. ለ 3. ሀ 5. ሐ

2. ሠ 4. መ

**III. ምርጫጥያቄችመልስ**

1. ሀ 2. ሐ

**IV. የአጭርገለፃጥያቄዎችመልስ**

1. ካርታበወረቀት ላይ የተነሳ ሲሆን "GPS" ግን የኤሌክትሮንክስ መሳሪያ ሆኖ ከሳተላይት ጋር የሚያገናኝነዉ፡፡
2. የአንድ አገር ወይም የአንድ ቦታ መገኛ ሌላ ከምታወቀዉ አገር ወይም ሌላ ቦታ በማስተያየት የሚገለጸዉ የአንፃራዊ ግኝት ሲባል እዉነተኛ መገኛ ግን የአከባቢ ወይም የአንድ አገር የኬክሮስ እና የኬንትሮስ መስመር በመጠቀም ትክክለኛዉን ይገልፃል፡፡

# ምዕራፍ 2

## ሳይንስን ግልፅ ማድረግ

**ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት**...............54

**ከምዕራፉ የሚጠበቁው የመማር ውጤቶች፣**

- የምግብ ስርዓተ-እንሽርሽሪት አቢይ ክፍሎችን ሥማቸዉን በመዘርዘር መሰረታዊ ተግባራቸዉን ይገልፃሉ
- የምግብ ስርዓተ-እንሽርሽሪት ክፍሎች ጥቅሞቻቸዉን ይገልፃሉ
- የዉሃ ጥቅሞች ይዘረዝራሉ
- መጠነ-ቁስ፣ርዝመት፣ይዜት፣ጊዜና የመሳሰሉትን ለመለካት ይለማመዳሉ
- እንቅስቃሴእና ለዉጥ እንድፈጠር የምረዱ የጉልበት ምንጮችእና ጥቅሞች ለምሳሌ፣ ምግብ፣ ነዳጅ፣ የፀሐይ ብርሃን ያብራራሉ፡፡
- የድምፅን ፍቺ በመስጠት በተለያዩ ነገሮች ዉስጥ የመተላለፍ ባህርያቸዉን ብራራሉ፡፡

### መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተለያዩ ርዕሶችን እንደ የምግብ እንሽርሽሪት፣የዉሃ ጥቅም፣ ልኬት፣የጉልበትና የድምፅ ምንጮች የመሳሰሉትን ይማራሉ፡፡ እያንዳንዱ ርዕስ የተለያዩ ይዜቶችን ይዘዉ ይገኛሉ፡፡የሰዉ የምግብ ስራዓተ-እንሽርሽሪት ሥር የምግብ እንሽርሽሪት ፍቺ፣ የምግብ እንሽርሽሪት ክፍሎች፣ የምግብ ስራዓተ-እንሽርሽሪት ጥቅሞች ይማራሉ፡፡ዉሃ በምለዉ ምዕራፍ ሥር ደግሞ የዉሃ ፍቺ፣ የዉሃ ቀመርና ዉሃ ህይወት ላላቸዉ ያለዉን ጥቅም ይማራሉ፡፡በተመሳሳይመንገድልኬትበምለዉምዕራፍሥርየመጠነ-ቁስ፣ ርዝመት፣ ይዜት፣ጊዜ፣መጠነ ሙቀትና የመሳሰሉትን ልኬት ይማራሉ፡፡ በተጨማር የጉልበት ፍቺና ምንጭ፣ የድምፅ ፍቺ፣ዓይነትና መተላለፍይማራሉ፡፡

## 2.1 የሰዉ የምግብ ስርዓተ-እንሽርሽሪት

ለዚህ ርዕስ የተሰጠ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ብዛት --------------------20

ቢያንስ ተማሪዎች መጎናጸፍ ያለባቸዉ ብቃት፡

- በምግብስርዓተ-እንሽርሽሪት ዋና ዋና ክፍሎች ስሞቻቸዉንና መሰረታዊ አገልግሎታቸዉን ያብራራሉ፡፡
- በምግብ ስርዓተ-እንሽርሽሪት የክፊሎቹን ጥቅም ይገልፃሉ፡፡

## ዋና ዋና ሃሳቦች

የምግብስርዓተ-እንሽርሽሪት በምለዉ ሥር፣የምግብ እንሽርሽሪት ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ የምግብ እንሽርሽሪት መዋቅር (እፍ፣ ምላስ፣ ጉሮሮ፤ ኢሶፋገስ፣ ጨጓራ፣ ቀጭንአንጀት፣ ትልቁአንጀት፣ቋተ-ኩስናቱሊ)፣ የእያንዳንዱ የምግብ እንሽርሽሪት መዋቅር ሥራ መማር አለባቸዉ፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር 20 ክፍለ ጊዜ ተሰቷል፡፡ በዚህ በተሰጠ ክፍለ ጊዜ ዉስጥ ተማሪዎች ማግኘት የሚገባችው እንድያገኙ የተለያዩ የመማር ማስተማርና የትምህርት መርጃ መሳሪያ መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር የሚዉሉ የመማር ማስተማር ዘዴ ዉስጥ ጥቅቶቹ፡ ጥያቄና መልስ፣ የቡድን ዉይይት፣ የጥንድ ዉይይት፣ የክፍል ሙሉ ዉይይት፣ገለፃ፣ፕሮጀክት፣የእንሽርሽሪት ቧንቧ ጫወታ ዘዴእና መልከታናቸዉ፡፡

በዚህ በትምህርቱ ርዕስ ሥር ለማስተማር፤ የምግብ ጥቅሞችና የምግብ ምድቦች በሦስተኛ ክፍል የተማሩት፤ እንዲሁም የምግብ ምንነት፣ ንጥረ ምግብና የተመጣጠነ ምግብ በአራተኛ ክፍል ዉስጥ ከተማሩት ጋር ማያያዝ ከመምህራን ይጠበቃል፡፡ ምግብ ለተለያዩ ጥቅም ላይ መዋል የሚችለዉ የምግብ እንሽርሽሪት ስካሂድ ብቻ መሆኑ ንእንዲረዱ ማድረግ፡፡ስለምግብስርዓተ-እንሽርሽሪትና ከመዋቅራቸዉ ጋር በማያያዝ መማር የወደፊት ለምማሩት መሰረት በመሆን እንደምያገለግል መታወቅ አለበት፡፡

## ቅድመዝግጅት

መምህር/ትይህን ርዕስ ማስተማር ከመጀመርህ/ሽ በፊት የሚያስፈልገዉን ዝግጅት መጠናቀቅ ይጠበቅብሃል/ሻል፡፡ ቅድመ ዝገግጅት ከምያስፈልገዉ አንዱ የትምህርት እቅድን በጥልቀት ማዘጋጄት ነዉ፡፡ ለእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የትምህርት ዕቅድ ማወጣት ግልፅ ነዉ፡፡ ለእያንዳንዱ ትምህረት ስትዘጋጅ ከርዕሱ ጋር የሚያያዙ በተማሪ መፅሐፍና በመምህሩ መመሪያ ላይ የተጠቀሱትን ድርግቶች፣ መልመጃዎች መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ከርዕሱጋር የሚገናኙ ከዋቢ መፅሕፍት በማንበብ በደንብ መዘጋጀት አስፈላጊ ነዉ፡፡ እንዲሁም፤ ተማሪዎችን የሚፈለገዉ ብቃት ማድረስ የሚያስፈልጉ የትምህረት የመርጃ መሳሪያዎችን ከአከባቢ ከሚገኙ ቁሶች በቅድሚ ያዘጋጅ፡፡ርዕሱን ለማስተማር የሚረዱ የትምህረት መርጃ መሳሪያዎች ዉስጥ የተወሰኑት፡

- የምግብእንሽርሽሪትየሚያሳዩሥዕል፣ፎቶእናፖሰታር
- የምግብ ስረዓተ እንሽርሽሪት ሞዴሎች

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ካለፉት ክፍሎች ሰለ ምግብ የተማሩትን ተማሪዎችን በመጠየቅ ትምህረቱን መጀመር፡፡ ምግብ ሳይበሉ ስመጡ ምን እንደምሰማቸ መጠይቅ፡፡ የምመገቡት ምግብ በሰዉነታቸዉ ዉስጥ የምግብ እንሽርሽሪት ስካሄድ ብቻ ለምፈለገዉ ጥቅም መዋል እንደሚችል ደግመዉ እንድያስታዉሱ ማድርግ፡፡


የምግብ እንሽርሽሪት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎች በግል እንዲያስቡና በጥንድ ደግሞ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ በጥንድ ከተወያዩ ሃሳቦች ዉስጥ የተወሰኑትን በመዉሰድ ለክፍል እንድገልጹ ማድረግ፡፡ ተማሪዎች ከሚያቀርቡ ሃሳብ በመነሳት ስለምግብ እንሽርሽሪት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቂ ገለፃ መሰጠት፡፡ ተማሪዎች አራት አራት በመሆን የምግብ እንሽርሽሪት ዋና ዋና ክፍሎች ስም እንድሰይሙ ማመቻቸት፡፡ተማሪዎች የሰየሙት ሥዕል እና በባለሞያ የተሰየመዉ ሥዕል ወይም ሞዴል በመጠቀም የምግብ እንሽርሽሪት ዋና ዋና ክፍሎች በማነፃፃር ትክክለኛዉን በመዉሰድ ለክፍል እንድያቀርቡ አድረጉ፡፡
ተማሪዎች የሰዉ የምግብ ስርዓት-እንሽርሽሪት ሥዕል በሚያነሱበትጊዜ ቁጥጥር በማድረግ፣ አቅጣጫ በማሳየት ለክፍል እንድያቀርቡ ከተደረገ በኃላ የሚታዩ ሰህተቶች በማረም ለክፍል በቂ ግንዛቤ መስጠት፡፡

በመቀጠል ተማሪዎች በእያንዳንዱ የምግብ እንሽርሽሪት ቧንቧዋናዋና ክፍሎች ላይ በቡድን እንድወያዩ አደርግ፡፡ የእያንዳንዱ ዋና ዋና ክፍሎች ጥቅማቸዉን በቡድን ከተወያዩ በኋላ  የዉይይታቸዉን ሃሳብ ለቡድን እንድያቀርቡ አድረጉ፡፡ ተማሪዎች ሃሳባቸዉን ካቀረቡ በኋላ  ከሃሳባቸዉ በመነሳት ሀሳብ ላይ ገለፃ አድርጉ፡፡ተማሪዎች በቡድን ከተመደቡ በኋላ   የምግብ እንሽርሽሪት ቧንቧ ጨወታ እንድጫወቱ መድረግ፡፡የእንሽርሽርት ጫዋታ እንድምከተለዉ ልሆንይችላል፡፡

## የእንሽርሽርት ጫዋታ

በትምህርት ክፍል ዉስጥ ጠመኔ ወይም ኖራድንጋይ ወይም ከሰል በመጠቀም የምግብ ስረዓት-እንሽርሽሪት ፅንሰ ሃሳብ የሚያሰይ እንድያነሱ አድረግ፡፡ ክፍል ዉስጥ የማይመች ከሆነ በመጫወቻ ሜዳ ላይ ክር፣ ችካል ወይም ድንጋይ በመጠቀም ከታች የሚታየዉ ሥዕል የሚመስለዉን በምልክት እንድያሳዩ አድርግ፡፡ በክፍል ዉስጥ ወይም በመጫወቻ ሜዳ ላይ በተዘጋጀዉ ወይም በተቀመጠዉ ምልክት ዉስጥ በመሄድ

እያንዳንዱ ቦታ የተቀመጡ ነገሮች እንድገልጹ አድርግ፡፡በተግባር ጊዜ ወይም ከተግባር በፊት አንዳንድ ቦታ በመጨመር መሰየም ይቻላል፡፡




## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ መርዳት

ልዩ ተስጥኦና ከፍተኛ ግንዛቤ ያላቸዉን ተማሪዎችን በማገዝ/በመርዳት የፈጠራ ችሎታ እንድያዳብሩ አብረታታ፡፡ ተማሪዎች ብቃትና ነገሮችን የመፍጠር ችሎታእንዲኖራቸዉ በተግባር ላይ እና ተማሪዎች የሚያሳትፍ የመማር ማስተማር ዘዴ በመጠቀም ዉጤታማ አድረግ፡፡በምማሩትየትምህርቱ ይዜት ላይ ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ የመሳተፍ እድል እንዲኖራቸዉ አድርግ፡፡ተማሪዎች በራሳቸዉ ጥረት የተለያዩ ግኝቶች እንድያመነጩ አበረታታ፡፡

ተማሪዎች አምስት አባላት ባለዉ ቡድን በመደራጀት በአከባቢ ከሚገኘዉ የምግብ እንሽርሽሪት ክፍሎች የሚያሳ ይሞዴል እንዲሰሩ ፕሮጀክት ስጣቸዉ፡፡ ለዚህ ስራ የምዉሉ ቁሶች፡ጣርሙስ፣ፕላስትክ፣የእንጨት ቅርፍት፣ ጠጠር፣ሙጫ፣እንጨት፣ ክርና የመሳሰሉ ትናቸዉ፡፡ ተማሪዎች በቡድን የሰሩትን ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡ በሚያቀርቡበት ጊዜ መከታተልና እርማትመስጠት አስፍላጊ ነዉ፡፡ተማሪዎች ለቀረቡት ፈጠራ አብረታታቸዉ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን በዚህ ርዕስ ሥር ያለዉን ሁሉ በተለያዩ መንገድ ማለትም በጥያቄዎች፣ በተግባራትና በፕሮጀክቶች እንዲሰሩ መድረግ፡፡ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን የሰሩትን በቅረበት መከታተልናየግንባታ ሃሳብ መስጠት፡፡

- ተማሪዎች የሰዉ የምግብ ስረዓተ-እንሽርሽሪት አካላት በሚወያዩበትእና በሚያቀርቡት ጊዜ መከታተል፡፡
- የተማሪ አፈፃፀም እየመዘገቡ መሄድ፡፡

***የተግባር 2.1 መልስ***

***1. የአዋቅሰዉ የጥርስ አይነቶች: የፊት ጥርስ፣ የዉሻ ክራንቻ፣ ቀዳሚ መንጋጋና ድህረ መንጋጋ ናቸዉ፡፡***

***2. የፊትጥርስ = (2/2)x2 = 8***

***ክራንቻ = (1/1)x2 = 4***

***ቀዳሚ መንጋጋ= (2/2)x2 = 8***

***ድህረ መንጋጋ = (3/3)x2 = 12***

***3.***




**የፊትጥርስ** ፊለፊት የሚገኝ ጥርስ ነዉ፡፡ ጠፍጣፋና ሹል ቅርፅ ያለዉ ሆኖ ምግብ ለማኘክ እና ለመቁረጥ ይረዳል፡፡

**ክራንቻ**: ከፊት ጥርስ በሁለቱም ጎኖች የሚገኝነዉ፡፡ክራንቻ ጫፍ ላይ በጣም ሹል ስላለዉ ምግብ ለመሰንጠቅእና ለመብላትያግዛል፡፡

**ቀዳሚ መንጋጋ**: ከክራንች ቀጥሎ የሚገኝ ነዉ፡፡ ቀዳሚ መንጋጋ ጠፍጣፋ ቅርፅ ስላለዉ ምግብ ለመሰባበርና ለመፍጨትያግዛል፡፡

**ድህረመንጋጋ**: ከኋላ መጨረሻ የሚገኝ ነዉ፡፡ እንደ ቀዳሚ መንጋጋ ጠፍጣፋ ቅርፅ ስላለዉ ምግብ ለመሰባበርናለመፍጨትያግዛል፡፡

**ተግባር 2.2**

1.

| የሚያመነጨዉአካል | ኢንዛይሞች |
|---|---|
| ከጨጓራግድግዳይመነጫል | ፔፕስን፣ሬኒን |
| ቀጭንአንጀት | ሱክሬስ፣ማልተስ፣ጋላክቴስ |
| ጠፊያ | ትራይፕስን፣ልፔስ |

2.

| ኢንዛይሞች | ተግባራቸዉ |
|---|---|
| ፔፕስን | ፕሮቲንወደፔፕቶንይለዉጣል |
| ሬኒን | የወተት(ኬዝን) ፕሮቲንእንድረጋማድረግ |
| ሱክሬስ | ሱክሮስንወደግሉኮስእናፍሩክቶሰይቀይራል |
| ማልተስ | ማልቶስወደሁለትግሉኮስይቀይራል |
| ጋላክቴስ | ላክቶስወደግሉኮስናጋላክቶስይቀይራል |
| ትራይፕስን | ፕሮቲንወደፔፕታይዲይቀይራል |
| ልፔስ | ልፒድወደግላይሴሮልናፋትአሲድይቀይራል |

**መልመጃ 2.1**

1. የምግብ እንሽርሽሪት ማለት ትላልቅ ምግብ በፊዚካልና በኬሚካል ወደ ትንንሽ ዩኒት የመሰባበር ሀደትነዉ፡፡
2. የምግብስርዓተ-እንሽርሽሪት ዋና ዋና ክፍሎች የሆኑት አፍ፣ጉሮሮ፣ኤሶፋገስ፣ ጨጓራ፣ ቀጭንአነጀት፣ ትልቅ አንጀት፣ቋተ-ኩስናቱሊ ያቀፈነዉ፡፡
3. የሰዉ የምግብ ስርዓተ-እንሽርሽሪት መሰረታዊ ተግባራት ከሰንጠረዥ 2.1 ታገኙታላቹ፡፡

## 2.2 ዉሃ

***ለዚህ ርዕስ የተሰጠየ ትምህርት ክፍለጊዜብዛት --------------------3***

*ቢያንስ ተማሪዎች መጎናጸፍ ያለባቸዉ ብቃት፡*

- *የዉሃ ጥቅም ይዘረዝራሉ፡፡*

### *ዋና ዋና ሃሳብ*

*በዚህ ርዕስ ሥር ስለ ዉሃ ምንነት፣ የዉሃ ቀመርና ዉሃ ህይወት ላላቸዉ ሁሉ ያለዉን ጥቅም ትማራላቹ፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር ሶስት ክፍለ ጊዜ ተሰቷል፡፡ተማሪዎችአነስተኛየመማርብቃትእንድዳብሩየተለያዩየመማርማስተማርዘዴዎችን፣የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና የተለያዩ ምዘናዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡ተማሪዎች ይህን ርዕስ መማራቸዉ ለወደፊት በሁለተኛ ደረጃና በከፊተኛ ትምህርት ተቋም ለምማሩት ትምህርት መሰረት ይሆናል፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር የሚረዱ የመማር ማስተማር ዘዴዎችዉስጥየተወሰኑትእንደምከተለዉ ይሆናል፡፡*

- *የቡድንናየጥንድዉይይት*
- *በገለፃ*
- *በፕሮጀክት*

### *ቅድመ ዝግጅት*

*መምህር/ትይህን ርዕስማስተማርከመጀመር በፊትከዚህ በታች ያሉትን መተግበር ይጠበቅቦታል፡፡*

- *የትምህርት እቅድን ማዘጋጀት፡፡*
- *ከርዕሱጋርየሚገናኙሃሳቦች ከተማር መፅሐፍና ከመምህሩ መምሪያ በደንብ አንብቦ መዘጋጀት፡፡*
- *ከርዕሱጋር የሚገናኙ ተግባሮችና መልመጃዎችን መረዳት፡፡*
- *ከርዕሱጋርየሚገናኙ ከወቢ መፅሐፍት አንብቦ የራሱን/ሷን ግንዛቤ ማሳደግ፡፡*
- *ከታች የትምህርቱን ግብ ልያጨብጡ የምችሉትን የትምህርት መርጃ መሳሪያ ማዘጋጀት፡፡*
    - *የዉሃ ቀመር የሚያሳይ ቻርት*
    - *የዉሃ ጥቅሚ የሚያሳይ ሰሌዳ*

***የመማርማስተማር ዘዴ***

- *ተማሪዎች በቡድን በቡድን ሁኖ በዉሃ ምንነትላይ እንድወያዩ  አድርግ፡፡*

- የዉይይታቸዉን ዉጤት ተራ በተራ ለክፍል እንድያቀርቡ አድርግ፡፡ከተማሪዎች ሃሳብ በመነሳት በቂ ግንዛቤ ተማሪዎችን ማስጨበጥ፡፡ ሃሳቡን በስፋትለማቅረብ የዉሃ ቀመር ቻርትመጠቀም ይችላሉ፡፡
- በመቀጠል ዉሃ ህይወት ላላቸዉ ሁሉ ያለዉን ጥቅም ሰፊ ጊዜ በመስጠት እንድወያዩ ማድረግ፡፡ተማሪዎች በተወያዩት ላይሃሳብ እንድለዋወጡ ማድረግ፡፡ የዉሃጥቅም የያዘ ቻርት በመጠቀም ዉሃ የሰዉል ጅን ጨምሮ ህይወት ላላቸዉ ሁሉ የሚሰጠዉን ጥቅም ላይ ገለፃ ማድረግ፡፡

***ተማሪዎችየፈጠራችሎታእንድያዳብሩመርዳት***

*ተማሪዎች በቡድን በመሆን በአከባቢ ከምገኙ ነገሮች ማለትም ለስላሳ ግንድ ያለቸዉ ዕፅዋት፣ከእንጨትልጥ፣ከአሸዋናከመሳሰሉትየዉሃ ቀመር ሞዴል እንዲሰሩ ፕሮጀክት ስጡ፡፡የሰሩትን ሞዴል ለክፍል እንድያቀርቡ አድርጉ፡፡*

## ***ተከታታይምዘና***

- *ተማሪዎችን በዚህ ርዕስ ሥር ያሉትን የተለያዩ ጥያቄዎች፣ ተግባራት፣ ፕሮጀክቶችን ሁሉ እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ ተማሪዎች በቡድን ወይም በግል የሰሩትን በቅርበት መከታተልና ገንቢ ሃሳብ መስጠት፡፡*

***የተግባራትመልስ***

***ተግባር 2.3***

ከአንድብርጭቆዉሃናከወርቅአንዱንምረጡበትባሉዉሃእንደምትመርጡይጠበቃል፡፡ምክንያቱምመኖርናህይወትማስቀጠልአይቻልም፡፡ህይወትበሌለበትወርቅአይጠቅምም፡፡

***ተግባር 2.4***

1. በዉሃ በሚሟ ስኳር ዉስጥ፡ዉሃ አሟሚ ሲሆን ስኳርደግሞ ሟሚ ነዉ፡፡

***መልመጃ*** 2.2

1. ዉሃዉህድሆኖበሰዉነትዉስጥለተለያዩጥቅሞችይዉላል፡፡
2. ዉሃበሶስትሁነትይገኛል፡፡እነሱም፡የጠጣርሁነት፣የፈሳሽሁነትናየጋስሁነትናቸዉ፡፡
3. የዉሃጥቅሞች፡
   - ዉሃየነገሮችጥሩአሟሚነዉ፡፡
   - ዉሃምራቅለመፍጠርይረዳል፡፡
   - ዉሃየአካልንመጠነ-ሙቀትለመቆጣጠርይረዳል፡፡
   - ዉሃበላብ፣በሽንትእናበሰገራቆሻሻንለማስወገድይረዳል፡፡

- ዉሃየስገራድርቀትንለመከላከልይረዳል፡፡
- ዉሃለልመት/እንሽርሽርይዉላል፡፡
- ዉሃበምመጡንጥረምግቦችዉስጥከፍተኛድርሻአለዉ፡፡
- ዉሃ የተለያዩ በሽታዎችን ለመከላከል ይዉላል፡፡
- ዉሃ ቆዳ እንድያብረቀርቅ ያደርጋል፡፡
- ዉሃየአካልንድርቀትይከላከላል፡፡

## 2.3 ልኬት

***ለዚህ ርዕስ የተሰጠ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ብዛት-------------------13***

የርዕሱየመማርዉጤት

በዚህ አካሄድና በርዕሱ መጨረሻ ተማሪዎች፡

ርዝመት፣መጠነ-ቁስ፣ጊዜ፣ይዜትናመጥነ-ሙቀትመለካትይለማመዳለ

***ዋናዋናነጥቦች***

በዚህርዕስሥርየተጠቀሱትነጥቦችርዝመት፣መጠነ-ቁስ፣ጊዜ፣ይዜትናመጥነ-ሙቀትመለካትላይትኩረትይሰጣል፡፡ይህን ርዕስ ለማስተማር የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን ማለትም እንደ ገለፃ፣ ትዕይንት፣ፕሮጀክት፣ የቡድንና የጥንድ ዉይይት፣ ምልከታ፣ የቡድን ሥራ መጠቀም እንድሁም የተለያዩ አቅርቦትን መጠቀም ይቻላል፡፡

***ቅድመ ዝግጅት***

መምህር/ት ይህን ርዕስ ማስተማር ከመጀመርህ/ሽ በፊት የሚያስፈልገዉን ዚግጅት መጠናቀቅ ይጠበቅብሃል/ሻል፡፡ ቅድምያ ዝገግጅት ከምያስፈልገዉ አንዱ ጥልቀት ያለዉና የሚፈለገዉ ችሎታ ጋ ማድረስ የሚችል የትምህርት እቅድን ማዘጋጄት ነዉ፡፡ ይህን ዕቅድ ስታዘጋጅ ከርዕሱ ጋር የሚገናኙ በተማሪ መፅሐፍ ዉስጥ የተገለፁትን መገንዘብ አለቦት፡፡ ከርዕሱ ጋር የሚያያዙትን ድርግቶች፣ መልመጃዎች ቀድሞ መዘጋጀትና መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በተጨማሪም፡ ከርዕሱ ጋር የሚገናኙ ከዋቢ መፅሐፍት በማንበብ በደንብ መዘጋጀትና የራስን ግንዛቤ ማሻሻል ይጠበቅበታል፡፡ እንድሁም፣ ተማሪዎችን የሚፈለገዉ ብቃት ጋ ለመድረስ የሚያስፈልጉ የትምህረት የመርጃ መሳሪያዎችን ዉስጥ የተወሰኑት፡

- መስመሪያ
- ሜትር
- ሚዛን

- ሰዓት
- መጠነ-ሙቀት
- ስሊንደር
- የተለያዩ የዉሃ መጠን መያዝ የምችሉ ጣርሙሶች እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

## የመማር ማሰተማር ዘዴ

የልኬት ትረጉም በመጠየቅ ጀምር፡፡ የልኬትን ፍቺ ከመለሱ በኃለ ተጨማርና መስተካከያ ሃሳብ በመስጠት የተለያዩ የተሰፋር አከላትን የተማከሉ አሃዶችን እንድዘረዚሩ አድረጉ፡፡ እንድዘረዝሩ ከምጠበቅባቸዉ ዉስጥ፡ የርዝመት የተማከለ(SI) አሃድ ሜትር(m)፣ የጊዜ የተማከለ(SI) አሃድ ሶኮንድ(s)፣ የመጠነ ቁስ የተማከለ (SI) አሃድ ኪሎግረም(kg)፣ የይዜት የተማከለ(SI) አሃድሊትር(l)ና የመጠነ ሙቀት የተማከለ(SI) አሃድ ኬልቭን(K) ናቸዉ፡፡ ተማሪዎችበአከባቢ የሚገኙ ነገሮች(የበህላዊ ዘዴ) ርዝመትን፣ መጠነ ቁስን፣ ጊዜን፣ ይዜትንና መጠነ ሙቀትን የምለካበት ሰዎችን በመጠየቅ ለክፍል እንድያቀርቡ አደርጉ፡፡ ለምሳሌ ርዝመትን ለመለካት(ስንዝር፣ ክንድ፣ እርምጃና ጫማ)፣ መጠነ ቁስ ለመለካት(ጣሳ፣ ኩንታልና ሰፌድ)፣ ጊዜን ለመለካት(ፀሐይ)፣ ይዜትን ለመለካት(እንስራ፣ ጮጮ፣ ብርጭቆና ዋናጫ) እና መጠነ ሙቀት ለመለካት(ቆዳችን) መጠቀም እንደምቻል በቂ ማብርያራ መስጠትና ሃሳባቸዉን እንድያጠናክሩ ማድረግ፡፡ ስያቀርቡ ስህተትካለ የማስተካከያ ሃሳብ መስጠት፡፡ተማሪዎች በቡድን ሆኖ በሚቀጥለዉ ሃሳብ ላይ በቅደም ተከተል እንድወያዩና እንድሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

- በልኬት ጥቅም ላይ ተማሪዎችን ትንሽ አባል ባለዉ ቡድን እንድወያዩ አድርጉ፡፡.
- የባህልና የሳይንስ አሃዶችን ጊዜ፣ መጠነ ቁስ፣ ርዝመት በመለካት በጥቅሞቻቸዉ ላይ እንድወያዩ አድርጉ፡፡ እንደዝሁም በተግባር 2.5 ስር ላሉት ጥያቄዎች በጥንድ ተወያይተዉ ለክፍል እንድያቀርቡ አግዛቸዉ፡፡
- በምያቀርቡበት ጊዜ ስህተት ካለ የማስተካከያ ሃሳብ በመስጠት እንድያስተካክሉ አድርጉ፡፡
- ተማሪዎችን አነስተኛ አባል ባለዉ ቡድን በማደራጀት መሰረታዊ ፊዚካላዊ አካላትና መሰረታዊ አሃዶች ላይ ተወያይተዉ ለክፍል እንድያቀርቡ አድርጉ፡፡.
- በማስመሪ በመጠቀም በስዕል 2.6 እንደታየዉ ርዝመቱ 4.3 ሴንትሜትር የሆነ እንጨት በማዘጋጀት ተማሪዎች እንድለማመዱ ሁኔታዉን አመቻቹ፡፡

- በመቀጠል መልመጃ 2.3 ስር የተሰጡትን ጥያቄዎች በጥንድ ከሰሩ በኃላ ለክፍል እንድያቀረቡ ሜትር በመስጠት አግዙት፡፡ በተጨማር የርዝመትን ፍቺ ላይ ገለፃ መስጠት፡፡
- ተማሪዎችን አነስተኛ አባል ባለዉ ቡድን በመደራጀት የተማከለና ተወራራሽ አሃዶች ላይ ተወያይተዉ ለክፍል እንድያቀርቡ አድረጉ፡፡
- የመጠነ- ቁስ ፊቺ በመስጠት፤ በአከባቢያቸዉ የነገሮች መጠነ ቁስ ማለትም ቅቤ፣ ማር፣ እህልና የመሳሰሉት በምን እንደምለኩ የአከባቢ ሰዎችን በመጠየቅ በቡድን እንድወያዩ በማድረግ ተጨማሪ ሃሳብ ስጡ፡፡
- ሚዛንን በመጠቀም የነገሮችን መጠነ ቁስ መለካት እንድለማመዱ አበረታቱ፡፡
- መጠነ-ቁስ ለመለካት የሚያገለግሉ የበህልና የሳይንስ መሳሪያዎችን ልዩነቶቻቸዉ ላይ ተወያይተዉ ለክፍል እንድያቀርቡ አድረጉ፡፡
- በተጨማሪም የመልመጃ 2.4 ጥያቄዎች በግል ከተለማመዱ በኃለ በቡድን እንድወያዩበት ሁኔታዉን አመቻቹ፡፡
- በጊዜ ፍቺ ላይ በጥንድ እንድወያዩበት ሁኔታዉን አመቻቹ፡፡
- ተማሪዎችን አነስተኛ አባል ባለዉ ቡድን በማደራጀት ጊዜን በመለካት ላይ ተወያይተዉ ለክፍል እንድያቀርቡ አድረጉ፡፡
- በመቀጠል፣ የተለያዩ የሰዓት ዓይነቶችን ክፍል ዉስጥ በማቅረብ ተማሪዎች የሴኮንድን፣ የደቂቃንና የሰዓትን ቆጣሪ እንድለማመዱ ሁኔታ በማመቻቸት አዟቸዉ፡፡ በተጨማሪ የተግባር 2.6 ጥያቄዎች ላይ ተወያይተዉ ለክፍል እንድያቀርቡ አድርጉ፡፡
- በይዜት ፍቺ ላይ በቂ መብራሪያ በመስጠት፣ በአከባቢያቸዉ የፈሳሽን ይዜት ለመለካት የሚያገለግሉ ነገሮች ላይ በጥንድ ሆነዉ እንድወያዩ በማድረግ ለክፍል እንድያቀርቡ ሁኔታዉን ማመቻቸት፡፡ በምያቀርቡበት ጊዜ ስተቶች ካሉ እርማት በመስጠት ተማሪዎች ትክክለኛዉን ሃሳብ እንድይዙ ማድረግ፡፡
- በባህላዊና በሳይንሳዊ ልኬት መካከል ያለዉን ቀድመዉ በጥንድ ተወያይተዉ ቀጥለዉ ደግሞ በቡድን ከተወያዩ በኃለ ለክፍል እንድያቀርቡ አበረታቱ፡፡
- በመቀጠል ቤተሰቦቻቸዉንና በአከባቢ ያሉትን ሰዎች የነገሮች ይዜት በምን መለካት እንደምቻል በመጠየቅ ለክፍል እንድያቀርቡ ካደረጋቹ በኃለ የስሊንደር ልኬት በመታገዝ የፈሳሽን ይዜት ለመለካት መከተል ያለበት ህደቶች ላይ በተወሰነ ቡድን ተወያይተዉ ለክፍል እንድያቀርቡ ሁኔታ ማመቻቸት፡፡ በተጨማሪም፣ የመልመጃ 2.5 ጥያቄዎችን በቡድን እንድለማመዱ ማበረታታት፡፡

- በመጠነ-ሙቀት ፍቺ ላይ በቂ መብራርያ በመስጠት፣ በአከባቢያቸዉ መጠነ-ሙቀት ለመለካት የሚያገለግሉ ነገሮች ላይ በጥንድ ሆነዉ እንድወያዩ በማድረግ ለክፍል እንድያቀርቡ ሁኔታዉን ማመቻቸት፡፡ በምያቀርቡበት ጊዜ ስተቶች ካሉ እርማት በመስጠት ተማሪዎች ትክክለኛዉን ሃሳብ እንድይዙ ማድረግ፡፡ በተጨማሪም ተግባር 2.7 እንድሰሩ ሁኔታ ማመቻቸት፡፡
- በመቀጠል የመጠነ-ሙቀት ታዋቅ አሃዶች ላይ በጥንድ ከተወያዩ በኃላ ለቡድን እንድገልጹ ማድረግ፣ በመልመጃ 2.6 ስር ያሉትን ጥያቄዎች በግል ከተለማመዱ በኃላ በቡድን እንድወያዩ ማበረታታት፡፡ ተማሪዎች ተራ በተራ ለክፍል ከሚያቀርቡ በመነሳት ዋናማጠቃለያ ሃሳብ በመስጠት ትምህርቱን ክፍለ ጊዜ ማጠቃለል፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንድያዳብሩ መርዳት**

ተማሪዎችን በቡድን በተለያዩ ርዕስ ስር በማደራጀት ከተለያዩ አካላት መረጃን በመሰብሰብ እንድጠናቅሩ አድርግ፡፡ የጠናቀሩትን ሃሳቦች ለክፍል እንድያቀርቡ በማድረግ ሃሳብ እንድለዋወጡ አድርግ፡፡

## ተከታተይ ሚዘና

- በሚቀረበዉ የትምህርት ርዕስ ፍሬ ሃሳቦችን (ዋና ነጥቦች) በመስተወሻ እድይዙ ማድረግ፡፡
- ሁል ጊዜ ትምህርቱን አስተምረዉ ስጨርሱ ተማሪዎች በደንብ እንድረዱ ዋና ዋና ነጥቦችን እንደገና በመድገም እንድያስተዉሱ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ የሚታቀርቡት ጥያቄዎችን፣ ተግባራትንና መልመጃ ለሰሩት በቂ የሆነ ግብረ-መልስ በጊዜ መስጠት፡፡
- ተማሪዎች የተለያዩ ጥያቄዎችን፣ ተግባራትንና ፕሮጀክቶችን በዚህ ርዕስ ስር ያሉትን ሁሉ በግል ወይም በቡድን እንድሰሩ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን የሰሩትን ስራ በቅርበት መቆጣጠርና ገንብ ሃሳብ መስጠት፡፡
- ለቤት ስራና ለክፍል ስራ ጊዜዉን የጠበቀ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡ የዘጋጃቹትን ጥያቄ መመለስ ያልቻሉትን ተማሪዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ተጨማሪ የትምህርት ጊዜ ወይም ልዩ እገዛ በመስጠት መርዳት፡፡
- ተማሪዎች ለጥያቄ የሰጡትን መልስ መፈተሽ፡፡
- ተማሪዎች ስያቀርቡ መመልከት፡፡
- ተማሪዎች ያቀረቡትንና አፈፃፀማቸዉን መመዝገብ፡፡

**የመልመጃ 2.3 መልስ**

1. በሜትር
2. ሀ. ርዝመትና አግድምክፍል ላይ ይወሰናል

   ለ. ርዘመትና ሰያፍ ክፍል ላይ ይወሰናል

   ሐ. ርዝመትና ከፍታ ጥቁር ሳሌዳ ላይ ይወሰናል

መምህር/ት! ተማሪዎች 2 ጥያቄ ስሰሩ አግዙ፡፡

**የመልመጃ 2.4 መልስ**

1. ሀ. በትክክል ቦታ ላይ የተቀመጠ ላይ ማስቀመጥ፡፡ለምሳሌ ሚዘን ላይ ማስቀመጥ፡፡

   ለ. የሚዘን ሰሃኖች ሚዛኑን ጠብቀዉ መቀመጣቸዉን ማረጋገጥ፡፡

   ሐ. የሚለካዉን ነገር መጠኑን ማወቅ፡፡

   መ. በአንዱ ሰሃን ላይ ከምለካ ነገር ጋር እኩል የሆነዉን ግራም ወይም ኪሎግራም ማስቀመጥ፤ በሁለተኛዉ ሰሃን ደገሞ ነገሩን መለካት፡፡ ይህም የምፈለገዉ መጠን እሰክደርስ ድረስ ቀስ በቀስ መጨመረና መለካት፡፡
2. የዚህ መፃሕፍ ክብደትና ተማርዉ የመለካት ችሎታ ይወሰናል፡፡
3. እንደ አከባቢያቸዉ ይወሰናል፡፡ ለምሳሌ ጣሳ፣ ሲኒ፣ ኩባያ፣ ቁና፣ ሚዛንና የመሳሰሉት መልስ መሆን ይችላሉ፡፡
4. የተወሰነ የቦርሳቸዉን ክብደት

**የተግባረ 2.6 መልስ**

1. ሀ.ሴኮንድ

   ለ. ደቂቃ

   ሐ. ሜትር ወይም ኪሎሜትር
2. የሴኮንድ ቆጣር ቀጭንና ረጅም (**ሀ**)፣ የደቂቃ ከሴኮንድ ትንሽ ወፈር ያለ (**ለ**)ና የሰዓት ቆጠር አጭርና ወፍራም(**ሐ**)ነዉ፡፡

**መልመጃ 2.5 መልስ**

በጠርሙሱ ይዜት ላይ ይወሰናል፡፡ ለምሳሌ፡ ባለግማሽ ሊትር፣ ባለአንድ ሊትር፣ ባለአንድ ከግማሽ ሊትር፣ ባለሁለት ሊትርና የመሳሰሉትን መሆን ይችላሉ፡፡

ተማሪዎች ለራሳቸዉ ባለግማሽ ሊትር፣ ባለአንድ ሊትር፣ ባለአንድ ከግማሽ ሊትር የሚያዘጋጁ ከሆነ መጀመሪያ ባለግማሽ ሊትር፣ በአንድ ሊትር ጠርሙስ ዉስጥ ዉሃ ይሙሉ፡፡ በመቀጠል ከሁለቱ ጠርሙስ ዉሃዉን ወደ ሶስተኛዉ ጠርሙስ ይገልብጡ፡፡ በመጨረሻም ባለግማሽ ሊትርና ባለአንድ ሊትር ከባለአንድ ከግማሽ ሊትር ጋር እኩል መሆኑን ይገንዘቡ፡፡

**ተግባር 2.7**

ሁኔታ ላይ በመወሰን እኩል ወይም ልበላለጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡ ጤንነታቸዉ፣ አለባበሳቸዉ፣ የአከባቢ አየርና የመሳሰሉት ሆኔት ላይ ይወሰናል፡፡

**የመልመጃ 2.6 መለስ**

1. ልኬት አንድ መጠኑ ያልታወቀዉን ነገር መጠኑ ቀደም ሲል ከታወቀዉ ነገር ጋር ጎን ለጎን አድርገን ማመዛዘን ነዉ፡፡
2. የተለያዩ መልስ ልኖረዉ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡ እንጨት፣ ብትር፣ ጠረጴዛ፣ ጋብ፣ መጫኛና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
3. የተለያዩ አሃዶች ትክክለኛ ልኬት አይሰጡም፣ ለግምት ይጠቅማሉ፡፡ አሳማኝ አይደሉም፡፡ ሳይንሳዊ አሃዶች ግን ትክክለኛ ልኬት ይሰጣሉ፣ አሰማኝም ናቸዉ፡፡
4. በቀጥታ ልለኩ የሚችሉ ናቸዉ፡፡ በሌላ ተሰፋር ፊዚካላዊ አካላት መገለፅ አይችሉም፡፡
5. 1ቀን = 24 ሰዓት ነዉ፡፡

   1 ሰዓት= 60 ደቂቃ ነዉ፡፡

   1 ደቂቃ= 60 ሴኮንድ ነዉ፡፡

ስለዚህ በአነድ ቀን ዉስጥ ደቂቃ ለመስላት መጀመሪያ 24 ሰዓትን ወደ ደቂቃ መቀየር ነዉ፡፡

1 ሰዓት = 60 ደቂቃ

24 ሰዓት = ስንት ይሆናል?

24 ሰዓት x 60 ደቂቃ/1ሰዓት = 1440 ደቂቃ ይሆናል

ስለዚህ አንድ ቀን 1440 ደቂቃ ይሆናል

አሁን ደግሞ 24 ሰዓት ወደ ሴኮንድ መቀየር አለብን

1 ደቂቃ = 60 ሴኮንድ

1440 ደቂቃ = ስንት ይሆናል?

1440 ደቂቃ x 60 ሴኮንድ/1ደቂቃ

= ሴኮንድ 86400 ነዉ፡፡

ስለዚህ አንድ ቀን ሴኮንድ 86400 ነዉ፡፡

## 2.4 የጉልበትምንጮች

***ለዚህ ርዕስ የተሰጠ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ብዛት --------------------9***

የርዕሱ የመማር ዉጤት

በዚህ ትምህርት ሂደት እና በርዕሱ መጨረሻ ተማሪዎች፡

- የጉልበት ምንጭና አስፈላጊነት ለማንኛዉም እንቅስቃሴ፣ ወይም ለማንኛዉም ለዉጥ የሚያግዙ፣ ለምሳሌ፣ ምግብ፣ ነዳጅ፣ የፀሐይ ብርሃን እና የመሳሰሉትን የብራራሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ርዕስ ስር ጉልበት አንድን ስራ የመስራት ብቃት መሆኑን አንድ አካል ስራ መስራት ከቻለ ደግሞ ጉልበት እንዳለዉ ተማሪዎች መማር አለባቸዉ፡፡ የአንድ አካል ጉልበት አካሉ መስራት በምችለዉ በስራ መጠን ይለካል፡፡ እንድሁም ጉልበት የተለያዩ ምንጮች እንዳለዉ፣ ከተለያዩ የጉልበት ምንጮች የተለያዩ የጉልበት ጥቅሞች እንደምገኝ ተማሪዎች መማር አለባቸዉ፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር በአጠቀላይ ዘጠኝ ክፌለ ጊዜ ተሰቷል፡፡ በዚህ በተሰጠ የትምህርት ክፌለጊዜ ዉስጥ ተማሪዎች መጎናጸፍ ያለባቸዉን እንድያገኙ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችንና የትምህርት መርጃ መሳራዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር የሚዉሉ የመማር ማስተማር ዉስጥ የቡድን ዉይይት፣ የሙሉ ክፍል ዉይይት፣ ገለፃና ሌሎች ለትምህርቱ ይዜት አመች የሆኑትንና የመሳሰሉትን ተጠቀሙ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

መምህር/ት ይህን ርዕስ ማስተማር ከመጀመርህ/ሽ በፊት የሚያስፈልገዉን ዚግጅት ማጠናቀቅ ይጠበቅብሃል/ሻል፡፡ ቅድማ ዝገግጅት ከሚያስፈልገዉ አንዱ ጥልቀት ያለዉ የትምህርት እቅድን ማዘጋጄት ነዉ፡፡ ለዘጠኙ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ዕቅድ ማዘጋጀት፡፡ እየንዳንዱ የትምህርት ዕቅድ ስታዘጋጅ ከርዕሱ ጋር የሚገናኙ በተማሪ መፅሐፍና በመምህሩ መምሪያ ዉስጥ የተገለፁትን ተግባራትና መልመጃዎችን መገንዘብ አለቦት፡፡ ከርዕሱ ጋር የሚያያዙትን ድርግቶች፣ መልመጃዎች ቀድሞ መዘጋጀትና መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በተጨማሪም፡

- የዚህ ትምህርት ይዜት ለማስተማር ቅድምያ ስለጉልበት፣ የተለያዩ የጉልበት ምንጮችና የጉልበት ዓይነቶች ላይ በቂ ግንዛቤ እንድኖርህ/ሽ ለሁለተኛና ለከፍተኛ ደረጃ የተዘጋጁትን የፊዚክስ ዋቢ መፅሐፍት በማንበብ መዘጋጀት፡፡
- ይህን የትምህርት ይዜት ለማስተማር የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ከትምህርት መአከልና በአከባቢ የሚገኙ እቃዎችን መጠቀም ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡ ንፋስ የእንቅስቃሴ ጉልበት ሆኖ እነዴት መዘዋሪን እንደምያስሽከረክር፡፡
- ሥዕሎችን፣ ፎቶ፣ የተለያዩ የጉልበት ምንጭ የሚያሳዩ ሞዴሎች ካሉ ተጠቀሙ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

የጉልበት ምንነት ከገለፃችሁበኋላ ፤ ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ የጉልበት ምንጮችን ዘርዝረዉ አንድወያዩበት ማድረግ፡፡ አነደዛዉም በጉልበት ምንጮች ላይ አወያዩ፡፡ ተማሪዎች ስለ ጉልበት ግንዛቤ በመፅሐፋቸዉ ላይ የተጠቀሰዉን ከኑሮ ዘይባቸዉ ጋር በማያያዝ በቡድን ወይም በግል እንድያሰላስሉ እድል ሰጧቸዉ፡፡ በመጨረሻም ሃሳባቸዉን ማዳበር፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንድያዳብሩ መርዳት

የዚህ የትምህርት ይዜት ችግር ፈች በሆነ ፈጠራን በምያበረታታ መልክ በማቅረብ ተማሪዎች ከፍተኛ የመሳተፍ እድል እንድኖራቸዉ በማድረግ ልዩ ተስጦ ያላቸዉ ተማሪዎች በራሳቸዉ ጥረት የተለያዩ የጉልበት ምንጭ ግኝት እንድያካሂዱ ማበረታታት፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

በምማሩት የትምህርቱ ዓላማ ላይ በመመስረት አንዳንድ ጥያቄዎች በማንሳት ጠይቁ፡፡

ለምሳሌ፡

- የጉልበት ምንጭ ዘርዝር፡፡
- የገልበት ዓይነቶችን ዘርዝር፡፡
- የጉልበት ምንጮችን እንድገልጹ መድረግ፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ስር ያካሄዱት ዉይይት ላይ ትኩረት በማድረግ ምንያህል እንደተረዱ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋግጥ፡፡

**የመልመጃ 2.7 መልስ**

1. ፀሐይ፣ ምግብ፣ ነዳጅ፣ ንፋስ
2. ለተለያዩ የብርሃን ይዉላል፡፡

   ለተለያዩ ለኤሌትርክ ዕቃዎች ይዉላል፡፡

   ለተለያዩ ፋብርካ ይዉላል፡፡

## 2.5 ድምፅ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠ የትምህርት ክፍለጊዜ ብዛት --------------------9

የርዕሱ የመማር ዉጤት

በዚህ የትምህርት ሂደት እና በሪዕሱ መጨረሻ ተማሪዎች፡

- የድምፅን ፍቺ በመስጠት በተለያዩ ነገሮች ዉስጥ መተላለፉን ያብራራሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ርዕሱ ስለድምፅ ምንነት፣ የድምፅ ዓይነቶችንና በተለያዩ ነገሮች ዉስጥ የሚደረገዉን የድምፅ መተላለፍ ሁሉ ተማሪዎች መማር አለባቸዉ፡፡ ድምፅ የጉልበት ዓይነቶች ሆኖ በነገሮች እርግብግብት የሚፈጠር ነዉ፡፡ ድምጽ በመስማትበስሜት የሚናረጋግጥ ፊዚካላዊ ክስተት ነዉ፡፡ ድምፅ ከድምፅ ምንጭ ወደ ሌላ ለመተላለፍ አስተላላፊ አካላትን እንደምያስፈልግ በጥልቀት ለተማሪዎች መነገር አለበት፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር ዘጠኝ ክፍለ ጊዜ ተሰጧል፡፡ በዚህ በተሰጠ የትምህርት ክፈለጊዜ ዉስጥ ተማሪዎች መጎናጸፍ ያለባቸዉን እንድያገኙ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችንና የትምህርት መርጃ መሳራዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር የሚዉሉ የመማር ማስተማር ዉስጥ የቡድን ዉይይት፣ የሙሉ ክፍል ዉይይት፣ ገለፃና ሌሎች ለትምህርቱ ይዜት አመች የሆኑትንና የመሳሰሉትን ተጠቀሙ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

መምህር/ት ይህን ርዕስ ማስተማር ከመጀመርህ/ሽ በፊት የሚያስፈልገዉን ዚግጅት መጠናቀቅ ይጠበቅብሃል/ሻል፡፡ ቅድሚ ዝገግጅት ከሚያስፈልገዉ አንዱ ጥልቀት ያለዉ የትምህርት እቅድን ማዘጋጀት ነዉ፡፡ ለዘጠኙ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ዕቅድ ማዘጋጀት፡፡ እየንዳንዱ የትምህርት ዕቅድ ስታዘጋጅ ከርዕሱ ጋር የሚገናኙ በተማሪ መፅሐፍና በመምህሩ መምሪያ ዉስጥ የተገለፁትን ተግባራትና መልመጃዎችን መገንዘብ አለበት፡፡ ከርዕሱ ጋር የሚያይዙትን ድርግቶች፣ መልመጃዎች ቀድሞ መዘጋጀትና መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በተጨማሪም፡

- ስለድምፅ በቂ ግንዛቤ እንድኖርህ/ሽ ለሁለተኛና ለከፍተኛ ደረጃ የተዘጋጁትን የፊዚክስ ዋቢ መፅሐፍት በማንበብ መዘጋጀት፡፡
- የተለያዩ ድምፅ የሚያመነጩ የተለያዩ የሙዚቃ መሳራዎችን እንደ ትምህርት መርጃ መሳሪያ በመጠቀም የተለያዩ ድምፅ በማመንጨት እንዴት በተለያዩ አካላት ዉስጥ እንደምተላለፍ ትምህርቱ ተጨባጭ መድረግ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ተማሪዎችን ስለድምፅ አፈጣጠር በመጠየቅ ያላቸዉን ግንዛቤ ከለያቹ በኋላ ፣ ድምፅ የጉልበት ዓይነቶች ሆኖ በነገሮች እርግብግብት የሚፈጠር ነዉ፡፡ ድምጽ በመስማትበስሜት የሚናረጋግጥ ፊዚካላዊ ክስተት መሆኑን መንገር፡፡ እንድሁም ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ድምፅ በምያመነጩት ላይ እንድወያዩ አድርጉ፡፡ በመጨረሻም ዉይይታቸዉን የምያጠናክር ሃሳብ ስጡ፡፡ ስለድምፅ ዓይነቶች ተማሪዎች እንድገነዘቡ ከመስማት በላይ ወይም ከፊተኛ ጩሄትና ድምፅ እያለ የማይሰማ ልዩነቶቻቸዉ ላይ እንድወያዩ ሁኔታ አመቻችላቸዉ፡፡ ሃሰባቸዉን ከተቀበላቹ በኃላ ሁለት የድምፅ አይነቶች እንዳሉ፣ እነሱም፡ የሚሰማ (audible sound)ና የማይሰማ (inaudible sound) እንደሆኑ ለተማሪዎች መንገር፡፡ በነገሮች ዉስጥ ድምፅ እንዴት እነደምተላለፍ ለማስገንዘብ መምህር/ት ክፍል ዉስጥ ስያስተምሩ ድምፅ ጆሮያቸዉ ጋ እንዴት እንደምደርስ ጠይቁዋቸዉ፡፡ ከዚህ በኃለ ድምፅ ከድምፅ ምንጭ ወደ ሌላ ለመተላለፍ አስተላላፊ አካላትን እንደምያስፈልግ በጥልቀት ለተማሪዎችተናገሩ፡፡ ይህ አስተላላፊ አካላት ከሞሎክዩል የተገነባ ስሆን በነኝህ ከሞሎክዩል እርግብግብት ድምፅ በአካላት ዉስጥ በማለፍ ጆሮያችን ጋ ደርሶ እንደምሰማ ንገሯቸዉ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንድያዳብሩ መርዳት**

የዚህ የትምህርት ይዜት ችግር ፈች በሆነ ፈጠራን በምያበረታታ መልክ በማቅረብ ተማሪዎች ከፍተኛ የመሳተፍ እድል እንድኖራቸዉ በማድረግ ልዩ ተስጥኦ ያላቸዉ ተማሪዎች በራሳቸዉ ጥረት የተለያዩ የጉልበት ምንጭ ግኝት እንድያካሂዱ ማበረታታት፡፡

**ተከታታይ ሚዘና**

ተማሪዎች በዚህ በትምህርቱ ዋና ነጥቦች ስር የተጠቀሰዉንና የሚፈለገዉ ችሎታ መጎናፀፋቸዉን በርዕሱ ዓለማ ላይ በመመስረት አንዳንድ ጥያቄ መጠየቅና ግብረ መልስ መስጠት ይጠበቅቦታል፡፡

ለምሳሌ፡

- ድምፅ ምን እንደሆነ እንድገልጹ፡፡
- የድምፅዓይነቶችን እንድዘረዝሩ፡፡
- ድምፅ ምን ዉስጥ እንደምተላለፍ መጠየቅ፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ስር ያካሄዱት ዉይይት ላይ ትኩረት በማድረግ ምንያህል እንደተረዱ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋግጥ፡፡

## የመልመጃ 2.8 መልስ

1. ጠጣር፣ ፈሳሽና ጋስ በምርገበገቡበት ጊዜ ድምጽ ያመነጫሉ፡፡
2. የሚሰማ ድምጽና የማይሰማ ድምጽ ይባላሉ፡፡
   የሚሰማ ድምጽ ለጆሮ ስሜት የሚሰጥ ነዉ፡፡ የማይሰማ ድምጽ ለጆሮ ስሜት የማይሰጥ ነዉ፡፡
3. ድምጽ ለመተላለፍ የድምጽ አስተላላፊ የሆኑት ጠጣር ፣ ፈሳሽና ጋስ ያስፈልገዋል::
4. ድምጽ የመካንካል ሞገድ ዓይነት ስለሆነ፡፡

## የምዕራፍ 2 መልመጃ

**እዉነት/ሐሰት**

1. ሐሰት 3. እዉነት 5. ሐሰት 7. እዉነት 9. ሐሰት

2. ሐሰት 4. እዉነት 6. ሐሰት 8. ሐሰት

**አዛምድ**

1. ሐ 2. መ 3. ለ 4. ሀ 5. ሠ

**II. ምርጫ**

1. ለ 6. መ 11.ሐ 16.ሐ 21. ለ

2. ለ 7. መ 12.ለ 17.መ 22. ሐ

3. ሐ 8. መ 13.መ 18.ለ 23. ሀ

4. ለ 9. ሐ 14.ሀ 19. ለ

5. ለ 10. ሐ 15. ሐ 20. ሐ

**Iv. አጭር መልስ**

1. ፍቺ

ሀ) ልኬት አንድ መጠኑ ያልታወቀዉን ነገር መጠኑ ቀደም ሲል ከታወቀዉ ነገር ጋር ጎን

ለጎን አድርገን ማመዛዘን ነዉ፡፡

ለ) በቀጥታ ልለኩ የሚችሉ ናቸዉ፡፡ በሌላ ተሰፋር ፊዚካላዊ አካላት መገለፅ አይችሉም፡፡

ሐ) ጊዜ የአንድን ድርጊት መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለዉን ቆይታ ወይም ደግሞ

የአንድን ክስተት ቆይታን የሚገልጽ ነዉ፡፡

መ) መጠነ-ቁስ በአንድ አካል ዉስጥ የሚገኝ የቁስ አካል መጠን ማለት ነዉ፡፡

2. ጉልበት ሥራ የመስራት አቅም ነዉ፡፡

3. ፀሐይ፣ ምግብ፣ ነዳጅ፣ ንፋስ

4. የጉልበት ዓይነት

   ሀ. የሶላር ጉልበት

   ለ. የኒኩለር ጉልበት

   ሐ. የመካኒካል ጉልበት

   መ. የኬሚካል ጉልበት

5. የጉልበት ጥቅም

   - ለተለያዩ የብርሃን ጉለበት ይዉላል፡፡
   - ለተለያዩ ለኤሌትርክ ዕቃዎች ይዉላል፡፡
   - ለተለያዩ ፋብርካ ይዉላል፡፡.

6. የሚሰማ ድምጽና የማይሰማ ድምጽ
7. ቫክዩም
8. ጠጣር፣ ፈሳሽ፣ ጋስ
9. ሎሚን ኢሙልስፋይ ማድረግ

# ምዕራፍ- 3 የኢትዮጵያየተፈጥሮሀብት

**ለምዕራፉ የተሰጠ የትምህርት ክፍለጊዜ ብዛት----------------------------54**

**የምዕራፉ የመማር ዉጤቶች**

**በምዕራፉ ትምህርት መጨረሻ ላይ፡-**

- በአየር ሁኔታ እና አየር ንብረት መካከል ያለዉን ልዩነት ይናገራሉ፡፡
- የአየር ንብረት ይዜቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- የኢትዮጵያን አየር ንብረት የሚወስኑ ዋና ዋና ነገሮችን ትለያለህ/ሽ፡፡
- የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች ይለያሉ፡፡
- የኢትዮጵያን የአፈር ዓይነቶች እና የአፈር ዕጥበትን ይለያሉ፡፡
- የኢትዮጵያን የዕፅዋት ዓይነቶችን ይለያሉ፡፡
- በኢትዮጵያ ዉስጥ የደን ሀብትን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ይናገራሉ፡፡
- የደን ሀብት ጭፍጨፋን እንዴት ማስቆም እንደሚቻል ይለያሉ፡፡
- የኢትዮጵያን የዉሃ ሀብት የሚጎዱ ዋና ዋና ምክንያቶች ይዘርዝራሉ፡፡
- የኢትዮጵያን የሐይቅ ዓይነቶች እና ባህሪያቸዉን ይለያሉ፡፡
- የኢትዮጵያን የወንዞች ሥርዓት-ፍሰት እና ሐይቆች ሁኔታን በማጥናት ይለያሉ፡፡
- በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ የማዕድናት አጠቃቀም ሁኔታ እና በአጠቀቀም ህደት ዉስጥ በአከባቢ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን ተፅዕኖ በጥልቀት ያጠናሉ፡፡
- የኢትዮጵያን የዱር እንስሳት ሊጎዱ የሚችሉ ዋና ዋና ምክንያቶችን ይገለፃሉ፡፡
- በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና የሃይል ምንጮችን ይዘረዝራሉ፡፡

- የሚታደሱ እና የማይታደሱ የሃይል ምንጮችን ይለያሉ፡፡
- በኢትዮጵያ እና በአከባቢዋ ስጋት የሆኑ ዋና ዋና ችግሮችን ይዘረዝራሉ፡፡
- በኢትዮጵያ ዉስጥ ዋና ዋና የአከባቢ ብክለት ምክንያቶች እና በተሰጠዉ መፍትሄ ላይ ይወያያሉ፡፡

## 3.1 የኢትዮጵያየአየርንብረት

ለዚህ ርዕስ የተሰጠ የትምህርት ክፍለጊዜ ብዛት --------------------10

የርዕሱ የመማር ዉጤት

በዚህ አካሄድና በርዕሱ መጨረሻ ተማሪዎች፡

- የአየር ሁኔታ እና አየር ንብረት ምንነትን በመለየት ይገልፃሉ፡፡
- በአየር ሁኔታ እና አየር ንብረት መካከል ያለዉን ልዩነት ይናገራሉ፡፡
- የአየር ሁኔታን ምሳሌ ይሰጣሉ፡፡
- የኢትዮጵያን የአየር ንብረት የሚወስኑ ዋና ዋና ነገሮችን ይለያሉ፡፡
- የአየር ንብረት ይዜቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- የአየር ንብረት የሚያደርሰዉን ተፅዕኖ ይገልፃሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ርዕሱ ስር ስለአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ምንነትን፣ በአየር ሁኔታ እና አየር ንብረት መካከል ያለዉን ልዩነት ተማሪዎች መማር አለባቸዉ፡፡ የኢትዮጵያን የአየር ንብረት የሚወስኑ ዋና ዋና ነገሮችን፣ የአየር ንብረት ይዜቶችን ና የአየር ንብረት በኑሮያቸዉ ላይ የሚያደርሰዉን ተፅዕኖ በጥልቀት ለተማሪዎች መነገር አለበት፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር አስር ክፍለ ጊዜ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ በተሰጠ የትምህርት ክፈለጊዜ ዉስጥ ተማሪዎች መጎናጸፍ ያለባቸዉን እንድያገኙ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችንና የትምህርት መርጃ መሳራዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር የሚዉሉ የመማር ማስተማር ዉስጥ የቡድን ዉይይት፣ የሙሉ ክፍል ዉይይት፣ ገለፃና ሌሎች ለትምህርቱ ይዜት አመች የሆኑትንና የመሳሰሉትን ተጠቀሙ፡፡

በዚህ ርዕስ ስር ያለዉን ትምህርት ለማስተማር ስለአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ምንነትን፣ በአየር ሁኔታ እና አየር ንብረት መካከል ያለዉን ልዩነት፣ የኢትዮጵያን የአየር ንብረት የሚወስኑ ዋና ዋና ነገሮችን፣ የአየር ንብረት ይዜቶችን ና የአየር

ንብረት በወረዳቹና በዞናቹ ያለዉን በ3ኛና በ4ኛ ክፍል ከተማሩት ጋር ማያያዝ እንድችሉ ማድረግ ከመምህሩ ይጠበቃል፡፡

የአየር ሁኔታ ማለት በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚቀያየር የአየር ጠባይ ማለት ነዉ፡፡ የአየር ንብረትማለት የአንድ ቦታ የአየር ጠባይ በአማካይ የአየር ንብረት ይዘቶች ሳይቀያየሩ በተመሳሳይ ሁኔታ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ነዉ፡፡የአየር ንብረት እና የአየር ሁኔታ ያላቸዉ ግንኙነት ተመሳሳይ የአየር ንብረት ይዜት የያዙ ስሆን ልዩነታቸዉ ደግሞ ያላቸዉ የጊዜ ርዝማኔ መሆኑን ተማሪዎች እንድረዱ ማድረግ ነዉ፡፡ በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች ያገኙት ዕዉቀት ወደ ፊት መሰረት ሆኖ እንደምያገለግል መገንዘብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

*መምህር/ት ይህን ርዕስ ማስተማር ከመጀመርህ/ሽ በፊት የሚያስፈልገዉን ዚግጅት መጠናቀቅ ይጠበቅብሃል/ሻል፡፡ ቅድማ ዝገግጅት ከሚያስፈልገዉ አንዱ ጥልቀት የለዉ የትምህርት እቅድን ማዘጋጄት ነዉ፡፡ ለአስሩም የትምህርት ክፍለ ጊዜ ዕቅድ ማዘጋጀት አለባቸዉ፡፡ እየንዳንዱ የትምህርት ዕቅድ ስታዘጋጁ ከርዕሱ ጋር የሚገናኙ በተማሪ መፅሐፍና በመምህሩ መምሪያ ዉስጥ የተገለፁትን ተግባራትና መልመጃዎችን በደንብ መገንዘብ አለቦት፡፡ ከርዕሱ ጋር የሚያያዙትን ድርግቶች፣ መልመጃዎች ቀድሞ መዘጋጀትና መገዘብ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በተጨማሪም፡ ስለአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ምንነትን፣ በአየር ሁኔታ እና አየር ንብረት መካከል ያለዉን ልዩነት፣ የኢትዮጵያን የአየር ንብረት የሚወስኑ ዋና ዋና ነገሮችን፣ የአየር ንብረት ይዜቶችን ና የአየር ንብረት በቂ ግነዛቤ እንድኖራቹ ለከፍተኛ ትምህርት የተዘጋጁ የጂኦግራፊ መጻሐፍትና በኢትዮጵያ የተዘጋጁ የጂኦግራፊ የዋቢ መጻሐፍትን አነብቡ፡፡*

*መምህር/ት ይህን ርዕስ ለማስተማርና ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ የኢትዮጵያ የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት የሚያሳይ ካርታ እንደ ትምህርት መርጃ መሳሪያ በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡*

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

*ይህንን ረዕስ ለማስተማር በመጀመሪያ አየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ጠይቁ፡፡ እንድሁም በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት መካከል ባለዉ ልዩነት ላይ ተወያይተዉ ለክፍሉ እንድያቀርቡ አድረጓቸዉ፡፡ በተጠናቀረዉ ላይም ሌሎች ተማሪዎች ሀሳብ እነድሰጡበት ከአደረገችሁ በኋላ ተጨማሪ መብራሪያ ስጡአቸዉ፡፡*

በመቀጠልም የክፍሉ ተማሪዎችም ስለ አየር ንብረት ይዜት፤ የአየር ንብረት ዞን እንድሁም የአየር ንብረትን በሚወስኑ ነገሮች ላይ እንድወያዩ አድርጓቸዉ፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ የተማሪዎችን ግንዛቤ ከለዩ በኋላ በስተመጨረሻ ላይ ትክክለኛዉን አቅጣጫ ለማስያዝ ተጨማሪ ገለፃ ይስጡአቸዉ፡

የዚህን ሪዕስ ዋና ዋና የኢትዮጵያ አየር ንብረት ተማሪዎች እንድገነዘቡ ለጥቂት ደቂቃ የሚኖሩበትን ወረደ እና ቀበሌ የአየር ሁኔታ እንድያስቡ እድል ስጡአቸዉ፡፡ በመቀጠልም ትክክለኛ አቅጣጫ ለማስያዝ የሀገራችን የአየር ንብት ዞን በአለም ዉስጥ በሞቃታማ አየር/ትሮፒካል/ በምድር ወገብ አከባቢ በሚገኘዉ እንደሚትገኝ እና ዓይነቶቹንም በመንገር በጥልቀት ገለፃ አድረጉላቸዉ፡፡

## ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንድያዳብሩ መርዳት

የዚህ ትምህርት ይዘቶች ችግርን በመቅረፍ መልኩ ፈጠራን ማበረታታት በሚችሉት አከኳን ተማሪዎች ከፍተኛ ተሳትፎ የማግኘት እድል እንድያገኙ በማድረግ የተለያዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ ያላቸዉ ተማሪዎች በራሳቸዉ ተነሳሽነት የዐየር ንብርት እና የአየር ንብረት ይዜቶችን በአከባቢያቸዉ ላይ ምርምር እና ጥናት እንድያካሂዱ እና በራሳቸዉ ፈጠራ እድያከናዉኑ ማበረታታት፡፡

## ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች በይዘቶቹ ስር ባሉት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ የሚፈለገዉን ብቃት መጎናፀፋቸዉን በተሰጠዉ ርዕስ ዓላማ ላይ በመመስረት አንድ አንድ ጥያቀዎችን በክፍል ዉስጥ በመጠየቅ እና ግብረ መልስ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

ለምሳሌ:

- የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብርትን በመለየት እንድገልፁ
- የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብርት መካከል ያለዉን ልዩነት እንድናገሩ
- የኢትዮጵያን የአየር ንብርት የሚወስኑ ነገሮችን እንድዘረዝሩ በመጠየቅ
- የአየር ንብርት ይዜቶችን እንድዘረዝሩ በማድረግ
- የአየር ንብርት አይነቶችን እንድዘረዝሩ በመጠየቅ
- የአየር ንብርት በኑሮአቸዉ ላይ ያለዉን ተፅዕኖ እንድገልፁ በማደርግ

በተጨማሪም በዚህ ርዕስ ሥር ባሉት የተማሪዎች ዉይይት እና ተግባራት ላይ ትኩረት በመስጠት ተማሪዎች ምን ያህል ትምህርቱን እንደተገነዘቡ የተለያዩ ጥያቄዎች በመጠየቅ አረጋግጡ፡፡

## 3.2. የኢትዮጵያየተፈጥሮሃብቶች

**ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠዉ ክፍለ ጊዜ ....................................................44**

**የዚህ ምዕራፍ የመማር ዉጤት**

**የዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡-**

- የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችን ይለያሉ
- የኢትዮጵያ የአፈር ዓይነቶች እና የአፈር መሸርሸርን ይገልፃሉ
- የኢትዮጵያ የእፅዋት ዓይነቶችን ይገልፃሉ
- በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙትን የደን ሃብት እንክብካቤ ይናገራሉ
- የደን መጨፍጨፍ የሚቆምበትን ሁኔታ ይለያሉ
- የኢትዮጵያን የዉሃ ሀብት የሚጎዱ ምክንያቶች ይዘረዝራሉ
- የኢትዮጵያን የባህር ዓይነቶች እና ባህሪያቸዉን ይለያሉ
- የኢትዮጵያን የወንዞች ሥርዓተ-ፍሰት እና ሐይቆች ሁኔታን በማጥናት ይለያሉ
- በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ የማዕድናት አጠቃቀም ሁኔታ እና በአጠቃቀም ህደት ዉስጥ በአከባቢ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን ተፅዕኖ በጥልቀት ያጠናሉ
- የኢትዮጵያን የዱር እንስሳት ሊጎዱ የሚችሉ ዋና ዋና ምክንያቶችን ይገልፃሉ
- በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና የሃይል ምንጮችን ይዘረዝራሉ
- የሚታደሱ እና የማይታደሱ የሃይል ምንጮችን ይለያሉ
- በኢትዮጵያ እና በአከባቢዋ ስጋት የሆኑ ዋና ዋና ችግሮችን ይዘረዝራሉ
- በኢትዮጵያ ዉስጥ ዋና ዋና የአከባቢ ብክለት ምክንያቶች እና በተሰጠዉ መፍትሄ ላይ ይወያያሉ፡

በተጨማሪም የእፀዋት ዶክመንተሪ ቪድዮ በመትከል እና በማንከባከብ ላይ የተሠራ ካለ፡ ወደ መማሪያ ክፍል በመምጣት፡ እፀዋትን የመትከል ጠቀሜታን እና እፅዋት የመጨፍጨፍ ጉዳት ላይ ግንዛቤ ከሰጡአቸዉ ቦኋላ ተማሪዎች በፍቃዳቸዉ በአከባቢ እንክብካቤ ላይ እፅዋትን በመትከል እና በማንከባከብ ዉስጥ እንድሳተፉ አበረታቱአቸዉ፡፡

የኢትዮድያ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ጥያቄ እና መልስ ለተማሮዎች በማድረግ፡ የግል አመለካከተ አቅጣጫ በማስያዝ እና በመገምገም፣ የዉሃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀምን እንድለዩ አግዙአቸዉ፡፡ በመጨረሻ ላይ ቀጥተኛ አቅጣጫን በማስያዝ ተጨማሪ ማብራሪያ ስለ ተፈጥሮ ሀብት እንከብካቤ ማለትም የተፈጥሮ ሀብትን በአከባቢ መጠቀም መቻል እንደሆነ ግለፁላቸዉ፡፡ ተማሪዎች ዋና ዋና ነጥቦች በተፈጥሮ ዉሃን

የሚጎዱ ሃሳባቸውን እንድገልፁ መጠየቅ ነዉ፡፡ እንደዚሁም ትክክለኛዉን አቅጣጫ ተማሪዎች እንድይዙ በማድረግ ተጨማሪ ሀሳብ ወይም ላላቸዉ ነገሮች ሁሉ በጣም ወሳኝ እንደሆነ የአከባቢያችንን ዉሃ ማንከባከብ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ፡ ዉሃን የማንከባከብ ዘዴዎችን በመዘርዘር ይግለፁላቸዉ፡፡

ተማሪዎችን በቡድን በመክፍል የባህሮችን እና የፈሳሽ ዉሃን ባህሪያት፣ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙትን እንደዘረዝሩ አድርጓቸዉ በመጨረሻ ተማሪዎች ትክክለኛዉን ሀሳብ በማስያዝ የባህሮች ባህሪያት በተለያየ ቦታ መገኘታቸዉ፤ ሁኔታቸዉ፡፡ (ስፋት ወይ ጥበት፤ጥልቀት እና ከላይ ያለ ጥልቀት መገኘት) የጨውነት ባህሪ ወዘተ የተለያዩ እንደሆኑ ይግለፁላቸዉ፡፡

- በአከባቢያቸዉ ያሉትን የተለያዩ የወንዞች አይነት ዋና ዋናዎቹን እንድዘረዝሩ የፍስት ባህሪያቸዉን እና በሚፈሱበትን አቅጣጫ ላይ እንድወያዩ አድርጉ፡፡ በመቀጠልም በኢትዮጵያ ወንዞች በአፈሳስ ሥርአት ላይ ተመርኩዘዉ ሦስት ዋና ዋና የምፈሱበት አቅጣጫ እንዳላቸዉ ይግለፁላቻዉ፡፡

የክፍል ተማሪዎችን በተለያየ ቡድን በመክፍል በአከባቢቸዉ ዉስጥ እንደሚገኙትን ሁሉ እንድዘረዝሩ እንድሁም ሥራ ላይ የማዋል ሁኔታን እና እነዚህ ሀብቶች በአግባቡ አላመጠቀም በአከባቢያቸዉ ላይ የሚያደረሰዉን ጉዳት በጥልቀት አንድወያዩበት ሁኔታ ያመቻቹላቸዉ፡፡

በመጨረሻ ትክክለኛዉ ሐሳብ በማስያዝ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ማዕድናት ላይ የጅኦሎጂ ጥናት እንደሚያመለክተዉ ሀገራችን ኢትዮጵያ በማዕድናት ሀብት የበለፀገች መሆኑን ለተማሪዎች መግለጫ ማድረግ ነዉ፡፡

የዱሮ እንስሳትን በአከባቢያቸዉ የሚገኙትን እንደዚሁም በአከባቢያቸዉ በሚገኘዉ ደን ዉስጥ የሚገኙትን የዱር እንስሳት እንዲጠቅሱ ዕድል መስጠት፡፡ በመቀጠልም እነርሱ ከዘረዘሩት የዱር እንስሳት ውስጥ በኢትዮጵያ ዉስጥ ብቻ የሚገኙትን የዱር እንስሳት በመለየት በፎቶ በመታገዝ፤ ብዛታቸዉን እና በሀገርቷ ዉስጥ የት ቦታ እንደሚገኙ በአግባቡ ገለፃ ማድረግ፡፡ በመጨረሻም በኢትዮጵያ ብርቅዬ የዱር እንስሳት ለአደጋ የምያጋልጡትን በመዘርዘር ያሳዩአቸዉ፡፡

በኢትዮጵያ የጉልበት ምንጭ አይነቶችን ተማሪዎች እንድዘረዝሩ አድርጉአቸዉ፡፡ በመቀጠልም የጉልበት ምንጭ ባህሪያትን በኢትዮጵያ ዉስጥ የምታደሱ እና

የማይታደሱ በማለትተማሪዎች እንድመደቡአቸዉ እና እንድወያዩባቸዉ አድርጉቸቸዉ፡፡

በመጨረሻ ትክክለኛ ሀሳብ በማስያዝ ተጨማሪ ሀሳብ ስጡአቸዉ፡፡

ኢትዮጵያን ችግር ዉስጥ የከተቱት ዋና ዋና ችግሮች ተማሪዎች እንድወያዩበት ሁኔታን ማመቻቸት፡፡

በመቀጠልም የተፈጥሮ ሀብትን ማንከባከብ እና ሥራ ላይ ማዋልን በተመለከተ በኢትዮጵያ ዉስጥ ዋና ዋና ችግር የሆነዉን ጥልቀት ባለዉ መልኩ ይሰጣቸዉ፡፡

ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንድያሳድጉ ማገዝ ይህ የትምህርተ ይዜት፡ ችግርን በመፍታት ፈጠራን ማበረታታት መቻል፤ ማቅረብ እና ተማሪዎች ከፍ ያል የመሳተፍ ዕድል እንድያገኙ ማድረግ ነዉ፡፡ የተለየ ሥጦታ እና የተሻለ ችሎታ ያላቸዉ ተማሪዎች በራሳቸዉ ተማሪዎች በራሳቸዉ ጥረት የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋልን፤የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ እና የኢትዮጵያን ስጋቶችን ጨምረዉ ጥናት እና ምርምር በማካሄድ በራሳቸዉ ፈጠራ ወፍትሔ እንድሰጡ አበረታቱአቸዉ፡፡

### ተከታታ ምዘና

ተማሪዎች በይዘቱ ሥር ለተጠቀሱ ዋና ዋና ነጥቦች የሚፈለገዉ ብቃት መገኘታቸዉን በተማሩት የትምህርት ርዕስ ላይ ተመርኩዘው እንዳንድ ጥያቄዎችን በማንሳት በክፍል ዉስጥ መጠየቅ እና ግብረ መልስ መስጠጥ ይጠበቃል፡፡
ለምሳሌ

- የተለያዩ በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቶችን እንድያሳዩ እና እንደገልፁ መጠየቅ
- የኢትዮጵያ የአፈር አይነቶችን እና የአፈር መሸርሸርን እንድገልፁ መጠየቅ
- የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ዕፅዋት አይነቶችን እንድለዩ መጠየቅ
- የኢትዮጵያ የዉሃ ሀብትን የሚጎዱ ዋና ዋና ምንክንቶችን እንድናገሩ መጠየቅ
- የኢትዮጵያ የሐይቅ አይነቶች እና ባህሪያቸዉን እንድናገሩ መጠየቅ
- የኢትዮጵያ ወንዞች ሥራአተ ፍሰት እና ባህሮችን በማጥናት እንደናገሩ መጠየቅ
- በአላማ ላይ ተመርኩዘዉ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ሁልጊዜ ጥያቄ መጠየቅ
- በተጨማሪም በእናዚህ ርዕሶች ሥር ዉይይት እና ተማሪዎች የሚያከናዉኑ ተግባራት ላይ በማተኮር ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንዳስተዋሉት የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋግጡ፡፡

**የምዕራፍ 3 መልመጃ መልሶች**

I, አውነት/ሐሳት

1. እዉነት 2. ሐሰት 3. ሐሰት 4. ሐሰት 5.ሐሰት 6. እዉነት 7. ሐሰት

II. ምርጫ

1. ለ 2.ለ 3.መ 4.መ 5.ሐ 6.መ 7.ሀ 8.ለ 9.ለ 10.መ 11.ሐ 12.መ 13.ሀ

III. አጭር መልስ

1. ዳዋ፣ጋናሌ፣ዋቤ ሸባሌ
2. የድንጋይ ከሰል፣ የነዳጅ ዘይት፣ የተፈጥሮ ጋዝ
3. ዉርጭ፣ ደጋ፣ ወይናደጋ፣ ቆላ እና በረሃ
4. - የሀገሪቷ የአየር ንብረት መቀየር
   - ሞቃታማ
   - ለእርሻ የሚዉል ለም አፈር መሸርሸር
   - የደኖች በእሳት መቃጠል እና የተፈጥሮ ሚዛንን መጠበቅ አለመቻል

# ምዕራፍ- 4 የኢትዮጵያማህበራዊአከባቢ

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት-------------------------------------------54

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**በዝህ ትምህርት እና ምዕራፍ መጨራሻ፡**

- የኢትዮጵያ የባህል ብዘሃነትን ያከብራሉ
- በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ ታዋቂ ባህሎችን ይለያሉ
- የኢትዮጵያ ትላልቅ የቋንቋ ቤተሰቦችን ይለያሉ
- የኢትዮጵያ ታዋቂ የባህል ቅሶችን በመለየት ይገልፃሉ
- በኢትዮጵያ የባህል ተቋማት ጥቅሞችን ይገለፃሉ
- ባህላዊ ቅርሶችን ለማንከባከብ የህብረተሰቡ ኋላ ፍነት እና ተጠያቂነት ይለያሉ
- የኢትዮጵያ ትላልቅ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ይለያሉ
- ኢትዮጵያ ወደ ዉጭ የሚትልካቸዉን የእርሻ ዉጤቶችን ይዘረዝራሉ
- የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ዉጤቶችን ይለያሉ
- በኢትዮጵያ የቱሪዚም እንቅስቃሴ ጥቅሞችን ይለያሉ
- በኢትዮጵያ ቱሪዚም እንዱስትሪ ላይ ተጽኖ የሚያሳድሩትን ይገልፃሉ፡፡

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ከምስራቅ አፍርካ ሀገሮች በህዝብ ብዛት የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ እንደዚሁም የባህል ብዘሃነት ባለቤት ሀገር መሆኗም ይታወቃል፡፡ከነዚህም ጎብረ ባህሎች ዉስጥ ጥቅቶቹ የአኗኗር ሁኔታ፤የአለባበስ ባህል፣ የአመልከ ስርዓት፣ ቋንቋ፣ የጋብቻ ስርዓት፣ ሐዘን እና ደስታ የሚካሄድባቸው ስርዓቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በዚህ ምዕራፍ ለላው ዋና ነጥብ ቅርሶች ያላቸዉን ጠቀሜታ ላይ ያተኩራል፡፡ ለታዋቂ ቅርሶች ተገቢ ጥበቃ እና እንክባከብ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም በዉስጡ ትላልቅ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን አቅፈው ስለምገኝ ነዉ፡፡

## 4.1 የኢትዮጵያህዝቦችየባህልብዝሃነት

### 4.1.1 የኢትዮጵያ ታዋቂ ባህሎች

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት----------------------------------------- 2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገቡ ብቃት

- የኢትዮጵያ ህዝቦች ኅብረ ባህል ያደንቃሉ
- በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ ታዋቂ ባህሎችን ይለያሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

መምህራን ተማሪዎችን ካላቸዉ ልምድ በመነሳት ባህል ማለት ምን እንደሆነ እንዲናገሩ በጥያቄ እና መልስ ዘዴ ተጠቅመው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎችን መልሳቸውን ከሰጡ በኋላ ባህል ማለት የሰዉ ልጅ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸው ግንኙኘነቶች፣ተግባቦት፣ ልምዶች እና አዳዲስ ነገሮችን ለማግኘት የሚያከናዉኑት ስራዎች ሁሉ ባህል እንደሆነ ማስጨበጥ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም በምሳሌ በመታገዝ ተጨማሪ የማጠናከሪያ ሓሳብ በማከል ትምህርቱን ማስጨበጥ ተገቢ ይሆናል፡፡

በመቀጠል ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ ያሉ ባህሎችን እዲዘረዝሩ ዕድል ይሰጣቸው፡፡ ተማሪዎች የሰጡትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ኢትዮጵያ የኀብረ-ባህል ባለቤት መሆኑዋን ማስጨበጥ ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም የኀብረ-ባህል ባለቤት የሆኑት የኢትዮጵያ ሕዝቦች እንዴት ተቻችለዉ እንደሚኖሩ በአከባቢ የሚጸባረቁትን እንደምሳሌ በመውሰድ የማጠቃለያ ገለጻ ይሰጣቸው፡፡ ለምሳሌ በአከባቢ የሚጸባረቁ የዘፈን ባህሎች፤የአለባበስ ባህሎች ፤የአመጋገብ የቋንቋ፤የአመልኮ ስርዓት እና የእንግዳ አቀባበል ባህሎች ላይ ተማሪዎችን ማወያየት ይቻላል፡፡

ባህል በአኗኗር ሁኔታ፣ቋንቋ እና በአየር ንብረትን ልዩነት ምክንያት ከቦታ ቦታ ይለያል፡፡ ለምሳሌ የኩሽ እና የሰም ግንድ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች መሀከል መጠነኛ የሆነ የባህል ልዩነቶች ይታያሉ ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ በሆኑት ሕዝቦች መሀከል መጠነኛ የሆነ የቋንቋ ትስስረ ይኖራል ፡፡ እንደዚሁም የሰም ግንድ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች መሀከልም መጠነኛ የሆነ የቋንቋ ትስስረ ይታያል፡፡ ስለዚህ ቋንቋ ከባህል ይዘቶች ውስጥ አንዱ ነዉ፡፡

በምስራቅ አፍሪካ ዉስጥ የተለያዩ ባህሎች አሉ፡፡ የጎረቤት ሀገሮች ባህሎችም ከኢትዮጵያ ኅብረ-ባህል ጋር ጠንካራ ቁርኝት አለዉ፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ሰሜን ህዝቦች ባህል ካአፍሮ ኢስቲክ ቋንቋ ተናጋሪዎች እንደ ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ህዝቦች፣ ፔንሱላ አረቢያን እና ኢንዲያ ጋር መጠነኛ ግንኙነት አለዉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባህል ፣ሥነ-ምግባር እና የታሪክ መፅሓፍት በማንበብ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ከመጀመራችሁ በፊት ተማሪዎች ለትምህርቱ የሚያደርጉትን ትኩረትእና ትምህርቱን በአግባቡ እንዲከታተሉ በማድረግ ያስፈልጋል ፡፡ ባህልን አስመልክቶ የሚያቁትን እንድናገሩ ጠይቋቸዉ፡፡ በአከባቢያቸዉ ያሉትን ባህሎችን እንዲዘረዝሩ እድል ስጣቸዉ፡፡በመምህራን በገለፃቸው ወቅክት ኢትዮጵያ የኅብረ-ባህል ባለቤት አገር እነደሆነች ማሰገነዘብ ያስፈላጋል ፡፡

## የመማር የማስተማር ዘዴ

ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ የሚገኙ ባህሎች ምንምን እነደሆኑ ጠይቋቸዉ ፡፡ ተማሪዎች በኢትዮጵያ ደረጃ እና በኦሮሚያ ክልል ታዋቂ የሆኑ ባህሎችን ቤተሰቦቻቸዉን ወይም አዋቅዎችን ጠይቀዉ በክፍል ሪፖር እንዲያቀርቡ የፕሮጀክት ሥራ ይሰጣቸዉ ፡፡ተማሪዎችን የቡድን በመክፍል የተለያዩ ባህሎችን በክፍላቸዉ ዉስጥ እርስ በርሳቸዉ እንዲነጋገሩ ማድረግ፡፡ በባህሎች መካከል የሚጸባረቁ ልዩነቶችን እንዲገልፁ አበረታታቸዉ፡፡ ልዩ ስጦታ እና የተሻለ ችሎታ ያለቸዉን ተማሪዎችን እና በአነስተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚቀበሉ ተማሪዎቸን ያማከል የመማር የማስተማር ዘዴ በመጠቀም ተማሪዎችን ማጠናከር፡፡ የተሻለ ችሎታ ያላቸዉ ተማሪዎችን ለብቻ ለይተን ሳናወጣ ከሁሉም ተማሪዎች ጋር በክፍል ውሰጥ እና ውጭ ዉይይት ፣ አብሮ እንዲያጤኑ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

- አጫጭር ጥያቄዎችን በማዘጋጀት
- ተማሪዎችን የተማሩትን ትምህርት ካልተረዱ ግብረመልስ በመስጠት
- የተማሪዎች ባህሪይ ለውጥ በተከታታይ መመዝገብ
- በቡድን እና በግል የሚሰሩትን በመከታተል መገመገም ናቸዉ፡፡

## 4.1.2 የኢትዮጵያ ባህል ይዘቶች

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት----------------------------------

1

**ዋና ዋና ነጥቦች**

የባህል ይዘቶች የተባሉት በህዝብ ዉስጥ የሚከናወኑ፣ ቋንቋ፣የአመልኮ ስረዓት፣ አለባበስ ፣ አብሮ የመኖር ሁኔታ እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡ በአጠቃላይ በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ተማሪዎች ካላቸው ልምድ በመነሳት የኢትዮጵያን የባህል ይዘቶችነ እንድረዱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የእለቱን የትምህርት ይዜት ካለፈዉ ትምህርት ጋር የሚገኙ የባህሎች እና የአከባቢያቸዉ ባህል ትርጉም መልሰዉ እንዲዘረዘሩ ማድረግ፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ባህሎች ምንምን እንደሆኑ ተሪዎችን መጠየቅ ናቸው፡፡ተማሪዎች በኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ የተለያዩ የባህል ይዜቶችን እንዲዘረዝሩ ማበረታታ ናቸዉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

ተማሪዎችን በቡድን በማቀናጀት የባህል ምንነት የተለያዩ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ ባህሎች ምንምን እንደ ሆኑ ተወያይቶበት ለክፍል እንዲያቀርቡ አበረታታቸዉ፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

ተማሪዎች የተማሩትን አስመልክተዉ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ የኢትዮጵያን ታዋቂ ባህሎች እና ታዋቅ እንዲሆኑ ያደርጋቸዉ ምንምን እንደሆኑ መጠየቅ፡፡ በብዙ ሰዎች ዘንድ የታወቁ መሆነቸዉን በመነጋገር እና ለነርሱም ተመልሰዉ እንዲዘረዘሩ ማድረግ፡፡ የተለየ ችሎታ ያላቸዉን ተማሪዎች በተለያየ የማስተማር ዘዴ በመጠቀም ማሳተፍ ጠቃሚ ናቸው ፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

**ተግባር 4.1**

ቀላል ካርታን በመሳል የትላልቅ ቋንቋዎችን ቤተሰብ እንዲያሳዩ አግዛቸዉ፡፡

**መልመጃ 4.1**

1. ባህል የአንድ አገር ወይም አከባቢ ህዝቦች አጠቃላይ ልምድ ነዉ፡፡ይኄዉም የኑሮ ሁኔታ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ ግንባታዎች፣ ደስታ እና ሀዘን የመሳሰሉት ናቸዉ

2. የባህል ይዘቶች ብዙ ናቸዉ ፡፡ እነዚህም ዋና ዋናዎቹ ዘፈን ፣የአለባበስ እና አነጋገር የእስፖርት ባህል ቋንቋ እምነት የተለያዩ በሌሎች ወዘተ ናቸዉ
3. በአከባቢያቸዉ የሚታወቁ ባህል እንድናገሩ አድርጋቸዉ
4. በኢትዮጵያ ዉስጥ ታዋቅ የሆኑት ባህሎች የእርቅ ባህል፤ የእንገዳ የአቀባበል እና የማስተናገድ ባህል ፣ የጋብቻ ባህል፣ የዘፈን፣ የአመጋገብ፣ ቋንቋ፣ የአመልኮ ስርዓቶች ናቸዉ፡፡

## 4.1.3 የኢትዮድያ ቋንቋ ቤተሰቦች

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት ---------------11

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገቡ ብቃት

- የኢትዮድያን ታላላቅ የቋንቋ ቤተሰቦች ይዘረዝራሉ፡፡

### ዋና ዋና ነጥቦች

*መመምህራን ተማሪዎች በሚኖሩበት በአከባቢ የሚነገሩ ቋንቋዎች እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ ትምህርቱን መጀምር ይኖርባቸዋል፡፡ መመምህራን ትላልቅ የቋንቋ ቤተሰቦች በመዘርዘር ለተማሪዎች ይገልፃሉ፡፡ የቋንቋን ካርታ በመጠቀም የት የት እንደሚገኙ ለተማሪዎች ያሳያሉ፡፡*

*መመምህራን የኢትዮድያን ቋንቋ ካርታ በማዘገጀት የትላልቅ ቋንቋ ቤተሰቦች መገኛ በሚያሳይ መልኩ የተለያዩ ምልክቶችን በመጠቀም ያሳያሉ፡፡*

## ቅድመ ዝግጅት

- ተማዎች ካርታን በመጠቀም የኢትዮድያን ትላልቅ ቋንቋ ቤተሰቦች መገኛ እንዲያሳዩ አድርጉአቸዉ
- ስለ ኢትዮድያን ቋንቋ የሚገልጽ መፃህፍትን ፈልገው በመግኝት ማንበብ እና በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ

ተማሪዎች ዋና ዋና የቋንቋ ቤተሰቦች ምን እንደሆኑ እንዲለዩ ማድረግ፡፡ ቀጥለው የቋንቋ ቤተሰቦች ምን ምን እንደሆኑ አጭር ማብራሪያ ከሰጡአቸዉ በኋላ ተማሪዎች በቡድን በማደራጀት የቋንቋ ቤተሰቦች እንደ ሴሜቲክ፣ ኩሽቲክ ስር የሚመደቡበትን በመዘርዘር ግንኙነታቸዉንም እንዲገልፁ ማበረታት አስፈላጊ ነዉ፡፡

የዉይይታቸዉን ሪፖርት ከጨረሱ በኋላ የትናንሽ ቋንቋቤተሰቦችን መገኛ በኢትዮድያ ካርታ ላይ በተወካዮቻቸዉ እንድአሳዩ አድርጉአቸዉ፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

የመልመጃ ጥያቀዎችን በማዘገጀት የቤት ሥራን ለተማሪዎች በመስጠት ብቃታቸውን በተከታታይ መገምገም፡፡ በኢትዮጵያ ካርታ ላይ የቋንቋ ቤተሰቦችን መገኛ እንድያሳዩ እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

## የመልመጃ ጥያቄዎች 4.2 መልስ

1. የኢትዮጵያን ትላልቅ የቋንቋ ቤተሰቦች የሆኑት የሴሜቲክ ቋንቋ ቤተሰብ፡ የኩሽክ፣ የኦሞቲክ እና የናይሎ ሰሐራ ቋንቋ ቤተሰቦች ናቸዉ፡፡
2. በኢትዮጵያ ዉስጥ በስፋት የሚነገሩ ዋና ዋና ቋንቋዎች ብዙ ሲሆኑ በብዙ ሰዎች የሚነገሩት ደግሞ ኦሮምኛ ፣ የአማርኛ እና የሶማሊኛ ቋንቋዎች ናቸዉ፡፡

### 4.1.4 በኢትዮጵያ ዉስጥ በስፋት የሚነገሩ ቋንቋዎች

በኢትዮጵያ ዉስጥ ከ80 በላይ የሚሆኑ ቋንቋዎች ይነገራሉ፡ ከነዚህም ዉስጥ ኦሮሚኛ እና አማርኛ በኢትዮጵያ ዉስጥ በስፋት የሚናገሩ ቋንቋዎች ናቸዉ፡፡ ኦሮማኛ ተናጋሪዎች 33.8% ሲሆኑ አማርኛ ተናገሪዎች ደግሞ 29.3% ናቸዉ ፡፡በኢትዮጵያ ዉስጥ ሌሎች በስፋት የሚነገሩ ቋንቋዎች ሱማሊኛ፣ትግረኛ፣ሲዳምኛ፣ ወላይተኛ፣ወዘተ ናቸዉ፡፡መምህራን ሌሎችም እንዳሉ ጨምረዉ ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

## 4.1.5 የኢትዮጵያ የባህል ቅርሶች

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት ----------------11

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገቡ ብቃት

- የዘመናዊ እና ባህላዊ የባህል ተቋማት ጥቅሞችን በመለየት ይገልፃሉ
- ባህላዊ ቅርሶችን የመጠበቅ ተጠያቅነት እና ድርሻ ምን ምን እንደሆኑ ይገነዘባሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥብ

ተማሪዎችን በጥያቄ እና መልስ ዘዴ የኢትዮጵያ ቋንቋ ቤተሰቦች እንዲዘረዘሩ ማድረግ፡፡ ተማሪዎች መልስ ስመልሱ በትኩረት መከታተል እና የማጠናከሪያ ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

- የኢትዮጵያ ካርታን በመጠቀም የኢትዮጵያ ታዋቂ የባህል ቅርሶች ማሳየት
- የኢትዮጵያ የባህል ቅርሶችን የሚያሳዩ የተለያዩ ሥዕሎችን በመፈለግ የቅርስ ምንነት ላይ ተጨማሪ መግለጫ መስጠትነዉ፡፡

- ካርታን እና የተለያዩ ሥዕሎችን ለተማሪዎች በማሳየት ትምህርቱን ሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

የዕቱን ትምህርት ይዜት ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት ቅርስ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎች እንዲናገሩ ማድረግ ነዉ፡፡ በመቀጠልም የባህል ቅርሶችን ማለት በድሮ ሰዎች ልምድ የተገኙ ስራዎች ሆነው ለቀጣይ የሚተላለፉ መሆናቸውን መግለጽ፡፡ ቀጣይ ትዉልድም ካለፉ ሰዎች ልምድ እወቀትና ትምህርት የሚያገኙ መሆናቸዉን ለተማሪዎች መግለጽ አስፈላጊ ነው፡፡በአከባቢያቸዉ ያሉትን የባህል ቅርሶች የሚያዉቁትን እንዲናገሩ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸዉ በቂ መረጃ በመጠየቅ ይዘዉ እንዲመጡ የፕሮጀክ ስራ ይሰጣቸዉ፡፡ ይሄዉም እያንዳዳቸዉ ከቤተሰቦቻቸዉ እንጅ ሌሎች ሰዎች መጠየቅ የለባቸዉም፡፡ይሄዉም ከወቅቱ የኮረና ቫይረስ እራሳቸዉን እንዲጠብቁ ስባል ነዉ፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

- የፕሮጀክት ሥራ የቅርሶችን አይነት እና ጠቀሜታቸዉ ቤተሰቦቻቸዉን ጠይቀዉ እንዲመጡ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ
- የባህል ቅርሶች ጠቀሜታ በቡድን ሆነው ከተወዩበት በኋላ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ
- አጫጭር ጥያቄዎችን በማዘጋጀት በመጠየቅ ያገኙትን ግንዛቤ በተከታታይ መገምገም፡፡

## 4.1.6 የኢትዮጵያ የተለያዩ ባህሎች መጠበቅ እና ማሳወቅ

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት ----------------------------------------1

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገቡ ብቃት

- የባህል ችግሮችን ይዘረዝራሉ
- የባህል መጠበቂያ (መንከባከቢያ) ዘዴዎችን ይናገራሉ
- የባህልን ማስተዋወቂያ ዘዴዎች እና ጥቅማቸውን ይገልፃሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

የባህል ችግር እና የመከላከያ ዘዴዎች ማስተማር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ሁለቱም የትኩረት ነጥቦች ናቸዉ፡፡ እነዚህን ነጥቦች ተማሪዎች ጋር የሚደረሰዉ በተለይ ዉይይትን በሚያሳይ ዘዴ ብሆን ይመረጣል፡፡

ይሄዉም የተለያዩ ችግሮችን የሚያዉቁ ተማሪዎች ከመፍተሔዎቻቸዉ ጋር መወያየት ስለሚችሉነዉ፡፡ፍላጎትና ችሎታ ያላቸዉን ተማሪዎች በመምረጥ የማስታረቅ ጥቅሞችን አቀባበልና ማስተናገድ የመሳሰሉት ላይ በመዘጋጀት ድርሻን መዉጣት፡፡ ልምዳቸዉን እንዲለዋወጡ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

- ሰዎች የሚታረቅበት የተፈጥሮ ሀብትና ዕፅዋትን ሰዎች እንዴት እንደሚከባከቡ እና የመሳሰሉት ሥዕሎችን ተጠቀሙ
- ተማሪዎች በምኖሩበት አከባቢ የሚገኙ የተለያየ ባህሎችን በመዘርዘር እና እንዲወያዩበት ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ተማሪዎች በትምህርታቸዉ ላይ እንዲያተኩሩ እና እንዲሳተፉ ጥያቄ በመጠየቅ ለምሳሌ የባህል ችግር ምንድነዉ? ላይ ሐሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ (ማበረታታ)፡፡ በሌላ በኩል እነዚህን ችግሮች ከላይ ከለዩ በኋላ ጥንድ ጥንድ ለመሆን ለችግሮቹ መፍቴሄ ያላቸዉን ሃሳብ አንድ ላይ በመዉጣት አሳብ በመለዋወጥ መልሰዉ እንዲገልፁ ማድረግ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

ተሪዎች በክፍል ተሳትፎ እና የተሰጠዉን የቤት ሥራን በአግባቡ መስራታቸውን እና የተመሪዎችን ብቃት በተከታታይ መገምገም እና የመሳሰሉት ናቸው ፡፡

## 4.1.7 የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ የኢትዮጵያ የባህል ቅርሶች

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት ------------------------------------------2

## ዋና ዋና ነጥቦች

በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙትን የባህል አይነቶች የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች መሆናቸውን መለየት ፡፡ የሚዳሰሱ ባህሎች ማለት ምን ማለት እንደሆነ በመግለፅ

ተማሪዎች የተሰጣቸዉን ምሳሌ በመጠቀም የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ባህሎችን እንዲለዩ ማብቃት ዋናዉ ነጥብ ነዉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የገዳ ትምህርት መፃሃፍ፤ የዜግነት እና የታርክ መፃሃፍ በማንበብ ትክክለኛ ግንዛቤ በማግኘት የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች በስዕል በማስደገፍ ትምህርቱን ማጠናከር ነዉ፡፡የሚዳሰሱ ቅርሶች ቤተክርስቲያኖች ፣ መስግዶች እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የሚዳስሱ ቅርሶች የራሳቸው የሆነ የበዓል አከባበር አላቸው ፡፡ የበዓል አከባበር ሁኔታ ደግሞ የማይዳሰሱ ባህሎች ናቸዉ፡፡ ስለዚህ ፎቶዎችና ስዕሎች ለዚህ ቦታዎች እንደ ትምህርት መረጃ መሳሪያነት ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

የማይዳሰሱ ቅርሶች ከሚዳሰሱ በምን ይለያል? ከሚለዉን በመነሳት በጥያቄ እና መልስ የመማር ማስተማር ሂደት ማስከድ አስፈላጊ ይሆናል ፡፡ በአከባቢያቸዉ የሚገኙ ቅርሶች እንዲዘረዝሩ እና ከቅርጾቹ ዉስጥ የሚዳሰሱትን እንዲናገሩ ሁኔታዎች እንዲመቻችላቸው ያስፈልጋል፡፡ የእነዚህን ቅርሶች በማህበራዉ እና በኢኮኖሚ ዉስጥ ያላቸውን ድርሻ ለይተዉ እንዲናገሩ በጥያቄ እና መልስ ዘዴ አቅርቡላቸዉ፡፡ በማወያየት ዘዴ እና ጥያቄ በመጠየቅ ትምህርቱን ማጠናከር ይቻላል፡፡

### 4.1.8 የኢትዮጵያ የባህል ቅርሶች እንክብካቤ የዜጎች ሀላፍነት እና ድርሻ

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት -------------------------------------3

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገቡ ብቃት

- ቅርሶችንየመጠበቅ ኋላ ፍነት እና ድርሻ ምን እንደሆነ ይገነዘባሉ
- ትላልቅ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ይለያሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

የባህል ቅርሶች ምንምን እንደሆኑ የመጠየቅ ባህሎችን ጠቃሚነት እንዲሁም እያደረሳቸዉ ያለዉን ችግር የዚህ ትምህርት ዋና ነጥቦች ናቸዉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የባህል ቅርሶችን የመጠበቅ ኋላ ፍነት እና ድርሻ እንዲሁም ለማቆየትና ለማገዝን አስመልክቶ የተፃፉትን ወይንም ተጨማር ምንጮችን በማንበብ በቂ ዝግጅት ማድረግ ነዉ፡፡ የዕለቱን ትምህርት ከመጀመራችሁ በፊት ተማሪዎች በቡድን በማደራጀት

የባህል ቅርሶችን መጠበቅና ማቆየት፡፡ ዜጎች መወጣት ያለባቸዉ ድርሻ ላይ በማወያየት ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

## የመማር የማስተማር ዘዴ

በዉይይት ፣ በጥያቄ እና መልስን ዘዴዎችን በመጠቀም የትምህርቱን አላማ ከግብ ማድረስ ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የባህል ቅርሶች በፕሮጀክት ሥራ የሚከባከቡበትን መንገድ እና የሚጠበቅበትን መረጃ የሚያገኙበት ጠይቀዉ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ ነዉ፡፡

### ተከታታይ ሚዘና

የመለማመጃ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የክፍል ተሳትፎ እና የመሳሰሉትን መጠቀም ነዉ፡፡

### የመልመጃ  ጥያቄዎች መልስ 4.3

1. የባህል ቅርሶች ባህላዊ ሰዎች ዉጤት ሆነዉ ለአሁኑ እና ለሚቀጥለዉ ትዉልድ እንደ ሀብት የሚጠቀሙ ልምድ እና እውቀት/ትምህርት/ የሚያስተላልፉ እና የገቢ ምንጭ  ናቸው፡፡
2. የማይዳሰሱ የባህል ቅርሶች የሆኑት የማይዳሰሱ እና በአይን የማይታይ ነገር ግን በአሳብ ያሉ የሚከበሩ ከትዉልድ ወደትዉልድ የሚያስተላልፍ ማለት ነዉ፡፡ ለምሳሌ የሚከበሩ በአላት፣የአመልኮ ስርዓቶች  እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
3. የማይዳሰሱ ቅርሶች ሆነዉ በዩኒስኮ (UNESCO) የተመዘገቡት የጥምቀት፣ ባዓል፣ የእሬቻ ባዓል፣ የጨበላላ በዓል እና የጥያ ድንጋይ ሲሆን የሚዳሰሱ ደግሞ ላሊበላ የፋሲል ግንብ፣የአክሱም አዉልት እና ከተማዋ አዋሽ፣ሰሜን ሸለቆ፣ ኦሞ ስምጥ ሸለቆ፣ሰሜን ቤሄራዊ ፓርክ፣ የጀጎል ግንብ እና የኮንሶ ልዩ የመሬት አቀማመጥ ናቸዉ፡፡
4. የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች ካላቸዉ ችግር ጥቅቶች፡- በቂ የመጓጓዥ መንገድ አለመኖር፣የስልክ ችግር፣ ጥበቃ አለመኖራቸው እና እንክብካቤ አለመኖር፣

## 4.1.9 ባህላዊ  እና ዘመናዊ  ተቋማት

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት ----------------2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገቡ ብቃት፡

- የኢትዮጵያ ትላልቅ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ይለያሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

የተለያዩ ባህላዊ እና ዘመናዊ ተቋማት በኢትዮጵያ ዉስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህም በማህበራዊ እና ኢኮኖማዊ ጉዳየች ዉስጥ ያላቸዉ ዉጤት ከፍ ያለነበር፡፡ እነርሱም በክልል እና በማህረሰብ ዉስጥ ልዩነት አላቸዉ የመላዉ ዋናዉ ነጥብ ነዉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

ባህላዊ ተቋማት የሚባሉት ሰዎች በኑሮአቸዉ ዉስጥ ለመተጋገዝ የመሠረቱት ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ማህበራት እና እቁብ የመሳሰሉት መሆኑን ከተረዱ በኋላ በአከባቢየቸዉ ባህላዊ ተቋማት ቤተሰብ፣ ጎረቤት እና የመሳሰሉትን በመጠየቅ ለክፍል ተማሪዎች ሪፖርት እንዲያደርጉ ማድረግ፡፡ ተማሪዎችን በማቀናጀት የዉይይት ነጥቦችን ማዘጋጀትና ማቅረብ የምሰጣቸዉ ጊዜ መወሰን የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡ ይህም የዕለቱን ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት በቂ ግንዛቤ በመስጠት ይከናወናል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ባህላዊ እና አመናዊ ተቋማት እንዲሁም ጥቅማቸዉ የሞላዉን ለማስተማር በቅዲሚያ የቤት ሥራን በግል ቤተሰብ ወይም ይህንን ሁኔታ የሚያዉቁ ሌሎች ሰዎች በመጠየቅ ወደ ክፍል በማምጣት ከተወያያችሁበት በኋላ እርስበርሳቸዉ እንድወያዩበት አግዙአቸዉ፡፡

በሚቀጥለው ክፍል ጊዜ ይህንን ትምህርት ለማጠናከር ስለምያገዝዎት የተማሪዎችን ፍላጎታቸዉን እና ችሎታቸዉን ከተረዱ በኋላ ሚናን በመጫወት ዘዴ በህላዊ ተቋማት አንድ ወይም ሁለት በመምረጥ ጥቅማቸዉን እና ጉዳታቸዉን እንዲያቀርቡ አበረታቱአቸዉ፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

የዚህን የትምህርት ይዜት ትምህርት ለማስጨበጥ ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ በመመልከት ሚና በምጫወቱበት ወቅት ያሳለፉት ዋና ነጥብ ማቅረብ ፡፡ በተጨማሪም በይዘቱ ላይ ተመስርተዉ ጥያቄ መጠየቅ ፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ለተማሪዎች ሁኔታዎችን በማመቻቸት አሳታፊ በሆነ መልኩ ብቃታቸውን በተከታታይ መገምገም፡፡

## የተግባር ጥያቄዎች መልስ

**ተግባር 4.2**

ተማሪዎችን በቡድን በማቀናጀት ይህንን ተግባር እንዲሠሩ ሁኔታዎችን አመቻቹላቸዉ፡፡

## 4.1.10 ለረጅም ጊዜ የቆየ ባህል እና ህይወት ያላቸዉ ባህል መካከል ያለዉ ልዩነት

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገቡ ብቃት፡

- በኢትዮጵያ ዉስጥ የተለያዩ ባህሎች መኖራቸዉን ይናገራሉ፡፡
- በባህሎች ልዩነት ዉስጥ የህዝቦች አንድነት መኖሩን ይገልፃሉ
- የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት አይነት እና በባህሎች መካከል ያለዉን ግንኙነት ያሳያሉ፡፡

## ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ትምህርት ርዕስ ሥር በተፈጥሮ ሀብት እና አጠቃቀማቸዉ መካከል ያለዉን ግንኙነት የሚገለጹበት ነዉ፡፡ ይህም ማለት በባህል ዉስጥ አከባቢን እና የተፈጥሮ ሀብትን እየጠበቅን እያንከባከባለን፡፡ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ዘዴዎቹን ተማሪዎቻችንን የምናስተምርበት ይሆናል፡፡

ለምሳሌ የኦሮሞ ህዝብ በገዳ ስርዓት ዉስጥ የኦዳ እንጨትን እስከ ዛሬ ድረስ ለምን እደሚጠቀሙበት እና ከፍተኛ አክብሮት እንደሚሰጡት ማስገነዘብ ፡፡ ከዚህ በመነሳት ለሌሎች ሀብቶች እክብካቤ እና ጥበቃ መደረግ እንደሚገባቸው የሀገሪቱ ማህበረሰቦች ኋላ ፍነት እንዳለባቸው ማስረዳት፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የመረጃ ምንጮችን በማንበብ ግንዛቤያቸውን ማዳበር አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የባህል እና የታሪክ መፃህፍትን በማንበብ ሰዎች በባህላቸዉ የአከባቢያቸዉ ተፈጥሮ ሀብት መንከባከብ ያስፈልጋል፡፡ የአከባቢያቸዉ ተፈጥሮ ሀብት በተለይ እየተጎዱ ያሉትን በባህላቸዉ ዉስጥ እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው ማስጫበጥ ያስፈልጋል፡፡ የታሪክ መጽሐፍትን በማንበብ ጓደኞቻቸዉን እና ሁኔታዉን የሚያዉቁትን ሰዎች በመጠየቅ፤ መምህሩን እና የዕድሜ ባለጠጎችን ማነጋገር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ተማሪዎችን ከተለያዩ የቤተሰብ ክፍሎች የመጡ ሥለሆኑ በአከባቢያቸዉ እንደሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶኝ እንዴት እንደሚያንከባክቡ እና እንደሚጠብቁ በጥየቄ እና መልክ የተማሪዎችን ሐሳብ በመቀበል ትምህርቱን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

ተማሪዎች ከመጡበት አከባቢ ጋር የሚመሳሰል ባህል ወይም የተለያየ መሆኑን በአጭር ጥያቄ ከጠየቁ በኋላ ጥንድ ጥንድ በመሆን በምን ሁኔታ ሰዎች ተግባብተዉ አብረው

እንደምኖሩ እንዲወያዩ ሁኔታን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ የዉይይቱን ደቂቃ ከወሰኑ በኋላ ተራ በተራ የዉይይታቸውን ውጤት ለክፍል እንድያቀርቡ አበረታቱአቸው፡፡

የተለያየ ቦታ የምኖሩ ሰዎች በባህላቸዉ ህግ መሠረት የተፈጥሮ ሀብትን እንዴት እንደሚያንከባከቡ እና እንደሚጠብቁ ማስረዳት፡፡ በኦሮሞ ብሔረሰብ በገዳ ስረዓት መሰረት ለተፈጥሮ ሀብቶች የሚያደርጉትን እንክብካቤ አስመልክቶ የሚያዉቁትን እንዲናገሩ አግዙአቸዉ፡፡ የኦሮሞ ህዝብ በባህሉ ዉስጥ ለተፈጥሮ ሀብት፤በተለይ ለእፅት እና ለዉሃ ምንጮች እንደ ባህር እና ወንዞች ጥበቃና እንክብካቤ የሚደርግ ሕዝብ ነዉ፡፡ የኮንሶ ህዝቦች ለአፈር እንክብካቤ በትኩረት የሚያደርጉት እንክብካቤ የሚያበረታታ መሆኑን እንዲናገሩ አድርጉ፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ ያሉህዝቦች ከመኖሪያ ቤታቸዉ ዉጭ የተለያዩ በአላትን እንደ ኢሬቻ ያሉት የት እንደመያከብሩ እና እነዚህ ቦታዎች ለምን እንደተመረጡ የሚያዉቁትን እንዲናገሩ አበረታቱአቸዉ፡፡ የተፈጥሮ ሀብትን በማንከባከብ ሂደት ዉስጥ የኦሮሞ ህዝብ የሚያከናውኑትን ስራዎችን ተማሪዎችን መጠየቅ፡፡ በተጨማሪም ጥያቄ ካላቸዉ መልስ በመስጠት የቀኑን ትምህርት ማጠናከር አስፈላገ ነዉ፡፡

## 4.1.11 ባህል በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያለዉ ድርሻ

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠ የክፍል ጊዜ ብዛት ------------------2

## ዋና ዋና ነጥቦች

ኢትዮጵያ ከምስራቅ አፍሪካ ዉስጥ በህዝብ ብዛት ቀዳሚ ደረጃ ይዛለች፡፡ እነዚህም ህዝቦች የተለያየ ባህል አላቸዉ፡፡ እንዚህ ባህሎች ከዚህ በፊት በነበረዉ ትምህርት ተምረዋል፡፡ የኦሮሞ፣የአማራ፣የሱማሌ፣የጉራጌ ባህሎች እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡ እነዚህ የተለያዩ ባህሎች በሀገራቷ ኢኮኖሚ ዉስጥ ከፍተኛ ድርሻ አላቸዉ፡፡የተለያዩ ሥራዎች እንደ ሻማ ፣ሽክላ ፣ማምረት እና የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤዎች (እንደ ኦሮሞ እና ኮንሶ ህዝቦች) የመሳሰሉትን በመዉሰድ ማስረዳት ይቻላል፡፡ ይህን አስመልክተዉ ተማሪዎች ከሚያዉቁት ላይ በመነሳት ስለ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዝግጅት እንድያደርጉ እና እንድገልፁ ማገዝ ነዉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

ግንዛቤን ለማዳበር ለዚህ ርዕስ የምሆኑትን የማጣቀሻ መፃህፍትን ማንበብ ካለፉት ክፍላት የህብረተሰብ መፃህፍን፣የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ በቂ ግንዛቤ ማደበር፡፡ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን የሚያሳይ የኢትዮጵያ ካርታን በመምረጥ ትምህርቱን ወደ ተሻለ ምቹ ሁኔታ ለማምጣት ዉይይት እንድያደርጉ ሁኔታን ያመቻቹ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

በገለፃ መልክ፣የኢኮኖሚ እንቅስቃሴንዎች፤የግለሰቦች የገቢ ምንጭ እና የሀገርዎን እንደሆነ በአጭሩ ይግለፁላቸዉ፡፡ በኢትዮጵያ ዉስጥ የህዝቦች ባህል የተለያየ በመሆኑ ምርታቸዉም የተለያየ መሆኑን ይገለጽላቸው፡፡ ይህም ደግሞ የተለያዩ የምርት ዉጤቶች ገበያ ላይ የማዋል ዕድል እንድፈጠር እና ገቢ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ በተለያዩ ማህበረሰብ የምመረቱ የተለያዩ የምርት ዉጤቶች ምንምን እንደሆኑ በጥያቄ እና መልስ ትምህርቱን ያጠናክሩት፡፡ በማስተማር ዘዴ ትምህርቱ እንድጠናከር ማድረግም ይቻላል፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

የመለመጃ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት አጫጭር ፈተናዎችን በመስጠት ተማሪዎች ለቀረቡት ሀሳብ መልስ በመስጠት ዉጤቱን መዝግቡ፡፡ የማጠናከሪያ ግብረ-መልስ በመስጠት የተማሪዎችን ብቃት ማሳደግ የምችለዉን መጠቀም ነዉ፡፡

### የመልመጃ 4.4 መልስ

1. በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ እና ብዙ የሆኑ ቅርሶች አሉ፡፡እነዚህም የማይዳሰሱ እና የሚዳሰሱ ቅርሶች ናቸዉ፡፡ የመስቀል በዓል አከባበር፤የትምቀት በዓል አከባበር፤የፍቼ ጨምበላላ፤የላሊበላ አቢያተ ክርስቲያናት፤የፋሲል ግንብ፤የአክሱም ሐዉልት እና ከተማዋ፤የአዋሽቀ፤የኦሞ ሸለቆ፤የሰሜን ናሽናል ፓርክ (የሰሜን ተራራዎች ፓርክ) የጢያ ድንጋይ እና የጀጎል ግንብ ናቸዉ፡፡
2. የማይዳሰሱ ቅርሶች በአይን የማይታዩ በእጅ የማይዳሰሱ ሥሆኑ የሚዳሰሱ ቅርሶች ደግሞ የሚታዩ እና በእጅ የሚዳሰሱ ናቸዉ
3. የቱሪስት ምንጭ በመሆን ገቢ ያስገባሉ

## 4.1.12 የኢትዮጵያ ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠ የክፍል ጊዜ ብዛት ------------------2

### ዋና ዋና ነጥቦች

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዉስጥ ህዝቦች በብዛት የሚሳተፉበት ግብሪና ስራ ላይ ነዉ፡፡ ግብሪና ማለት ሰብል ማምረት እና እንስሳት ማርባትን ያጠቃልላል፡፡ ስለዚህ በዚህ ትምህርት ዉስጥ ተማሪዎችን የአገባቢያቸዉን የህብረተሰቡን የአኮኖሚ እንቅስቃሴ ከገለፁ በኋላ በአጠቃላይ የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲገነዘቡ ማድረግ ነዉ፡፡

የኢትዮጵያ ህዝቦች በመጀመሪያ ደረጃ ኢኮኖኮኖሚ እንቅስቃሴ ዉስጥ በብዛት የሚሳተፉበት ሀገር ናት ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚባለዉ እርሻ፣ አሳን ማስገር፣የደን ሀብት መጠቁም ማዓድናትን ማዉጣት እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡ ከዚህም ዉስጥ በብዛት በእርሻ ላይ የሚሳተፉ ናቸዉ፡፡ ይሁን እንጂ ለሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችም እየተስፋፉ ይገኛሉ፡፡ እንዱስትሪዎች ማዕድናትን ማዉጣት፣ንግድ፤ ቱሪዝም፡ የአገለግሎት ሰጭ ተቋማት ወዘተ ናቸዉ፡፡

### ቅድመ ዝግጅት

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚን በማስመልከት የተለያዩ የህበረተሰብ ሳይንስ መፃህፍትን ማንበብ፣ አጫጭር እና ለዉይይት የሚሆኑ ጥያቄዎችን ቀድመዉ ማዘጋጀት፡፡ አጫጭር ማስታወሻዎችን ማዘጋጀት፡፡ተማሪዎችን ለመገምገም የሚረዱ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎች በሚሰጡት መልስ ላይ ትክክለኛ የሆነውን መልስ እና ግብረ መልስ መስጠት፡፡ መምህራን የተላያዩ የማጣቀሻ መጽሀፍቶችን በማንበብ ግንዛቤያቸውን ማጠናከር ያስፈልጋል ፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴ

ተማሪዎች አከባቢያቸውን እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ምን ምን እንደሆነ ማስረዳት፡፡ መምህራን የከባቢያቸዉን እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በማስመልከት የቃል ጥያቄ ማቅረብ ፡፡እንደ ሁኔታዉ የገለፃ ዘዴ በመጠቀም ከሰጡት ሐሳብ በመነሳት ትላልቅ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እንዲዘረዝሩ ማድረግ ነዉ፡፡ ከዘረዘሩት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዉስጥ ታላላቅ የሆኑትን እንዲናገሩ አበረታቱአቸዉ፡፡ተማሪዎች በሰጡት መልስ መሰረት የኢትዮጵያ ሕዝቦች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዙሪያ ማጠቃለያ ይሰጠበት፡፡ተማሪዎች ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

ከላዩ በኋላ ቤተሰቦቻችዉ በየትኛው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ እንደተሳተፉ እዲያቀርቡ ዕድል ይሰጣቸው ፡፡ተማሪዎች በቡድን ሆነው በአከባቢያቸው በስፋት ሕዝቡ እየተሳተፈበት የሚገኘው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እንዲያቀናጁ አበረታቱአቸዉ፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

የቃል ጥያቄ እና ተማሪዎች በሰጡት መልስ ላይ ግብረ-መልስ በማከል በተከታታይ መገምገም፡፡

## 4.1.13 .በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ግብርና ያለዉ ድርሻ እና ወደ ዉጭ የሚላኩ ሰብሎች

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠ የክፍል ጊዜ ብዛት -------------------4

ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገቡ ብቃት፡

- በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውሰጥ ግብርና የሚጫወተውን ሚና ይለያሉ
- በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ወደ ውጭ የሚላኩ የሰብል ምርቶችን ይዘረዝራሉ

## ዋና ዋና ነጥቦች

የዚህ ትምህርት ይዜት ትኩረት ትክክለኛ የግብርና ፊቺ ይሆናል፡፡ የግብርና እንስሳት ማርባት እና ሰብል ማምረትን ያጠቃልላል፡፡ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ህዝቦች የተሳተፉበት የስራ ዘሪፍ መሆኑን ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የግብርና ስራ በአየር ንብረት እና በመሬት አቀማመጥ ልዩነት ምክንያት ከቦታ ወደ ቦታ ልዩነት አለዉ፡፡አንዳንድ ቦታዎች (አከባቢዎች) በብዛት እንስሳትን የሚያረቡ ሲሆን በሌላ አከባቢዎች ደግሞ በብዛት ሰብልን የሚያመርቱ ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ ግብሪና ለምን ማደግ ያልቻለበት ለማስገንዘብ በጥያቄ እና መልስ ዘዴ ማወያየት ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ ግብሪና ስራ ሰብል ማምረት እና እንስሳትን በማርባት ዉስጥ ያሉ ችግሮችን እንዲገልጹ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

ከተማሪ መጽሐፍ ጋር ተያያዥነት ያለው ከሌሎች ምንጮችም ላይ አጫጭር ማስታወሻዎችን ማዘጋጀት ፡፡ሊተኮርበት የሚገባዉን ነጥቦችን በመለየት መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ የግብርና አይነቶች በመሬት አቀማመጥ እና አየር ንብረት ምክንያት አንዳዶቹ ሰብሎችን በማምርት ላይ ሲያተኩሩ ለሎች ቦታዎች ደግሞ እንስሳት ማርባት

ላይ ይሰማራሉ ፡፡ ሁለቱም በግብርና ስራ ዘርፍ ስር እንደሚከናወኑ ማስገንዘብ ያስፈልጋል ፡፡

## የማማር ማስተማር ዘዴ

መምራን ከተለያዩ የማማር ማስተማር ዘዴዎች ለምሳሌከገለፃ፣ ዉይይት ፣ ጥያቄ እና መልስ ዘዴዎች ውስጥ ምቹ የሆነውን መርጠው በመጠቀም የትምህርቱን አላማ ከግብ ማድረስ ይቻላል ፡፡ተማሪዎች በትምህርት ወቅት ያልገባቸዉን እንዲጠይቁ አበረታቱአቸዉ፡፡ መልሶችን በምሳሌ በማስደገፍ ይብራራላቸው፡፡የተገናዘቡትን እንዲገለፁ ዕድል ይሰጣቸው ፡፡ የግብረና ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸዉን አስመልክተዉ በቡድን ዉይይት ዘዴ ትምህርቱን ማጠናከር ተገቢ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

የመልመጃ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡ ተማሪዎች መልስ በሚመልሱበት ጊዜ በትኩረት በማዳመጥ፣ የሚያሳዩትን የበህሪይ ለውጥ በተከታታይ መገምገም ፡፡ የማጠናከሪያ ግብረ መልስ ተጨምሮበት ማጠቃለል ያስፈልጋል፡፡

## የመልመጃ 4.5 መልስ

1. የኢትዮጵያ ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች፡ግብርና እንዱስትሪ፣እና ቱሪዝም ናቸዉ፡፡
2. ግብርና ማለት የተለያዩ ነገሮችን ማምረትሲሆን እነሱም የተለያዩ እንስሳትን ማርባት እና ሰብል ማምረትን ያጠቃልላል፡፡
3. የኢትዮጵያ ግብርና ችግሮች ብዙ ናቸዉ፡፡ ከእነሱም ዋና ዋናዎቹ ድርቅ፣የአፈር መሸርሸር፣የደኖች መጨፍጨፍ፤ የግጦሽ መሬት እጥሬት፤ የገበያ እጥሬት እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
4. ግብርና አብዛኛው የሀገሪቱ ዜጎች የተሳተፉበት ነው ፡፡ በአጠቃላይ አብዛኛው የሀገሪቱ ህዝቦች እና የሀገሪቱ የገቢ ምንጭ ነዉ፡፡
5. ኢትዮጵያ ወደ ዉጪ ከምትልካቸዉ ዋና ዋና ምርቶች የግብርና ምርቶች ሲሆኑ እነርሱም ቡና፣ቆዳ እና ሌጦ፤ የጥራጥሬ ሰብሎች፤የቅባት እህሎች፣ማር እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

## 4.1.15 በኢትዮጵያ የሚገኙ ፋብሪካዎች እና ኢንዱስትሪዎች ድርሻ

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ በዛት -------------2

## ዋና ዋና ነጥቦች

የፋብሪካ እንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃዎች በመቀየር ወይም አዳድስ የተሻሉ ምርቶች የሚመረቱበት ነዉ፡፡ተማሪዎች የሚያዉቁትን ፋብሪካዎች እና የሚያመረቱትን የዕቃ አይነቶች እንዲዘረዝሩ ማድረግ ፡፡እንዱስትሪዎች የሚጠቀሙበትን ጥሬ ዕቃ እንድናገሩ አበረታቱአቸዉ፡፡ በመቀጠልም በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ፋብሪካዎች ወይም ኢንዱስትሪዎች በብዛት ቀላል መሆናቸዉን እንዲያዉቁ በገለፃ ውስጥ ማካተት ፡፡ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ዉስጥ ፋብሪካዎች እየተስፋፉ መሆኑን መግለጽ፡፡ እንዲሁም የእንዱስትሪ ፓርኮች በተለያዩ ክልሎች የተመሠረቱትን መዘርዘር ያስፈልጋል፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

በተማሪ መጽሐፍ ያሉትን ሐሳቦችን በማንበብ አጭር ማስታወሻ ማዘጋጀት እና ከዚህ ርዕስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችን ማጠናከር ፡፡ የፋብሪካ ወይም ኢንዲስትሪ አይነቶች እና ትርጉማቸዉን በተመለከተ የተሸለ ግንዛቤ መጨበጥ ያስፈልጋል፡፡የኢትዮጵያ የፋብሪካ ወይም እንዱስትሪ ሥርጭት የሚያሳይ የኢትዮጵያ ካርታ ማዘጋጀት ያስፈልገል፡፡ ተማሪዎች ፋብሪካ ወይም ኢንዱስትሪዎች ምን እንደሆኑ ከመጠየቃቸው በፊት የፋብሪካ ምርቶች አይነት ላይ ሁለት ሁለት ሁነዉ እንዲወያዩ አድርጉአቸዉ፡፡ የተወያዩባቸዉን የፋብሪካ እና የግብርና ዉጤቶች እንዲለዩ አድርጓቸዉ፡፡ በመቀጠልም የፋብሪካ ምርቶች ሂደት ለይ እንዲወያዩ አድርጏቸዉ፡፡ ቀጥሎም ፋብሪካዎች ጥሬ ዕቃዎችን ሰዎች እንደሚጠቀሙበት እና ለገበያ ፍጆታ እንዲውል የሚያመርት መሆኑን ማስገንዘብ ፡፡በመጨረሻም ከጥሬ ዕቃዎች ዕቃዎች ተለውጠው አዳድስ ምርቶች ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን ማስገንዘብ ነዉ፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

የክፍል ተሳትፎ፤ የቃል ጥያቄ እና የመሳሰሉትን ተራ በተራ የተወሰኑ ተማሪዎችን በመጠየቅ፡፡ የትምህርቱን አላማ ግብ እንድመታ ጠይቁአቸዉ፡፡ መልመጃዎችን በማዘጋጀት በክፍል ዉስጥ እንዲሰሩ አበረታቱአቸዉ፡፡

### 4.1.16 የኢትዮጵያ ፋብሪካ እና እንዱስትሪዎች ዋና ዋና ችግሮቻቸዉ እና አይነታቸዉ

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ----------1

## ዋና ዋና ነጥቦች

ተማሪዎች ትላልቅ የፋብሪካ አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ከተናገሩ በኋላ በዕድገታቸዉ ላይ እንቀፋት የሆኑ ችግሮችን እንዲዘረዝሩ አድርጉአቸዉ፡፡ እነዚህ ችግሮች በተከታታይ የሚከሰቱ የጥሬ ዕቃዎች እጥሬት፣ የቴክኖሎጅ እና የተለያዩ እጥሬቶች ናቸዉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የፋብሪካ ኢንዱስትሪዎችን ስርጭት የሚያሳይ የኢትዮጵያ የፋብሪካ ወይም ኢንዱስትሪዎች ሥርጭት መገንዘብ፡፡ አጫጭር ማስታወሻዎችን መያዝ እና የመመዘኛ ጥያቄዎችን መጠየቅ ናቸዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

መምራን ከተለያዩ የማማር ማስተማር ዘዴዎች ለምሳሌከገለፃ፣ ዉይይት ፣ ጥያቄ እና መልስ ዘዴዎች ውስጥ ምቹ የሆነውን መርጠው በመጠቀም የትምህርቱን አላማ ከግብ ማድረስ ይቻላል

## ተከታታይ ሚዘና

የክፍል ተሳትፎ፤ የቃል ጥያቄ እና የመሳሰሉትን ተራ በተራ የተወሰኑ ተማሪዎችን በመጠየቅ፡፡ የትምህርቱን አላማ ግብ እንድመታ ጠይቁአቸዉ፡፡ መልመጃዎችን በማዘጋጀት በክፍል ዉስጥ እንዲሰሩ አበረታቱአቸዉ፡፡በመጨረሻም የግንዛቤ ደረጃቸውን በመገምገም ገንቢ ግብረ መልስ በመስጠት፡፡

## 4.1.17 የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ቱሪዝም አይነቶች፡፡

ለዚህ ትምህርት ይዜት የተሰጠ የክፍል ጊዜብዘት -----------------------------------------------2

## ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ርዕስ የተጠቃለሉ ዋና ዋና ነጥቦች የቱሪዝም ምንነት ፣የቱሪዝም አይነቶች፣ የቱሪዝም ቦታዎች እና ትላልቅ ብሔራዊ ፓርኮች ናቸዉ፡፡

## ቅድመ ዝግጅት

የኢትዮጵያ ቱርዝም ላይ የተፃፉ የተለያዩ ፅሑፎችን ከባህል እና ቱርዝም ቢሮ በማግኘት ግንዛቤያችሁን ማዳበር ፡፡ በቱሪዝም ካርታ ላይ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ፓሪክ ሥርጭት የሚያሳይ በማግኘት መጠቀም ፡፡ የትምህርቱን ዋና ዓላማ ከግብ የሚያደርሱ ነጥቦችን አስቀድመው ማቀናጀት ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

መምራን ከተለያዩ የማማር ማስተማር ዘዴዎች ለምሳሌከገለፃ፣ ዉይይት ፣ ጥያቄ እና መልስ ዘዴዎች ውስጥ ምቹ የሆነውን መርጠው በመጠቀም የትምህርቱን አላማ ከግብ ማድረስ ይቻላል ፡፡የቱሪዝም ፍቺ እንዲሰጡ ጥያቄ በመጠየቅ ይጀምሩ፡፡ ተማሪዎች የምሰጡትን መልስ በማድመጥ የቱሪዝም ዘርፍ ለመዝናኛነት የምጠቅም መሆኑን ተማሪዎችን ማስጨበጥ ያስፈልጋል ፡፡ በአከባቢያቸዉ በቱሪስት የምጎበኙ ቦታዎች ካሉ እንዲናገሩ ማድረግ ፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የቱሪዝም አይነቶች እንዳሉ ማስረዳት ፡፡ የሚዳሰስ እና የማይዳሰሱ የቱሪዝም ቅርሶች ፤የታሪክ ቱሪዝም፣የአሪኮሎጂ ቱሪዝም እና የመሳሰሉትን እንዲረዱ ማድረግ፡፡

### ተከታታይ ሚዘና

ተማሪዎችን በቡድን በማደረጀት የኢትዮጵያ ካርታን በማዘጋጅት የፓርኮች መገኛ እንዲያሳዩ በማድረግ ግንዛቤያቸውን መገምገም ፡፡

## 4.1.18የኢትዮጵያ ቱሪዝም በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ላይ ያላዉ ድርሻ

ለዚህ የትምህርት ይዜት የተሰጠዉ የክፍል ጊዜ ብዛት----------------------------------2

## የመማር ማስተማር ዘዴ

መምራን ከተለያዩ የማማር ማስተማር ዘዴዎች ለምሳሌከገለፃ፣ ዉይይት ፣ ጥያቄ እና መልስ ዘዴዎች ውስጥ ምቹ የሆነውን መርጠው በመጠቀም የትምህርቱን አላማ ከግብ ማድረስ ይቻላል፡፡ ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን የኢትዮጵያ ቱሪዝም በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ላይ ያላዉ ድርሻ እና ችግር ላይ ከተወያዩ በኋላ እንዲገልፁ አግዙአቸዉ፡፡ ቱሪዝም ከምሳጠዉ ትልቁ ጥቅም ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ መሆኑን ማስረዳት፡፡ ይህም ማለት በአከባቢ ላይ የአየር ብክለት /ችግር/ ሳያከትል ጥቅም ይሰጣል ማለትነዉ፡፡በመቀጠልም በአከባቢያቸው ሆነ በሌሎች ቱሪዝም ለህዝቡ የሚያስገኘው ጥቅሞችን እንዲያብራሩ ጠይቁአቸዉ፡፡

## ተከታታይ ሚዘና

ተማሪዎች የመለማመጃ ጥያቄዎች፣ የጹሑፍ እና የቃል ጥያቄዎችን ስሰሩ መገምገም፡፡ እንዲውም ተማሪዎች በግል እና በቡድን ስራ ውስጥ የሚያሳትን ተሳትፎ እና የባህሪይ ለውጥ በተከታታይ በመመዝገብ መገምገም ናቸው፡፡

**የምዕራፍ 4 የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ**

## I. እውነት/ሐሰት

1.ሐሰት 2.ሐሰት 3. እዉነት 4.እዉነት

## II.አዛምድ

1. ረ 2.ለ 3.ሀ 4.ሐ

## III. የምርጫ ጥያቄዎች መልስ

1. ለ 2.ለ 3.ሐ 4.ሐ 5.ለ 6.ሀ

## IV. የአጫጭር ጽሑፍ መልስ ጥያቄ

ከ1-4 ያሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎች እንደ አከባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ እንዲመለሱ አግዙአቸዉ፡፡

# ምዕራፍ-5 የተለየ ትኩረት የምሹ ጉዳዮች

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠዉ ክፍለ ጊዜ ………………………………………………30

የዚህ ምዕራፍ የመማር ዉጤት

የዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡-

- ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በሀገር ላይ የሚያመጣዉን ተፅዕኖ በመለየት ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- የኢትዮጵያን የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ስርጭት ዳታን ትለያለህ/ሽ፡፡
- ጉዳት የሚያደርሱትን ኬሚካሎች እና መድኃኒቶች ትለያለህ/ሽ፡፡
- ሱስ የሚያስዙ ዋና ዋና ነገሮችን ትዘረዝራለህ/ሽ፡፡
- በወረዳ እና በዞን ዉስጥ የሚገኙትን ጎጂ ልማዶች ትለያለህ/ሽ፡፡
- የድርቅ እና የረሃብን ፅንሰ ሀሳብ ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- ለኢትዮጵያ ድርቅ ምክንያቶች እና መንስኤዎቹን ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- የዝናብ ሥርጭትን በሚያሳዩት የመረጃ ቴክኖሎጅዎች በመጠቀም የዝናብን ሁኔታ ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- የዝናብ ካርታን በመጠቀም በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙትን ደረቃማ ቦታዎች ታሳያለህ/ሽ፡፡
- የኢትዮጵያ ደርቅ ለመቋቋም የሚጠቅሙ የሀገር ዉስጥ ዘዴዎችን ትዘረዝራለህ/ሽ፡፡
- በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙትን ድርቅ ቦታዎች ትለያለህ/ሽ፡፡
- ድርቅ የግድ ለረሃብ መንስኤ እንደማይሆን ምክንያቶቹን ትገልፃለህ/ሽ፡፡

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ የተለያዩ ርእሶች እንደየኤች.አይ.ቪ.ኤድስ በኢትዮጵያ፣ ህገወጥ ኬሚካሎች እና መድኃኒቶች፣በአከባቢያችን ጉዳት የሚያስከትሉ ጎጂ ልማዶች እና ድርቅ እና ረሃብ የሚሉትን ትማራላችሁ፡፡እያንዳንዱ ርዕስ የተለያዩ ይዘቶች አሉት፡፡ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ በኢትዮጵያን በሚለዉ ስር ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ያለዉ ተፅዕኖ፣ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ስርጭት በኢትዮጵያ፣ የኤች .አይ.ቪ.

.ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች፤ የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከላከያ መንገዶች፤ ለኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ታማሚዎች የሚደረግላቸዉ ድጋፍ እና እንክብካቤ ትማራላችሁ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በወረዳ ዉስጥ ህገወጥ ኬሚካሎች እና መድኃኒቶችን መጠቀም በምለዉ ርእስ ስር፡- በሚካሎች እና መድኃኒቶች ሱስ መያዝ የሚያመጠዉ ጉዳት፤በአከባቢያችን ጉዳት የሚያስከትሉት ጎጂ ልማዶችን ትማረለችሁ፡፡ ለአከባቢያችን ድርቅ ምክንያት እና መንስኤ ልሆኑ ከሚችሉት ነገሮች በሚለዉ ርዕስ ስር ደግሞ የአከባቢያችን የሚገኙትን ደረቃማ ቦታዎች እና ዓይነቶችን ትማራላችሁ፡፡

## 5.1 ኤች.አይ.ቪ.ኤድስበኢትዮጵያዉስጥ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠዉ ክፍለ ጊዜ: ............................7

የዚህ ርዕስ የመማር ዉጤት

የዚህ ርዕስ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡-

- ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በሀገር ላይ የሚያመጣዉን ተፅዕኖ በመለየት ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- የኢትዮጵያን የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ስርጭት ዳታን ትለያለህ/ሽ፡፡

***ዋና ዋና ነጥቦች***

የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ በኢትዮጵያን ዉስጥ በሚለዉ ርዕስ ስር፤ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያመጣዉን ተፅዕኖ፤ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ስርጭት በኢትዮጵያ፤የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች፤የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከላከያ መንገዶች፤ለኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ታማሚዎች የሚደረግላቸዉ ድጋፍ እና እንክብካቤን መማር አለባቸዉ፡፡ ይህን ምዕራፍ ለማስተማር ሰባት(7) ክፍለ ጊዜ ተሰጥተዋል፡፡ በዚህ በተሰጠዉ ክፍለ ጊዜ ዉስጥ ተማሪዎች ልጎናፃፉ የሚገባቸዉን እንድጎናፃፉ የተለያዩ የመማር እና ማስተማሪያዘዴዎች እና የተለያዩ የትምህርት መርጃ መስሪያዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡

ይህን ርዕስ ለማስተማር ከሚንጠቀምባቸዉ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ጥቅቶቹ፡- ጥያቄ እና መልስ፤የቡድን ዉይይት፣የጥንድ ዉይይት፣ የአጠቃላይ ክፍል ዉይይት፣ ገለፃ፣ ፕሮጀክት፣ ምልከታ እና ሚና መጫወት ናቸዉ፡፡ በዚህ ርዕስ ሥር ያሉትን ትምህረቶች ለማስተማር በኤች.አይ.ቪ እና ኤድስ መካከል ያለዉን ልዩነት፤ በሶስተኛ ክፍል ዉስጥ የተማራችሁትን የኤድስ ምልክቶች፤እንድሁም የመተላለፊያ መንገዶች እና የመከላከያ ዘዶዎቹን ደግሞ በአራተኛ ክፍል ዉስጥ ከተማሩት ጋር እንድያያዙ ከመምህራኖች ይጠበቃል፡፡

# ቅድመ ዝግጅት

*መምህር/ት ይህን ርዕስ ከማስተማሩ/ሯ በፊት አስፈለጊዉን ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከሚያስፈልጉት ዝግጅቶቹ ዉስጥ አንዱ ጥልቀት ያለዉ የትምህርት ክፍለጊዜ ማዘጋጀት ነዉ፡፡ ለተሰጡት ሰባቱም የትምህርት ክፈለጊዜ ማዘጋጀት አስፈለጊ መሆኑ ግልፅ ነዉ፡፡ ለእያንዳንዱ ክፍለጊዜ እቅድ ስታወጡ ከርዕሱ ጋር ግንኙነት ያላቸዉን መረጃዎች ከተማሪዎች መጽሃፍት እና በመምህሩ መምሪያ ላይ የተጠቀሱትን፣ተግባራት እና መልመጃዎችን በደንብ መረዳት አስፈለጊ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን የማጣቀሻ መጽሀፍትን በድንብ ማንበብ ያስፈልጋል፡፡እንድሁም የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ከአከባቢ ከሚገኙት ነገሮች በማዘጋጀት እና በመጠቀም የሚጠበቀዉን ብቃት ለማሳከት መጣር አለባቸዉ፡፡ የህን ርዕስ ለማስተማር የሚረዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ዉስጥ ጥቂቶቹ፡-*

- *የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጉዳት እና ስርጭትን ሚያሳዩ ሥዕሎች፣ፎቶዎች እና ፖስተሮችን በመጠቀም፡፡*

***የመማር ማስተማሪያ ዘዴ***

*ይህን ርእስ ለማስተማር መምህር/ት አስቀድመዉ የመግቢያ ይዜት ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎች ከሚያዉቁት በመነሳት በጋራ እንድወያዩ እና እንድገለፁ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነዉ፡፡ በተለይም መምህሩ/ቷ ይህን ርዕስ ሚና በመጫት የማስተማር ዘዴ ብተቀሙ ተመራጭ ነዉ፡፡*

*በዚህ ዘዴ ለማስተማሪ በቅድሚያ ለተማሪዎች የሚጫወቱበት ድርሻ መከፋፈል አለበት፡፡ ለምሳሌ፡- አባት፣ልጆች፣ጎረቤት እና የጤና ባለሙያ በመሆን መከፋፈል ይቻላል፡፡ በዚህ ዘዴ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች እና መከላከያዉን ማስተማሪ ተመራጭ ነዉ፡፡*

*የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በግለሰብም ሆነ በሰፊዉ ቤተሰብ ዉስጥ በሚያደርሰዉ ጉዳት ላይ ግንዛቤ በማግኘት ከዚህ በሽታ እራሳቸዉን እንድጠብቁ ያግዛል፡፡ ይህንን ግንዛቤ ለማጠናከር የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ትችላላችሁ፡፡*

*ለምሳሌ፡-*

- *በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ክበባት ዉስጥ መሳተፍ እንደሚገባቸዉ፡፡*
- *በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ላይ የተፃፉትን ፅሁፎች ማንበብ አለባቸዉ*
- *በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰራጩትን መረጃዎች ከተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን መከታተል እንዳለባቸዉ*

- በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ላይ ከሚሰሩት የጤና ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የራሳቸዉን ግንዛቤ እንድያዳብሩ እና የመሳሰሉትን እንድያከናወኑ በጥልቀት ማስተማር አለባችሁ፡፡

የኤድስ በሽታ እድሜን፣ ፆታን፣መልክን እንድሁም የትምህርት ደረጃን ሳይለይ ሁሉንም የህብረተሰብ የሚጎዳ ስሆን በተጨማሪም የዚህ በሽታ መስፋፋት በዜጋዎች ላይም ሆነ በህገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያመጣ ተፅዕኖ፣ ድህነት እና ሥራ አጥነት እንድሰፋፋ በማድረግ ትልቅ ድርሻ ያለዉ መሆኑን በደንብ መረዳት አስፈላጊ ነዉ፡፡በመቀጠልም በ5.1 ስር ያሉትን የመልመጃ ጥያቄዎች ላይ በቡድን እንድወያዩ እና ለክፍሉ እንድያቀርቡ አበረታታቸዉ፡፡

የ2012/13 ዓ.ም.የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ተቋም እንደሚያሳየዉየኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ስርጭት በደማቸዉ ዉስጥ የተገኘ በፆታ ተለይተዉ በሰንጠረዥ 5.1. ዉስጥ የተቀመጡትን በቡድን ተወያይተዉ ለክፍሉ እንድያቀርቡ ሁኔታዎችን በማመቻቸት መርዳት አስፈላጊ ነዉ፡፡
በኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች እና የመከላከያ መንገዶች ላይ በአቅራቢያቸዉ የሚገኙትን ሰዎች በመጠየቅ በግል ለክፍሉ እንድያቀርቡ በማድረግ፣ በመጨረሻም በሙሉ ክፍል እንድወያዩበት በማድረግየመጠቃሊያ ሀሳብ ስጥዋቸዉ፡፡

የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ በደማቸዉ ለሚገኙት ሰዎችልደረግላቸዉ በሚገቡድጋፎችእና እንክብካቤዎች ላይ ሚና በመጫወት የማስተማሪያ ዘዴ እንድታስተምሩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት፣ በሚያቀርቡበት ጊዜ ስህተት ካለ ለማስተካከል ሞክሩ፡፡ በተጨማሪም በሰንጠረዥ 5.2 ስር ያሉትን የመልመጃ ጥያቄዎች በግል ከሰሩ በኋላ በጥንድ በመሆን ሀሳባቸዉን እንዲካፈሉ እና በመጨረሻ በቡድን እንድወያዩበት እና ለሁሉ ክፍል እንድያቀርቡ ሁኔታዎችን በማመቻቸት መርዳት ያስፈልጋል፡፡

ተማሪዎች ተራ በተራ ለክፍሉ ያቀረቡትን ሀሳብ በመነሳት በክፍለ ጊዜዎቹ ትምህርት ላይ ዋና ዋና ነጥቦች እናማጠቃለያ በመስጠት ትምህረቱን ማጠቃለል ትችላላችሁ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታን እንድያዳብሩ መርዳት**
ተማሪዎች አስር አባል ባለዉ ቡድን በመከፋፈል በአከባቢያቸዉ የሚገኘዉን የጤና ተቋም በመጎብኘት ስለ ኤች.አይ. ቪ. ኤድስ የሚገልፁትን ሥዕሎች እና ፖስተሮች እንድሰሩ ፕሮጀክት ስጥዋቸዉ፡፡ ተማሪዎቹም በቡድን የሰሩትን ለሁሉ ክፍል እንድያሳዩ አደርጓቸዉ፡፡ ስያቀርቡም በመከታተል መስተካከል የሚገባቸዉን

መስተካከል ያስፈልጋል፡፡ የፈጠራ ሥራ ያቀረቡትን ተማሪዎች መበረታታት፤ሞራል እና እዉቅና መስጠትም አስፈላጊ ነዉ፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ሥር የሉትን ሁሉ በግል ወይም በቡድን ሆነዉ ፕሮጀክት፣ጥያቄዎች እና የተለያዩ ተግባራትን እንድሰሩ በማድረግ
- ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን የሰሩትን በቅርበት በመከታተል እና ግብረ መልስ በመስጠት ገንቢ ሀሳቦችን መስጠት ነዉ፡፡
- ተማሪዎች በሰሩት ፕሮጀክት ላይ ስወያዩ እና ስገልፁ በመከታተል
- በተማሪዎች መጽሃፍት ዉስጥ ከተጠቀሱት የተለያዩ ተግባራት እና የመልመጃ ጥያቄዎች ዉስጥ ጥቂት ጥያቄዎችን በመዉሰድ የክፍል እና የቤት ሥራ እንድሰሩ በማድረግ
- የተሳሳቱትን እንድያስተካክሉ በማገዝ
- የተማሪዎችን አፈፃፃም ገምግመህ በመመዝገብ
- የተማሪዎች ግንዛቤ በሚያጠናክሩ ሁኔታዎች ላይ እያቀዱ በመሄድ፡፡

**የትግባራ መልሶች**

**መልመጃ 5.1**

1. ኤች.አይ.ቪ. የሚተላለፉባቸዉ መንገዶች
   - ጥንቃቄ በጎደለዉ ልቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት
   - ያልተመረመረ ደም ለታማምዎች በመስጠት
   - ስለት ባላቸዉ መሳሪያዎች በጋራ በመጠቀም እና በመሳሰሉት ነዉ፡፡
2. ወጣቶች ከጋብቻ በፊት
   - ጥንቃቄ ከጎደለዉ ልቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት እራሳቸዉን በመጠበቅ
   - ከጋብቻ በፊት የደም ምርመራ ማድረግ
   - በማንኛዉም ሁኔታ የሌሎችን ደም አለመንካት
   - ስለት ያለቸዉን መሳሪያዎች ከሌሎች ሰዎች በጋራ አለመጠቀም እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
3. የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በትምህርት ላይ ያለዉ ተፅዕኖ፡-
   - ይህበሽታ ህፃናትን ያለቤተሰብ ያስቀራል፡፡ በዚህም የተነሳ ህፃናት እራሳቸዉን ችሎ ለመኖር ስለምችገሩ ትምህርታቸዉን ሊያቋርጡ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ በትምህርት ቤት ዉስጥ የተማሪዎችን ተሳትፎ ይቀንሳል፡፡

4. ከኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች
   - ከኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን አለማግለል ፣ተገቢዉን እንክብካቤ በማድረግ እና ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነት በመፍጠር አብሮ መኖር
   - የበሰሉ ምግቦችን በመስጠት፣ልብሳቸዉን በማጠብ እንድሁም የጤና አገልግሎት እንድያገኙ ማገዝ አስፈላጊ ነዉ፡፡

**መልመጃ** 5.2

1. የሀገርን ቁጠባ እና እንቨስትመንት ይቀንሳል፡፡
   - የጤና ተቋማት ወጭን እንድጨምር ያደርጋል
   - ምርትን እና ምርታማነትን በመቀነስ የግል ገቢን ይቀንሳል
   - ህፃናትን ያለቤተሰብ ያስቀረል፡፡
   - በትምህርት ቤት ዉስጥ የተማሪዎችን ተሳትፎ ይቀንሳል፡፡
2. ኤች አይቪ ኤድስ ለመከላከል
   - ከጋብቻ በፊት የግብረ ስጋ ግንኙነት አለማድረግ
   - ከጋብቻ በፊት የደም ምርመራ ማድረግ
   - በማንኛዉም ሁኔታ የሌሎችን ደም አለመንካት
   - ስለት ያለቸዉን መሳሪያዎች ከሌሎች ሰዎች በጋራ አለመጠቀም እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
3. ህፃናትንያለቤተሰብ በማስቀረት እናትምህርታቸዉንእንድያቋርጡ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ የተማረ የሰዉ ኃይልን ይቀንሳል፡፡

## 5.2 በወረዳዉስጥህገወጥኬሚካሎችእናመድኃኒቶችንመጠቀም

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠዉ ክፍለ ጊዜ ……………….8

የዚህ ምዕራፍ የመማር ዉጤት

የዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡-

- ጉዳት የሚያደርሱ ኬሚካሎች እና መድኃኒቶችን ይለያሉ፡፡
- ሱስ የሚያስዙ ዋና ዋና ነገሮችን ይዘረዝራሉ

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ ርዕስ ሥር በወረዳ ዉስጥ ህገወጥ ኬሚካሎች እና መድኃኒቶችን መጠቀም እና በኬሚካሎች እና መድኃኒቶች ሱስ መያዝ የሚያስከትለዉን ጉዳት ይማራሉ፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር የተሰጠዉ የክፍለጊዜ ብዛት ስምንት (8) ነዉ፡፡ ተማሪዎች ቢያንስ ልጎናፃፉ የሚገባቸዉን እንድጎናፃፉ የተለያዩ የመማር እና ማስተማሪያ ዘዴዎች፣

የተለያዩ የትምህርት መርጃ መስሪያዎች እና የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡

ተማሪዎች ይህን ርዕስ በመማር የወደፍት ማህበራዊ ኑሮአቸዉን እና በሚማሩበት ሁለተኛ ደረጃ እና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ዉስጥ መሰረት በመሆን ያገለግላል፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር ከሚንጠቀምባቸዉ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ጥቅቶቹ፡-

- ጥያቄ እና መልስ
- ገለፃ በመስጠት
- በማሳያት/በምልከታ
- በቡድን፣ በጥንድ እና በሁሉ የክፍል ዉይይት በመስጠት
- በፕሮጀክት፣ በምልከታ እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

### ቅድመ ዝግጅት

መምህር/ት ይህን ርዕስ ከማስተማሩ/ሯ በፊት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ጥልቀት ያለዉ የትምህርት እቅድ ማዘጋጀት ነዉ
- ከርዕሱ ጋር ግንኙነት ያላቸዉን መረጃዎች ከተማሪዎች መጽሃፍት እና በማምህሩ መምሪያ ዉስጥ የተጠቀሱትን በደንብ መገንዘብ
- ከርዕሱ ጋር ግንኙነት ያላቸዉን ፣ተግባራት እና መልመጃዎችን በደንብ መረዳት
- ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን የመጣቀሻ መጽሀፍትን በማንበብ የራስን ግንዛቤ ማዳበር
- የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በአከባቢ በሚገኙት እንደ የተምባሆ ተክል፣ጫት፣ አልኮል ወይም
- የተምባሆ ፣የአደንዛዥ እፅዎች እና የአልኮል መጠጥ የሚያስከትለዉን ጉዳት የሚያሰይ ሥዕል በማሳየት፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴ

ተማሪዎችን ህገወጥ ኬሚካሎች እና መድኃኒቶች እነማን ናቸዉ የሚለዉን እንድገልፁ በመጠየቅ ይህን ርዕስ ማስጀመር ይቻላል፡፡ተማሪዎቹም በህገወጥ ኬሚካሎች እና መድኃኒቶች ላይ በጥንድ እና በቡድን በመሆን እንድወያዩበት አድርጉ፡፡

- የዉይይታቸዉንም ዉጤት ለክፍሉ ተማሪዎች እንድያቀርቡ አድርጉ
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት ተማሪዎች በፊት ያላቸዉን እዉቀት ለመገንዘብ እና ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚያገለግሉ ወደ ገለፃ ከመግባት

በፊት በቡድን ተወያይተዉ ሀሳባቸዉን እንድገልፁ አድርጉ፡፡ በተጨማሪም የመልመጃ 5.3 ጥያቄዎችን መጀመሪያ በግል እንድለማመዱ፤ በመቀጠል በጥንድ እንድወያዩ፤ ከዚያ በኋላ በቡድን ተወያይተዉ ሀሳባቸዉን እንድለዋወጡ በማድረግ፤ ገንቢ ግብረ መለስ እና ትክክለኛ የሆነዉን መልስ ይስጡአቸዉ፡፡

- ህገወጥ ኬሚካሎች እና መድኃኒቶች ብዙ ጊዜ እና ተደጋግሞ ከተወሰደ ቀስ በቀስ እየተቀየረ በመሄድ ሱስ በመሆን ኢኮኖሚያዊ ፣ የማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ለአዕምሮ ችግር፣ለሰዉነት እንቅስቃሴ እና ለመሳሰሉት ልያጋልጥ እንደሚችል በደንብ ማስገንዘብ አለቦት፡፡
- በመቀጠል በኬሚካሎች እና መድኃኒቶች ሱስ መያዝ የሚያመጣዉን ጉዳት ላይ በመጀመሪያ በጥንድ እንድወያዩ፤በኋላ ደግሞ በሙሉ ክፍል እንድወያዩ እና ለክፍሉ እንድያቀርቡ ዕድል ይስጡአቸዉ፡፡ እንድሁም በአከባቢ እድገት ላይ የሚያመጣዉን እንቅፋት በዉይይታቸዉ ህደት ዉስጥ ማንሳት እንድችሉ አስታዉሳቸዉ፡፡ በተጨማሪም በመልመጃ 5.4 ስር ባሉት ጥያቄዎች ላይ እንድወያዩ እና ለክፍሉ እንድያቀርቡሁኔታዎችን አመቻቹላቸዉ፡፡ እነሱ በሚያነሱት ሀሳብ ላይ በመመርኮዝ ዋና ዋና ነጥቦችን እና ማጠቃሊያ በመስጠት ለዚህ ርዕስ መጠቃሊያ ልትሰጡ ትችላለችሁ፡፡

### ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንድያዳብሩ መርዳት

ተማሪዎችን በቡድን በቡድን በመመደብ አሽሽ እና ትምባሆ በማጨስ ላይ ከተለያዩ አካላትን ላይ መረጃ በማሰባሰብ እንድያቀነጁ አድርጓቸዉ፡፡ ያሰባሰቡትን እና ያቀናጁትን መረጃዎች ለክፍሉ እንድያቀርቡ እና ሀሳብ እንድለዋወጡ አድርጓቸዉ፡፡ ስያቀርቡም በመከታተል መስተካከል የሚገባቸዉን ነገሮች ማስተካከል አስፈላጊ ነዉ፡፡

### ተከታታይ ምዝና

- ጥያቄዎችን፣ ተግባሮችን ፣ ያዘጋጃችሁትን የመልመጃ ጥያቄዎች ለተማሪዎቻችሁ የሰጣችሁት የቤት ስራ እና ጊዜዉን የጠበቀ ትክክለኛ ግብረ መልስ ስጡአቸዉ፡፡
- ተግባራትን፣ የመልመጃ ጥያቄዎችን እና በተሰጡት የመወያያ ነጥቦች ላይ ዉስንነት ያላቸዉ ተማሪዎች ካሉ በተለያዩ አከኋን ብቃታቸዉን እንድያሻሽሉ የማያቋርጥ ክትትል ማድረግ እና መርዳት አስፈላጊ ነዉ፡፡

- ተማሪዎቻችሁ የርዕሱን መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳብ ወይም የቀረበዉን ትምህርት መያዝ እንድችሉ አጫጭር ማስታወሻዎችን ስጡአቸዉ፡፡

**የተግባራት እና የመልመጃዎች መልስ**

**መልመጃ** 5.3

1. በአከባቢ ተጨባጭ ሁኔታ፤ ሳያስቡበት በስሜት፤የሚጠቀሙትን በማየት፤የጓደኛ ግፊት፤ ተስፋ መቁረጥ እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
2. ትምባሆ፣አሽሽ፣ አልኮል እና ጫት ልሆኑ ይችላሉ፡፡
3. በተለያዩ የእድሜ ክልል ዉስጥ የሚገኙ ሰዎች ልሆኑ ይችላሉ፡፡ ከብዙ ምክንያቶች ዉስጥ ጥቅቶቹ፡- ሰዓትን ማሳለፍ፣የጓደኛ ግፊት፤እንደ ዘመናዊነት መዉሰድ እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
4. የሰዉነታችን ዋና ዋና አካል የሆኑትን እንደ ልብ፣ሳምባ፣ጣፊያ እና ኩላሊት ይጎዳሉ፡፡ለካንሳር እና ለስኳር በሽታዎች ያጋልጣሉ፡፡ የሰዉነት ክብደት፣ በቤተሰብ እና የጓደኞች ግንኙነት እንድሁም በህብረተሰብ መካከል ያለዉን ግንኙነት ይቀንሳል፡፡ ብዙዉን ጊዜ አለመረጋጋት፣ መረበሽ፣መደበር፣ እንቅልፍ ማጣት፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ አቅም ማጣት፣እራሳቸዉን ማጥፋት፣ ወይም ለመሞት መመኘት፣ወንጀል እንደሰሩ መሰማት፣ ተስፋ ማጣት እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡**መልመጃ** 5.4

1. በተግባር 5.3 ስር የ4ኛን ጥያቄ መልስ ይመልከቱ
2. ጫት መቃም ያለዉ ጉዳት
    - የሰዉነት ሙቀት፣ የልብ ትርታ እና የደም ግፊት መጨመር
    - የምግብ ፍላጎት መቀነስ
    - እንቅልፍ ማጣት
    - ለረጅም ጊዜ ማዉረት ወይም ዝም ማለት እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

## 5.3 በአከባቢያችንጉዳትልያስከትሉየሚችሉጎጂልማዶች

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠዉ ክፍለ ጊዜ ……………………………………………….7

የዚህ ምዕራፍ የመማር ዉጤት

የዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡-

- በወረደ እና ዞን ዉስጥ ጉዳት ልያስከትሉ የሚችሉ ጎጂ ልማዶችን ይለያሉ፡፡

### ዋና ዋና ነጥቦች

በዚህ ርዕስ ዉስጥ በወረዳ እና ዞን ዉስጥ ጉዳት ልያስከትሉ የሚችሉ ጎጂ ልማዶች ላይ ይመረኮዛል

በዚህ ርዕስ ስር የቀረቡት ዋና ዋና ነጥቦች በሴት ልጅ ግርዛት፣የወተት ጥርስ መንቀል ፣ ያለ እድሜ ጋብቻ እና የሴት ልጅ መጥለፍ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህን ረዕስ ለማስተማር የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች እንደ ገለፃ፣ማሳየት፣ፕሮጀክት የቡድን እና የጥንድ ዉይይቶች፣ ሀሳብ ማመንጨት(brainstorm) እንድሁም የተለያዩ አቀራረቦችን መጠቀም ይቻላል፡፡

### ቅድመ ዝግጅት

መምህር/ት ይህን ርዕስ ከማስተማሩ/ሯ በፊት አስፈላጊዉን ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከሚያስፈልጉት ዝግጅቶቹ ዉስጥ አንዱ ጥልቀት ያለዉ የትምህርት ክፍለጊዜ እና የሚጠበቁ ብቃት ጋር ለመድረስ የሚያስችል ማዘጋጀት ነዉ፡፡ ይህን የክፍለጊዜ እቅድ ስታወጡ ከርዕሱ ጋር ግንኙነት ያላቸዉን መረጃዎች ከተማሪዎች መጽሃፍት እና በማምህሩ መምሪያ ላይ የተጠቀሱትን፣ተግባራት እና መልመጃዎችን በደንብ መረዳት አስፈለጊ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን የመጣቀሻ መጽሀፍትን በድንብ ማንበብ ያስፈልጋል፡፡ እንድሁም የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ከአከባቢ ከሚገኙት ነገሮች በማዘጋጀት እና በመጠቀም የሚጠበቀዉን ብቃት ለማሳካት መጣር አለባቸዉ፡፡

እንድሁም የተፈለገ ግብ ጋር ለመድረስ የህን ርዕስ ለማስተማር የሚረዱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ወይም ሌሎችን ቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

- የሴት ልጅ ግርዛትን የሚያሳይ ሥዕል
- ከሴት ልጅ ግርዛትን የሚመጡ ጉዳቶችን የሚያሳይ ሥዕል
- የወተት ጥርሰ መንቀልን የሚያሳይ ሥዕል
- ያለእድሜ ጋብቻ ያለዉን ጉዳት የሚያሳይ ሥዕል
- የሴት ልጅ መጠለፍ ያለዉን ጉዳት የሚያሳይ ሥዕል

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ጎጂ ልማዶች ማለት ምን ማለት እንደሆነ በመጠየቅ ጀምሩ፡፡ ጎጂ ልማዶች ትርጉም ካነሱ በኋላ ተጨማሪ ሀሳብ እና የማስተካከያ ሀሳብ በመስጠት ጎጂ ልማዶችን እንድዘረዝሩ አድርጓቸዉ፡፡ እንድዘረዝሩ የሚጠበቁት ነጥቦች በሴት ልጅ ግርዛት፣የወተት ጥርስ መንቀል ፣ያለ እድሜ ጋብቻ እና የሴት ልጅ መጠለፍ የሚሉትን እንድያነሱ ማበረታታት ነዉ፡፡
- በመቀጠል እያንዳንዱን ጉዳት የሚያደርሱ ጎጂ ልማዶች ላይ እንድወያዩ እና እርስ ለራሳቸዉ እንድያቀረቡ አድርጓቸዉ፡፡ በመጽሃፏቸዉ ቅደም ተከተል መሰረት እንድወያዩበት አድርጓቸዉ፡፡
- የሴት ልጅ ግርዛት ምንድን ነዉ? በሴቶች፣በቤተሰብ እና በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ምንድን ነዉ? በእነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች ቡድን በቡድን ሆነዉ ከተወያዩበት በኋላ የዉይይታቸዉን ዉጤት ለሁሉ ክፍል እንድያቀረቡ አድረጓቸዉ፡፡ እነሱ በቀረቡት ነጥብ ላይ በመነሳት የሴት ልጅ ግርዛት ያለዉን ጉዳት የሚያሳይ ሥዕል በመጠቀም ሰፊ ገለፃ አድርጉላቸዉ፡፡
- የወተት ጥርስ መንቀል ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና የሚያደርሰዉን ጉዳት ላይ ተማሪዎች ቤተሰቦቻቸዉን እና በአከባቢያቸዉ የሚገኙትን የጤና በለሙያዎች በመጠየቅ ሀሳባቸዉን እንድያቀናጁ አድርጓቸዉ፡፡ በቡድን ወይም በግል ያቀናጁትን ሀሳብ ለሙሉ ክፍል እንድያቀርቡ አድርጓቸዉ፡፡ ከሚያቀርቡት ሀሳብ በመነሳት የመርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሚያስፈልገዉን ገለፃ በመስጠት የትምህረቱን ይዘቶች መቋጨት ነዉ፡፡
- በተመሳሳይ መልኩ ያለእድሜ ጋብቻ እና የሴት ልጅ መጠለፍ ምን እንደሆኑ፣እንድሁም በግለሰቦች እና በህብረተሰቡ ላይ በሚያደርሱት ጉዳት ላይ ተማሪዎችን አምስት አምስት አባላት በማከፋፈል እንድወያዩበት አድረጉ፡፡ ተማሪዎች የዉይይት ዉጤታቸዉን ለሁሉም ክፍል እንድያቀርቡ አድርጓቸዉ፡፡ ከተማሪዎች ሪፖርት በመነሳት መጀመሪያ በተዘጋጀዉ መርጃ መሳሪያዎች በመጠቀም የሚያስፈልገዉን ገለፃ በመስጠት ማጠናቀቅ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንድያዳብሩ ማገዝ**

ተማሪዎችን ቡድን በቡድን በመመደብ በርዕሱ ስር ያሉትን የተለያዩ ነጥቦች ከተለያዩ አካላት መረጃ በማሰባሰብ እንድያቀነጁ አድርጓቸዉ፡፡ ያሰባሰቡትን መረጃዎች አቀናጅተዉ ለክፍላቸዉ አቅርበዉ ሀሳብ እንድለዋወጡበት አድርጓቸዉ፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ተማሪዎች ጥያቄዎችን፣ ተግባራት እና የተለያዩ ፕሮጀክቶች በዚህ ርዕስ ስር ያሉትን ሁሉ በግል ወይም በቡድን እንድሰሩ አድርጓቸዉ፡፡ ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን የሰሩትን በቅርበት በመከታተል እና አዎንታዊ ግብረ መልስ ስጡአቸዉ፡፡
- የተማሮዎችን ሥራ እየመዘኑ ለመሄድ የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች ለጥያቄዎቹ የሰጡትን መልሶች በመመልከት
- የተማሪዎችን ዉይይት በመከታታል
- የተማሪዎችን በሚያቀርቡበት ጊዜ በመከታታል
- የተማሪዎችን አቀራረብ እና አፈፃፀም በመመዝገብ
- ለተማሪዎች አፈፃፀም አዎንታዊ ግብረ መልስ በመስጠት

**መልሶች**

***መልመጃ 5.5***

1. በተለያዩ መሳሪያዎች እንደ ምላጭ፣ መንጠቆ፣የብርጭቆ ስብርባሪ እና በመሳሰሉት ይፈፀማል፡፡ይህም የረጅም እና የአጭር ጊዜ ጉዳቶችን ሊያስከትል ይችላል፡፡

   የአጭር ጊዜ ጉዳቶች፡-

   - ከፍተኛ ህመም
   - በመራቢያ አካለት ጎን ያሉት ህብረ ህዋስ መጎዳት
   - የደም መፍሰስ
   - ለተለያዩ በሽታዎች መጋለጥ

   የረጅም ጊዜ ጉዳቶች፡-

   - የሽንት ቧንቧዎች መበከልን ሊያመጣ ይችላል
   - በወሊድ ጊዜ መቸገር
   - ለመሽናት መቸገር
   - የወር አበባን ለማስወጣት መቸገር
   - ለፌስቱላ በሽታ መጋለጥ
2. የሴት ልጅ ግርዛት ብዙዉን ጊዜ የጤና ሙያ በሌላቸዉ ሰዎች ይካሄዳል፡፡

**ተግባር 5.1**

1. በምታስተምሩበት ወረዳየሴት ልጅ ግርዛት መኖሩን እና አለመኖሩን የጤና ተቋማትን ወይም የሚመለከተዉን አካል መጠየቅ ይጠበቅቦታል፡፡
2. የሚካሄድ ከሆነ በየትኛዉ እድሜ ክልል እንደሚካሄድ መመዘን አስፈለጊ ነዉ፡፡
3. የህዝቡን ሀሳብ በመጠየቅ ማቀናጀት ነዉ፡፡

**መልመጃ 5.6**

1. ጉዳት የሚያመጡ ጎጂ ልማዶች፡-የሴት ልጂ ግርዛት፣ ያለእድሜ ጋብቻ ፣ አስገድዶ መድፈር እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
2. በወረዳ እና ዞን ዉስጥ የሚገኙትን ልማዶች እንድጠቅሱ ማድረግ፡፡
3. በአንዳንድ ሁኔታ ጉዳት የሚያመጡ ልማዶች መግለጫ በተማሪዎች መፅሃፍት ዉስጥ የተሰጡትን መመልከት
4. ጉዳት የሚያመጡ ልማዶች በግለሰብ እና በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት አለዉ፡፡ በግለሰብ ላይ የጤና ፣ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚ እና አእምሮአዊ ችግሮችን ልያስከትሉ ይችላሉ፡፡

## 5.4 ድርቅእናረሃብ

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠዉ ክፍለ ጊዜ ……………………………..8

የዚህ ምዕራፍ የመማር ዉጤት

የዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡-

- የድርቅ እና የረሃብን ፅንሰ ሀሳብ ይገልፃሉ፡፡
- በኢትዮጵያ ለሚከሰተዉ ድርቅ ምክንያት የሆኑትን ይገልፃሉ፡፡
- የኢትዮጵያን የዝናብ ካርታን በመጠቀም ደረቅ ቦታዎችን በማመልከት ይገልፃሉ፡፡
- የዝናብን ዳታ በመራጃ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ማሳየት ይችላሉ፡፡
- በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙትን ደረቃማ ቦታዎች ይለያሉ፡፡
- ድርቅ የግድ ለረሃብ ምክንያት መሆን እንደማይችል ይገልፃሉ፡፡
- ኢትዮጲያ ዉስጥ ያለዉን ድርቅ ለመከላከል የሀገር ዉስጥ ባህላዊ ዘዴዎች ያለቸዉን ሚና ይዘረዝራሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ ርዕስ ስር የድርቅ እና የረሃብን ፅንሰ ሀሳብን፤ በኢትዮጵያ ለሚከሰተዉ ድርቅ ምክንያቶች፤ የኢትዮጵያን ዝናብ እና ደረቅ ቦታዎችን ግንኙነት፤ በኢትዮጵያ ዉስጥ

የሚገኙትን ደረቃማ ቦታዎችን እና ድርቅ የግድ ለረሃብ ምክንያት መሆን እንደማይችል መሆኑን በአጠቃላይ መማር አለባቸዉ፡፡ ይህንንም ርዕስ ለማስተማር ስምንት ክፍለጊዜዎች ተሰጥተዋል፡፡ በተሰጠዉ ክፍለ ጊዜ ዉስጥ ተማሪዎች መጎናፀም የሚገባቸዉን ብቃት እንድጎናፃፉ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም እና የተለያዩ የመርጃ መሳሪያዎች መጠቀም አስፈለጊ ነዉ፡፡ ይህንን ርዕስ ለማስተማር የሚዉሉ የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች መካከል ጥቅቶቹ፡-የቡድን ዉይይት፣ የጥንድ ዉይይት፣የችገር መፍቻ ዘዴ፣አጭር ገለፃ እና ለትምህርቱ ይዜት ይመቻል የሚትሉትን ሌሎች ዘዴዎችን ተጠቀሙ፡፡

በዚህ ርዕስ ዉስጥ ተማሪዎች፡- ድርቅ የሚንለዉ በአንድ ቦታ ለረጅም ጊዜ ዝናብ ስጠፋ የሚፈጠር ነዉ፡፡ ረሃብ የሚንለዉ ደግሞ ድርቅ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ከሆነ እና ህይወት ያለቸዉ ነገሮች የሚበሉትን እና የሚጠጡትን በማጣት የሚፈጠር ነዉ፡፡

ለረሃብ ድርቅ በቻዉን ሰበብ ልሆን እንዳማይችል እና ረሃብ በቂ ምርት በለመገኘቱ ልፈጠር እንደሚችል መማር አለባቸዉ፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

መምህር/ት ይህን ርዕስ ከማስተማሩ/ሯ በፊት አስፈለጊዉን ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከሚያስፈልጉት ዝግጅቶቹ ዉስጥ አንዱ ጥልቀት ያለዉ የትምህርት ክፍለጊዜ ማዘጋጀት ነዉ፡፡ ለተሰጡት ስምንቱም የትምህርት ክፈለጊዜ ማዘጋጀት አስፈለጊ መሆኑ ግልፅ ነዉ፡፡ ለእያንዳንዱ ክፍለጊዜ እቅድ ስታወጡ ከርዕሱ ጋር ግንኙነት ያላቸዉን መረጃዎች ከተማሪዎች መጽሃፍት እና በማምህሩ መምሪያ ላይ የተጠቀሱትን፣ተግባራት እና መልመጃዎችን በደንብ መረዳት አስፈለጊ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን የመጣቀሻ መጽሀፍትን በድንብ ማንበብ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም፡-

- በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ስጋት የሆኑ ነገሮችን ለማወቅ ወቅታዊ ፅሁፎችን በማንበብ እና የተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን በማዳመጥ ሀገራችንን እያስጨንቁ ያሉትን ከእነዚ ምንጮች በማሰባሰብ ግንዛቤን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡
- በዚህ ርዕስ ላይ በቂ ግንዛቤ ለማግኘት በከፍተኛ ጥራት የተዘጋጁትን የተለያዩ የመጣቀሻ መጽሃፍት በማንበብ ግንዛበዎን ያዳብሩ፡፡
- የሀገራችንን የድርቅ ክስተት የሚያሳዩትን መረጃዎች በማሰባሰብ አቀናጁ፡፡
- ከመቶ አመት ወድህ ድርቅ በሀገራችን ላይ ያስከተለዉን ተፅኖ በማጥናት ተዘጋጅ፡፡
- በድርቅ መከሰት ምክንያት በሀገራችን የተከሰተዉን ረሃብ በመለየት ያስታዉሱ፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ይህንን ርዕስ ለማስተማር በመጀመሪያ ተማሪዎች ስለ ድርቅ እና ረሃብ ምን እንደሚያዉቁ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ለይ፡፡ በመቀጠል ከተማሪዎች መልሶቻቸዉን ከተቀበሉ በኋላ ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ የድርቅ ምክንያቶች እና ተፅዕኖ ላይ እንድወያዩ አድርጓቸዉ፡፡

በስተመጨራሻም ትክክለኛ አቅጣጫ በማስያዝ በተጨማሪ ድርቅ ማለት በአንድ ቦታ ለረጅም ጊዜ ዝናብ ስጠፋ የሚፈጠር መሆኑን እና ረሃብ የሚንለዉ ደግሞ ድርቅ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ከሆነ እና ህይወት ያለቸዉ ነገሮች የሚበሉትን እና የሚጠጡትን በማጣት የሚፈጠር መሆኑን ገለፃ አድርግላቸዉ፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ እንደ ማሳሰቢያ ለተማሪዎች መነገር የሚገባቸዉ ድርቅ ብቻዉን ለረሃብ ምክንያት እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ረሃብ በቂ ምርት በለመኖሩ ልፈጠር የሚችል መሆኑን አጠንክረዉ መስገንዘብ አለቦት፡፡

ተማሪዎች በካርታ ላይ በቂ ዝናብ ባላቸዉ ቦታዎች ድርቅ እንደሌለ እና ጥቂት ዝናብ ባላቸዉ ደግሞ ድርቅ እንደሚበዛባቸዉ እንድጎበኙ እና እንድያቀርቡ ማድረግ አለቦት፡፡እንድሁም ተማሪዎች የኢትዮጵያን ካርታ በመጠቀም በኢትዮጵያ ዉስጥ በአንፃራዊነት ድርቅ ያለባቸዉን ቦታዎች እንድያሳዩ አሳትፏቸዉ፡፡ ተማሪዎች ሥራዎቻቸዉን ለሙሉ ክፍል እንድያቀርቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና በመጨረሻም ትክክለኛ አቅጣጫን ለማስያዝ ተጨማሪ ገለፃ ስጡአቸዉ፡፡

በኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉትን ደረቃማ ቦታዎች ሥዕል ስለዉ እንድያሳዩ የሙከራ ፈተና ስጡአቸዉ፡፡ በመቀጠልም የሙከራ ፈተናቸዉን ገለፃ እንድያደርጉ እድል ስጡአቸዉ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች በኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉትን ደረቃማ ቦታዎች ለመገገም የሚዉሉትን ዘዴዎች እንድጎበኙ እና እንድመዘግቡ በመጋበዝ ተጨማሪ ሀሳብ በመስጠት ትክክለኛዉን አቅጣጫ ያስዙ፡፡

### ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንድያዳብሩ ማገዝ

የዚህ ትምህርት ይዘቶች ችግርን በመቅረፍ መልኩ ፈጠራን ማበረታታት በሚችሉት አከኋን ተማሪዎች ከፍተኛ ተሳትፎ የማግኘት እድል እንድያገኙ በማድረግ የተለየ ተሰጥኦ እና ችሎታ ያለቸዉ ተማሪዎች በራሳቸዉ ተነሳሽነት የሀገራችን የድርቅ ሁኔታ ምን እንደምመስል፣ ለኢትዮጵያ ድርቅ ምክንያት እና ችግሮቹን፣ የዝናብ እና

የደረቃማ ቦታዎች ግንኙነት በኢትዮጵያ፤ድርቅ በብዛት በሚያጠቃቸዉ ቦታዎች ላይ ምርምር እና ጥናት ማካሄድ እና በራሳቸዉ ፈጠራ መፍትሄ እንድሰጡ ማበረታታት፡፡

### ተከታታይ ምዘና

ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ሥር የሉትን ዋና ዋና ነጥቦች እና የሚፈለገዉን ብቃት መጎናፃፋቸዉን በርዕሱ ዓላማ ላይ በመመርኮዝ አንድ አንድ ጥያቄዎችን በማንሳት በክፍል ዉስጥ መጠየቅ እና ግብረ መልስ መስጠት ይጠበቅቦታል፡፡

ለምሳሌ፡-

- የድርቅ እና የረሃብን ፅንሰ ሀሳብን መለያቸዉን መጠየቅ
- በኢትዮጵያ ለሚከሰተዉ ድርቅ ምክንያት የሆኑትን እንድገልፁ በማድረግ
- የዝናብን ዳታ የመራጃ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ማሳየት መቻላቸዉን በመጠየቅ
- በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙትን ደረቃማ ቦታዎች እንድዘረዝሩ በማድረግ

በተጨማሪም በዚህ ርዕስ ስር ዉይይት እና ተማሪዎች በሚያከናወኑት ተግባራት ላይ ትኩረት በመስጠት ተማሪዎች ምን ያህል እንደተገነዘቡ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋግጡ፡፡

### መልሶች

### የምዕራፍ አምስት መልመጃዎች

I. **እዉነት/ሀሰት**

1. እዉነት  3. እዉነት  5. ሀሰት  7. እዉነት
2. ሀሰት  4. እዉነት  6. ሀሰት

II. **ምርጫ**

1. መ  2. ሀ  3. ሀ  4. ሐ  5. ሀ  6. መ

III. **አጭር መልስ**

1. **የተሰጠዉ መልስ**
   - ለዚያ ቦታ ዉሃ እንዴት ማድረስ እንዳለበት ላይ መስራት
   - የእንስሳትን መኖ አስቀድመዉ ማዘጋጀት
   - ዉሃን ከምድረ ከርስ ቆፍሮ ማዉጣት
   - በዚያ አከባቢ እፅዋትን መትከል
   - ከተቻለ በዉሃ ቧንቧ በመታገዝ አከባቢዉን ማጠጣት

- ድርቅን የሚቋቋሙ ተክሎች መትከል

2. በሱማሌ፣ በቦረና ፣በአፋር፣ በሰሜን ወሎ፣ በደቡብ እና ምስራቅ ትግራይ አከባቢዎች

3. **የተሰጠዉ መልስ**
   - የዚያ አከባቢ እፅዋት ይጠፋሉ
   - የዉሃ ምንጮች ይደርቃሉ፤ያሉትም ይበከላሉ
   - የዱር እንስሳት ይሞታሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ይሰደዳሉ
   - አፈር በንፋስ ይወሰዳል
   - በንፅህና ጉድለት በሽታ ልስፋፋ ይችላል፡፡

# የአካባቢ ሳይንስ መርሃ ትምህርት

# 5ኛ ክፍል

# የአምስተኛ ክፍል፡ አካባቢ ሳይንስ መርሀ ግብር

## የመማር ግብ

ግብ፣አላማ፣ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት፣ አካታችነት፣ ፍልስፍና፣የትምህርቱ መምሪ (አካባቢ፣ሀገር እና አለም አቀፍ)፣ ከ1977 የቲቢሊ አዋጅ የተወሰደ ነው።

## እነዚህ ግቦች፤

1.የከተማና ገጠር ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖሎቶካዊ ትስስር እና የአርኪኦሎጂ ግንዛቤ ማጠናከር።

2. ተማሪዎች የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ላይ ያላቸውን አመለካከት፣ ስነምግባር አስፈላጊ የሆነ ግንዛቤ እንዲገኙ ማድረግ።

3. የአከበቢ ጥበቃ ላይ የሕብረተሰቡ አመለካከት ላይ ለውጥ ማምጣት።

## የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት አላማ፣ (The categoriesof environmental education objectives are)

**ግንዛቤ፡-** የተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎችና ግለሰቦች የአከበቢ ጥበቃና የአከበቢ ላይ ጠቅላላ ኃለፊነትና ግንዛቤ እንዲያደብሩ ማድረግ፤

**ዕውቀት-** የተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎችና ግለሰቦች የአከበቢ ጥበቃና የአከበቢ ላይ የተለያዩ ልምዶችና መሰረታዊ ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ማድረግ፤ አመለካከት-የተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎችና ግለሰቦች የአከበቢ ጥበቃና የአከበቢ ላይ ኃለፊነት በተነሳሽነት እንክብካቤና ጥበቃ ማድረግ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፤

**ብቃት-** የተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎችና ግለሰቦች የአከበቢ ጉዳት የሚያስከትሉ ነገሮችን በመለየት መፍትሄ መስጠት ላይ ዕውቀት እንዲያገኙ መርዳት ፤

**ተሳትፎ-** የተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎችና ግለሰቦች የአከበቢ ችግሮችን ለመፍታት ዕድል እንደያገኙ ማድረግ

## የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት አላማ

የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ባስቀመጠው አቅጣጫ ይህን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኃላ በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪው/ዋ፤

- በአከበቢ ጉዳዮች ላይ ተጨባጭ ግንዛቤ ከአኗኗራቸው ሁኔታ ላይ በመመስረት ይኖረዋል/ታል፡፡
- በአከበቢ ጉዳዮች ላይ በተፈጥሮ ያላቸውን ግንዛቤና የፈጠራ ችሎታ ታጎለብታለህ/ሽ፤
- በአከበቢ ላይ ያለህን/ሽን የተለያዩ እውቀቶችን ታጎለብታለህ/ሽ፤
- በተፈጥሮ ሀብት፣ቅሳካላትና የሰው ልጅ ላይ ያለችሁተ ጠያቂነትና ኃላፊነት ታጎለብታለህ/ሽ፤
- ስለ እኩልነት፣ ፍትሃዊነት፣የሰውልጅ መብቶች መከበር ታነሳለህ/ሽ፡፡

| 5ኛ ክፍል:ምዕራፍ 1 | 5ኛ ክፍል:ምዕራፍ 1<br>1.የኢትዮጵያ መገኛ<br>( የክፍለ ጊዜ 42) | የማር ማስተማር ዘዴ | ተከታታይ ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ካርታን መጠቀም የሰዎች የመገናኘት ፍላጎት ይኖረዋ፤<br>• ስለ አንጻራዊና ፍፁማ መገኛ ትወያያላችሁ፤<br>• ስለ አንጻራዊ የኢትዮጵያ መገኛ ያሳያሉ፤<br>• ስለ ፍፁማ /አስትሮኖሚያዊ / የኢትዮጵያ መገኛ ያሳያሉ፤<br>• በኢትዮጵያ ካርታ ላይ የኬክሮስ ናየኬንትሮስ መስመር በመጠቀም የተለያዩ አካባቢዎችን አቅጣጫ ያሳያሉ፤<br>• ጂፒኤስ (GPS)፣ የጎግል ካርታና የመሬት ካርታን በመጠቀም(GPS, Google | መገኛ<br>▪ የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገሮችን አንጻራዊና ፍፁማ መገኛ በማስተያየት የኢትዮጵያ መገኛ በካርታ ላይ<br>▪ የኢትዮጵያየተለያዩ አካባቢዎችን መገኛና አቅጣጫ ለማነስት ጂፒኤስ ‘GPS’ መጠቀም | ▪ ተማሪዎች ስለ የኬክሮስ ናየኬንትሮስ መስመሮች የሚያውቁትን መጠየቅ<br>▪ ተማሪዎች ሁለት ሁለት ወይም በቡድን በመሆን የኢትዮጵያ መገኛ ላ ይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>▪ ተማሪዎች ስለ አንጻራዊ የኢትዮጵያ መገኛ እንዲገልፁ ማድረግ<br>▪ ተማሪዎች የአለምን ካርታ በመጠቅም የኢትዮጵያን ፍፁማመገኛ እንዲገልፁ ማድረግ<br>▪ ባለ አራትና ስድስት መስመር ግሪድ በመጠቀም የአንድን አካባቢዎች መገኛ በካረታ ላይ እንዲያሳዩ ሁነየታዎችን ማመቻቸት | ▪ ለተጠየቁት ይያቄዎች የሰጡትን ግብረ መልስ መመልከት<br>▪ ተማሪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ተለያዩ ቦታዎች መገኛ ማፈለግ ላይ ደረጉትን መከታተል<br>▪ ተማሪዎች በቡድን በሚወያዩበት ወቅት ክትትል በማድረግ<br>▪ ተማሪዎች ሀሳብ በሚሰጡበት ወቅት ክትትል በማድረግ<br>▪ ተማሪዎች የተለያዩ ክንውን በሚያደርጉበት ወቅት ክትትል በማድረግ<br>▪ ተማሪዎች ዘገባ መመዝገብ ክትትል በማድረግ<br>▪ ጂፒኤስ (GPS)፣ የጎግል ካርታና የመሬት ካርታን በመጠቀም ላይ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| map and Google earth ) በመጠቀምየ ተለያዩ አካባቢዎችን(ቦታዎችን) የመለካትና የመመዝገብ ችሎታ ያሳድጋሉ፤<br>• ቀላል ካርታን በማዘጋጀት ፍፁማ /አስትሮኖሚያዊ / የኢትዮጵያ መገኛ ያሳያሉ፤<br>• የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገሮችን ስማቸውን ይናገራሉ፤<br>• | | ▪ ተማሪዎች የአለምን ካርታ በመጠቅም የኢትዮጵያን አንጻራዊመገኛ እንዲገልፁ ማድረግ<br>▪ ተማሪዎች ጂፒኤስ (GPS) ፣ የካርታ ጎግል እና የመሬት ጎግል በመጠቀም የአንድን አካባቢ አቅጣጫ በመለካትና በመስፈር እንዲመዘግቡ ማድረግ<br>▪ ተማሪዎች የጎረበቤት ሀገሮችን ቅጣጫ፣ መገኛ እና ርቀት እንዲፈልጉ የቤት ስራ መስጠት | ተማሪዎች መከታተል፤<br>▪ እያንዳንዱን የተማሪዎች ተግባር በመከታተል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት፤<br>▪ ተከታታይ ምዘና መስተት ለምሳሌ የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገሮችን የሚያሰይ ካርታ እስኬች ስሰሩ መከታተል |

| 5ኛ ክፍል:ምዕራፍ 2 | 5ኛ ክፍል:ምዕራፍ 2<br>2. ስርአተ ልመት<br>( የክፍለ ጊዜ 54) | የማር ማስተማር ዘዴ | ተከታታይ ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የስርአተ ልመት ክፍሎቸ ስሞችን ና ተግባራቸውን | • 2.1. ዋና ዋና የሰው ስርአተ ልመት ክፍሎቸ<br>• የስርአተ ልመት | • ተማሪዎችየሰው ስርአተ ልመት ክፍሎቸ ላይ በሚወያዩበት ወቅት ክትትል ማድረግ | • ተማሪዎች የሰው ስርአተ ልመት ክፍሎቸ ላይ በሚወያዩበት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መግለጽ<br>• የስርአተ ልመት ክፍሎቸ ጥቅማቸውን መግለጽ<br>• ውሃን ከኮመፓውንደ መለየት<br>• ውሃን ትቅሞች ይዘረዝራሉ<br>• መጠም፣ ርዝመት፣ ይዘት፣ ጊዜ እና የመሳሰሉትን መለካት ይለማመዳሉ<br>• የኃይል ምንጭና ትቅሞች ይዘረዝራሉ ለምሳሌ ምግብ፣ ነዳጅ፣ የፀሀይ ብርሀንን ያብራራሉ<br>• የተለያዩ ደምጽ አስተላለፊ ነገሮችን | ትርጉምአፍ፣ምላስ አይሶፋገስ እና ጨጓራ፣ ትልቁ አንጀት፣ ትንሹ አንጀት<br>• የስርአተ ልመት ጥቅማችው<br>2.2. ውሃ ትቅሞች<br>• ውሃን ትርጉም<br>• ፎረሙላ ($H_2O$)<br>• ውሃ ሕይወት ላላቸው ሁሉ የሚሰጠው ትቅሞች<br>2.3. ልኬት<br>መጠም፣ ርዝመት፣ ይዘት፣ ጊዜ፣ ቴምፐሬቸር እና የመሳሰሉት። | • ተማሪዎች የሰው ስርአተ ልመት ክፍሎች ሥዕል እንዲስሉ ማድረግነ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያሳዩ ማድረግ ና ከትምርት ማርጃ መሳሪያ ጋር እንዲያነጻጽሩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች የሰው ስርአተ ልመት ክፍሎች ጥቅም እንዲገልጹ ማድረግ<br>• ተማሪዎች በቡድን በመከፈል በአካባቢቸው የሚገኝ የውሃ ጥቅም<br>• (ለምሳሌ ውሃ ኤለመንቶች እንደ H ና O = $H_2O$) እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ለማስኖ ፤<br>• ለምግብ ዝግጅት፤<br>• ለሕይወት ላቸው በመሉ እንዲኖሩ ለማድረግ፣ ለመጓጓዛ፣ ኃይል ለማመንጨት… ውሃ ስፈላጊ | ወቅትበአይን ክትትል ማድረግ<br>• ተማሪዎች ሀሳብ እንድለዋወጡ በማድረግ ለሚቀጥለው እራሳቸውን እንዲያሻሽሉ ማበረታታት፤<br>• ሞዴሎችን፣ ሥዕሎችን፣ዲያግረሞችነ ተማሪዎችን የሚጠቅም ምልከታ ማካሄድ፤<br>• የተማሪዎችን ክንውን እየመዘገቡ መሄድ<br>• የተማሪዎችን ክንውን ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ታብራራላችሁ<br>• | 2.4.የኃይል ምንጭ<br>• የኃይል ትርጉም<br>• የተለያዩየኃይል ምንጮች<br>2.5. ደምጽ<br>• የደምጽ ትርጉም<br>• የደምጽ አይነቶች<br>• ደምጽ አስተላለፊ | ነው።<br>• ተማሪዎች በቡድን በመከፈል መጠም፣ ርዝመት፣ ይዘት፣ ጊዜ፣ (ለምሳሌ የክፍላቸው ርዝመት ፣ የቦርሳቸው ክብደት እና የመሳሰሉ) በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን እንዲለኩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች የተለያዩ የሀይል ምንጮችን( ምግብ፣ ከሰል፣ እንጨት፣የፀሀይ ብርሃን፣ ንፋስ፣ ነዳጅ፣ጂኦተርማር)ላይ ገኛሉ።<br>ደምጽ<br>• ተማሪዎችየደምጽ አይነቶች ና ደምጽ አስተላለፊ (ፈሳሽ፣ጠጣር እና ጋዝ) እንዲዘረዝሩ ማድረግ | |

| 5ኛ ክፍል:ምዕራፍ 3 | 5ኛ ክፍል:ምዕራፍ 3<br>3.የኢትዮጵያ የተፈጠሮ ሀብት<br>( የክፍለ ጊዜ 54) | የማር ማስተማር ዘዴ | ተከታታይ ምዘና |
| --- | --- | --- | --- |
| • የኢትዮጵያ አየር ንብረትና የአየር ፀባይ ልዩነት ይገልፃሉ<br>• ቴምፐሬቸርን የመለካትና የመመዝገብ እንዲሁም የዝናብ መረጃን የመመዝገብ ብቃት የጎለብታሉ፤<br>• የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ከትሮፒክ አካባቢ ሀገሮች የመለየት ምክንያቶችን ያገናዝባሉ፤<br>• ዋና ዋና የኢትዮጵያ አየር ንብረት መቆጣጠረየዎችን | 3.1. የኢትዮጵያ የአየር ንብረት<br>• አየር ንብረትና የአየር ፀባይ ልዩነት<br>• የአየር ንብረት ይዘት<br>• አየር ንብረት ዞኖች<br>• አየር ንብረት ዞኖች<br>• መቆጣጠሪያ<br>• የኢትዮጵያ የአየር ንብረት<br>• አይነቶች<br>3.2 የኢትዮጵያ የተፈጠሮ ሀብት<br>• የኢትዮጵያ የተፈጠሮ ሀብት አይነቶች<br>• የኢትዮጵያ አፈር መሸርሸር ምክንያቶች | • ለተማሪዎች ስለ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት እንዲደንቁ መጠየቅ፤<br>• ተማሪዎች በጥያቄና መልስ ማልክ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀበት እንዲለዩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች በቡድን በመደራጀትየኢትዮጵያ አፈር መሸርሸር ምክንያት ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች የኢትዮጵያ የዕጸዋትን ትስስር (vegetation belt)በካርታ ላይ እንዲሳዩ ማድረግ<br>• | • ተማሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄመልስ መስጠታቸውን መልከት<br>• በአየር ንብረትና የአየር ፀባይ ልዩነት ላይ የተሰጡትን ሙከራ ጥቄዎች መከታተል<br>• የተማሪዎችን ተገባር መከታተል ለምንሳሌ ቴምፐሬቸርን የመለካትና የመመዝገብ እንዲሁም የዝናብ መረጃን የመመዝገብና ማንበብ.<br>• ቴምፐሬቸርን የመለካትና የዝናብ መረጃን የመመዝገብ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይለያሉ፤<br>• የኢትዮጵያ የተፈጠሮ ሀብት አይነቶች ይለያሉ፤<br>• የአፈር መሸርሸርና የአፈር አይነቶችን ይገልፃሉ<br>• በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠሮ. ሀብት እንክብካቤ፡ና የደን ምንጣሮን ይገልፃሉ<br>• ውሃን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚቻል ይገልፃሉ<br>• የኢትዮጵያ ውሃ የሚጎዱ ዋና ዋና ምክንያቶችን ይዘረዝራሉ፤<br>• የኢትዮጵያ ወንዞች እና ሀይቆች የተፋሰስ ስርአት ጥናት ያካሄዳሉ | • የኢትዮጵያ አትክልትና ፍራርሬ አይነቶችን<br>• በኢትዮጵያ የደን ምንጣሮን ምክንያቶች<br>• በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠሮ. ሀብት እንክብካቤ አይነቶች<br>• የተፈጠሮ. ሀብት እንክብካቤና የአፈር አይነቶች ላይ የህብረተሰቡ ያለው ግንዛበ<br>• የኢትዮጵያ ውሃ ስራ ላይ የማዋል ሆኔታዎች<br>• የኢትዮጵያ ውሃ የሚጎዱ ዋና ዋና ምክንያቶችን<br>• የኢትዮጵያ ወንዞች እና ሀይቆች የተፋሰስ ስርአት ጥናት<br>• የኢትዮጵያ የሀይቆች አይነትና ባህሪያቸው | •<br>• ተማሪዎች የደን መመንጠር ምክንያቶች ምሳሌ በመጥቀስ እንዲገልፁ ማድረግ<br>• የተለያዩ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የእንክብካቤ ትግበራ ላይ ተማሪዎች<br>• በጥያቄና መልስ መልኩ በማከሄድ የራሳቸውን አመለካከት እንዲኖራቸው በማድረግ መገምገም እንዲሁም የኢትዮጵያ ውሃ ሀብት አግባቡ የ ሆነ አጠቃቀምን እንዲለዩ ማድረግ፤<br>• ተማሪዎች የኢትዮጵያ ውሃ ሀብት የሚጎዱ ዋና ዋና | ስልቶችን ለተማሪዎች ማሳየት<br>• ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ ለተማሪዎች መስጠት .<br>• የተማሪዎችን ዘገና በማረጋገጥ ገንቢ የሆነ ግብረ ግብረ መልስ ለተማሪዎች መስጠት<br>• ተከታታይ ምዘና ማካሄድ<br>• ተማሪዎች ስለ የተፈጠሮ. ሀብት መልስ ሲሰጡ መከታተል<br>• የተማሪዎችን ተነሳሽነት ላማበረታታትና ለማብቃት ገንቢ ሀሳቦችን መስጠት<br>• ተማሪዎች ለወደፊቱ እራሳቸውን እንዲያሻሽሉ ማበረታታት. |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • የኢትዮጵያ ማዕድናት አጠቃቀምና በአካባቢ ላይ ያስከተሉት ጉዳቶች ላይ ጥልቅ የሆነ ጥናት ያካሄዳሉ<br>• የዱር አራዊቶችን የሚጎዱ ዋና ዋና ምክንያቶችን ይገልፃሉ፤<br>• ዋና ዋና የኢትዮጵያ የኃይል ምንጮችን ይዘረዝራሉ<br>• ታዳሽ የኃይል ምንጮችን ከማታደስ የኃይል ምንጮችን ይለያሉ<br>• ዋና ዋና የኢትዮጵያ አካባቢ ችግሮችን ይዘረዝራሉ<br>• ዋና ዋና የኢትዮጵያ አካባቢ የመበከል ምክንያቶች ላይ ወያሉ | • የኢትዮጵያ ዋና ዋና የወንዞች አይነት<br>• የኢትዮጵያ የማዕድን ሀብት<br>• የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም<br>• የኢትዮጵያ ማዕድናት አጠቃቀምና በአካባቢ ላይ ያስከተሉት ጉዳቶች<br>• የኢትዮጵያ የዱርአራዊቶች<br>• በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ የዱርአራዊቶች<br>• የኢትዮጵያ የዱርአራዊቶች የሚቀንሱ ምክንያቶች<br>• ተጋላጭ የሆኑ የኢትዮጵያ የዱርአራዊቶች<br>• የኢትዮጵያ አየር ንብረትና የአየር ፀባይ ባህሪያት<br>• ዋና ዋና የኢትዮጵያ | ምክንያቶችን ላይ እንዲገልፁ መጠየቅ<br>• ተማሪዎች በቡድን በመካፋፋል የኢትዮጵያ ሀይቆችና ወንዞች<br>• ባህሪያትይዘረዝራሉ።<br>• ተማሪዎችየኢትዮጵያ ሀይቆችና ወንዞች ባህሪያት መግባባታቸውን ማስገንዘብ<br>• ተማሪዎች የኢትዮጵያ የማዕድን ሀብት አይነቶችነ እንዲዘረዝሩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች በቡድን እንዲደራጁ በማድረግ የኢትዮጵያ የማዕድን ሀብት እንዴት ስራ ላይ እነደሚውል መተየቅ<br>• ተማሪዎች የዱርአራዊቶች፣ | • የዕለቱን ትምህርት ከመማራቸው በፊት ከባለፈው ክፊለጊዜ ትምህርት አጫጭርጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• ግብረ መልስን በመመዝገብ ተማሪዎች የተሰጣቸው ትምህርት ካልገባቸው በድጋሜ ገለፃ ማድረግ<br>• የሚሰጠው ገለፃ በሥእል፣ በዲያግራምና ወዘተ የተደገፈ ይሁን<br>• እያንዳንዱን ተማቷ በትኩረት ክትትል እክብካቤ እየተደረገ መሆኑን ማሳወቅ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የኃይል ምንጭ አይነቶች<br>•<br>• የኢትዮጵያ ታዳሽ የሆነ የኃይል ምንጮችና ታዳሽ ያልሆኑ የኃይል ምንጮች ባህርይ<br>• ዋና ዋና የኢትዮጵያ አካባቢ የመበከል ምክንያቶች (Major environmental problem of Ethiopia)<br>• የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም እንክብካቤ ትግበራ | አእዋፍ፣ የቤት እንስሳትንና ባህሪያቸውን እንዲያብራሩ ማድረግ<br>•<br>• የዱርአራዊቶች የሚጎዱ ምክንያቶችን በትያቄና መልስ መልኩ እንዲገልጹ ማድረግ<br>• ተማሪዎችበቡድን በመደራጀት ስለ አየር ንብረት፣የሙንሱን አየር ንብረት ፣የአየር ይዘት እና ስለ አየር ንብረት ለውጥግዳትና መፍትሀሄ እንዲዘረዝሩ ማድረግ<br>• የኢትዮጵያ የኃይል ምንጭ አይነቶች ሃሰብ እነዲለዋወጡ ማድረግ<br>• የኢትዮጵያ ታዳሽ የሆነ | • ለተማሪዎች መልሰ በሚመለስበትና ሀሳብ በሚሰትበት ወቅት የተማሪዎችን መመልከት<br>• ተማሪዎች ውይይት በሚያደርጉበት ወቅት<br>• ያመጡትን ለውት መመዝገብ<br>• ተማሪዎች በቡድን ውይይት ሲያደርጉበት በመከታተል መመዝገብ<br>• በተማሪዎች የሚነሱትን ጥያቄዎችና ሀሳቦች መስፋፋት<br>• ተማሪዎች ውይይት በሚያደርጉበት ወቅት ክትትል ማድረግ<br>• ተማሪዎች ገላፃ በመመዝገብ ወዲያውኑ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | የኃይል ምንጮችና ታዳሽ ያልሆኑ የኃይል ምንጮች ይለያሉ<br>• ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ከኢትዮጵያ የኃይልምንጮች ውስጥ ታዳሽ የሆነና ታዳሽ ያልሆኑ የኃይል ምንጮችማለት መግለፅ፤<br>• ተማሪዎች የኢትዮጵያ አካባቢ የመበከል ዋና ዋና ምክንያቶች (Major environmental problem of Ethiopia)ና መፍትሀሄው ላይ ጥቂና መልስ እንዲያደርጉ ማድረግ | ግብረ መልስ መስጠት<br>• ለ ተማሪዎች ተግባር ገንቢ ሆነ ግብረ መልስ መስጠት<br>• ተማሪዎች በሰጡት መልስ ላይ በመመስረት የተሸለ እንዲሰሩ ገንቢ ሀሳብ ምጠት<br>• ግልፅ በመሆን ተማሪዎችን ለመርዳት መዘገጀት |

| 5ኛ ክፍል:ምዕራፍ 4 | 5ኛ ክፍል: ምዕራፍ 4<br>4. የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ<br>( የክፍለ ጊዜ 54) | የማር ማስተማር ዘዴ | ተከታታይ ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ለያዩ የኢትዮጵያ ባህሎችን ያከብራሉ፤<br>• ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ በህሎችን ይለያሉ ፤<br>• ኢትዮጵያ የተለያዩ ቋንቋ ቤተሰቦችን ይዘረዝራሉ፤<br>• ናዋና የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች በመለየት ገለፃ ያደርጋሉ፤ | 4.1. የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህሎችን<br>▪ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ በህሎችን ይለያሉ<br>▪ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ በህላዊ ቅርሶች ይለያሉ<br>▪ የተለያዩ የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦችን<br>▪ በስፋት ያሚነገሩ የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦችን<br>▪ የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች | ▪ ተማሪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ በህሎችን እንዲገልፁ መጠየቅ<br>▪ ተማሪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ባህላዊ ድርጊቶችን እንዲለዩ ማበረታታትናመደራጀት፤<br>▪ ተማሪዎችበኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ በህላዊ ቅርሶች እንዲዘረዝሩ ማበረታት፤<br>▪ ተማሪዎች በጥያቄ ና መልስ ውስጥየተለያዩ የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦችን እንዲዘረዝሩ መጠያቅ፤ | አዲስ ርእስ ከመጀመርዎ በፊት ላለፈው ክፈለጊዜ ትምህርት አጫጭር ጥያቂዎችን መስጠት፤<br>• ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ያልተረዱ ከሆነ ግብረ መልስ በማዘጋጀት ገላጻ ማድረግ፡፡ ገለፃው በሥዕል፣ዲያግራም፣ ወ.ዘ..ተ መደገፍ መሆን አለበት፤<br>• ለእያንዳንዱ ተማሪ ክትትል እየተደረገ መሆኑን ማሳየት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • ተለያዩባ ህላዊና ዘመናዊ የኢትዮጵያ ተቋማትን በመለየት ገለፃ ያደርጋሉ፤<br>• ኢትዮጵያ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴን ይለያሉ፤<br>• ኢትዮጵያን የተለያዩ የግብርና ዘርፎችን በመለየት ገለፃ ያደርጋሉ፤<br>• ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የሚላኩ ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን ይዘረዝራሉ፤<br>• | ▪ የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች መጠቀብና ማስተዋወቀ፤<br>▪ የሚዳሰሱ የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች<br>▪ የማይዳሰሱ የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች<br>▪ የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች የመጠቀብና የማቆየት ሃላፊነትና ድርሻ፤<br>▪ የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህላዊና ዘመናዊ ተቋማት<br>▪ የባህል ልዩነትና ህይወት ያላቸው ነገሮች የነበራቸው በታሪክ ውስጥ ቆይታ፤ | ▪ ተማሪዎች ያተለያዩ ቡድኖችን እንዲመሰርቱ በማድረግ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ በህላዊ ቅርሶች በመዘርዘር እንዲወያዩበት መጠየቅ፤<br>▪ ተማሪዎች ያተለያዩ ቡድኖችን እንዲመሰርቱ በማድረግ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶችን እንዲለዩ መጠየቅ፤<br>▪ ተማሪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ በህሎችን እንዲያደንቁ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች መጠቀብና ማቆየት የመንግስትና የሕብረተሰብ ሃላፊነትና ድርሻ መሆኑን በጥያቄና መልስ መልኩ እንድገልጽ ማድረግ፤ | • ተማሪዎች መልስ ሲመልሱ በትኩረት በመከታተል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት፤<br>• ተማሪዎች በቡድን በሚወያዩበት ወቅት ክትትል በማድረግ አፈፃፀማቸውን መመዝገብ<br>• ከተማሪዎች ለቀረቡ ጥያቄዎችና ሀሳቦች ገለጫ መስጠት<br>• ተማሪዎች ለሰጡት አጭር መልስ ፈጣን ግብረ መልስ በመስጠት መመዝገብ<br>• ተማሪዎች ለሰጡት ሀሳብ ፈጣን ግብረ መልስ መስጠትና ውጤቱን መመዝገብ<br>• ገንቢ የሆነና |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያን ተለያዩ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ይለያሉ፤<br>• ትዮጵያን ከቱሪዝም የምታገኛቸውን ጥቅሞችይለያሉ፤<br>• ኢትዮጵያን የኢንዱስትሪ ቱሪዝም ላይ ተፅዕኖ ያሚያደርሱትን ነገሮችን ይገልፃሉ፡፡ | ▪ (Cultural diversity and its Rootedness in Biodiversity and its history.)<br>▪ በኢትዮጵያን ምጣኔ ሀብት ውስጥ ባህል ያለው ሚና<br>▪ የኢትዮጵያ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ<br>▪ የተለያዩ የግብርና ዘርፎች በኢትዮጵያ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ውስጥ ያለው ሚና፤<br>▪ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ የሚላኩ ዋና ዋና ሰብሎች (crops)<br>▪ ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ውስጥ | ▪ ተማሪዎች የተለያዩ የኢትዮጵያ ባህላዊና ዘመናዊ ተቋማት ጥቅሞችን እንዲገልጹ ማድረግ<br>▪ ተማሪዎች የኢትዮጵያ ዋና ዋና የምጣኔ ሀብት ዘርፎችን እንዲለዩ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች በቡድን በመደራጀት የኢትዮጵያ የግብርና እንቅስቃሴን እንዲገልጹ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች በጥያቄና መልስ መልክ የኢትዮጵያን የተለያዩ የኢንዱስትሪ አይነቶች እንዲዘረዝሩ ማድረግ<br>▪ ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ውስጥ ያለው ሚና እንድገነዘቡ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች በጥያቄና መልስ መልክ የኢትዮጵያን የተለያዩ | የተማሪዎችን ብቃት የሚያሳድግ ግብረ መልስ መስጠት፤<br>• ተማሪዎች ለጠየቁት ጥያቄዎችና ለሰጡት መልሶች ግልፅ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት፤<br>• ተማሪዎችን ለመርዳት በቂ ዝግጅት ማድረግና ግልፅነትን ማዳበር፤<br>• ተማሪዎች የሚሰጠው ትምህትር ላይ የመጡትን ለውጥ በመመዝገብ ለሌሎች ታማሪዎች እንዲሁም ለተማሪወ ቤተሰብ መዘገብ/ማሳወቅ/፡፡<br>• ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ ትምህርታቸውን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ያለው ሚና ፤<br>▪ የኢትዮጵያን የተለያዩ የኢንዱስትሪ አይነቶች<br>▪ የኢትዮጵያን የተለያዩ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ አይነቶች፤<br>▪ ቱሪዝም በኢትዮጵያ የምጣኔ ሀብትና ባህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለው ሚና ፤<br>▪ በኢትዮጵያን የኢንዱስትሪ ቱሪዝም ላይ ተፅዕኖ ያሚያደርሱትን ነገሮች፡፡ | የቱሪዝም አይነቶችና ባህርይ እንዲዘረዝሩ ማድረግ፤<br>▪ የቱሪዝም እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሚና እንዲያገናዝቡ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች በኢትዮጵያን የኢንዱስትሪ ቱሪዝም ላይ ተፅዕኖ ያሚያደርሱትን ነገሮች እንዲገልጹ ማድረግ፤<br>. | መከታተላቸውንናአለመከታተላቸውን መረጃዎችን በማሰባሰብ ማቅረብ፡፡ |

| 5ኛ ክፍል:ምዕራፍ 5 | 5ኛ ክፍል: ምዕራፍ 5<br>ልዩ ትኩረት የሚፈልጉ ጉዳዮ<br>( የክፍለ ጊዜ 30) | የማር ማስተማር ዘዴ | ተከታታይ ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ተለያዩ ኬሚካሎች እና መድሀኒቶች የሚያደረሱትን ጉዳት ትለያለችሁ፤<br>• ስ ስስ የሚያሲዙ ነገርችን ይዘረዝራሉ፤<br>• ወረዳችሁና በዞናችሁ የሚደረጉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ትለያለችሁ፤<br>• ድርቅና ረሀብ ጽንሰ ሀሳብን ይገልፃሉ፤<br>• ኢትዮጵያ የድርቅና ረሀብ መከሰት ምክንያቶች እና የሚያመጡት ችግሮች ይገልፃሉ፤<br>• ኢትዮጵያ ደረቃማና | 5.1.ኤችአይቪ/ኤድስ በኢትዮጵያ<br>5.2 በወረዳችን ውስጥ የተለያዩ ዕጾች እና ኬሚካሎችን አጠቃቀም<br>5.3 በአካቢያችን የሚገኙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች<br>• የሴት ልጅ ግርዛት፣<br>• ድድ መባጠጥ እና እንጥል መቁረጥ<br>• ያለእድሜ ጋብቻ፣<br>• ጠለፋ ናቸው።<br>5.4. ድርቅና ረሀብ<br>5.4.1. የድርቅና ረሀብ ትርጉም<br>5.4.2. በኢትዮጵያ የድርቅና ረሀብ መከስት ምክንያቶች እና የሚያመጡት ችግሮች<br>▪ የኢትዮጵያ ደረቃማ አካባቢዎች<br>▪ ሀገር በቀል ድርቅ ለመቋቋም የሚረዱ | ▪ ተማሪዎች ስለ ድርቅና ረሀብ ምን እን ደሚያውቁ መጠየቅ፤<br>▪ ተማሪዎች ያተለያዩ ቡድኖችን እንዲመሰርቱ በማድረግ የድርቅና ረሀብ መከስት ምክንያቶች እና የሚያመጡት ችግሮች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች ደረቃማና ዝናባማ አካባቢዎች በካርታ ላይ በመመልከት እንዲገልጹ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች የኢትዮጵያን ካርታ በመጠቀም በአንፃራዊ ደረቃማ ቦታዎችን እንዲያሳዩ ማሳተፍ፤<br>▪ ተማሪዎች ስራዎቻቸውን ለክፍል ተማሪዎች እንዲቀርቡ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች የኢትዮጵያ ደረቃማ አካባቢዎችን ሥዕል በመሳል እንዲያሰዩ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች ድርቅ ለመቋቋም | • ተማሪዎች የሰጡትን መልስ በመመልከት<br>• ተማሪዎች በቡድን በሚወያዩበት ወቅት ክትትል በማድረግ<br>• ተማሪዎች ገለፃውበሚያደርጉበት ወቅት ምልከታ ማድረግ፤<br>• የተማሪዎችን ገለፃውና ትግበራ መመዝገብ፤<br>• ለተማሪዎችን ትግበራ ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት፤<br>• ለተከታታይ ምዘና የሚሆኑ ተግባሮችን ለተማሪዎች ማስጠት ለምሳሌ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዝናባማ አካባቢዎች በካርታ ላይ በመመልከት ይገልፃሉ፤<br>• ዝናብ መለኪያ ቴክኖሎጂን በመጠቀም መረጃዎችን የብራራሉ<br>• ኢትዮጵያ ደረቃማ አካባቢዎች ይለያሉ፤<br>• ኢትዮጵያ ሀገር በቀል(indigenous) ድርቅ ለመቋቋም የሚረዱ ነገሮችን ያብራራሉ፡ | ዘዴዎች | የሚረዱ ዘዴዎን በመመልከት እንዲመዘግቡ ማድረግ፡፡<br>. | |